
ካህናተ፡ሰማይ።
አጋዕዝተ፡ዓለም፡ሥላሴ።
ካህናተ፡ሰማይ።

ካህን

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ፩ አምላክ ፡፡

አንድ አምላክ በሆነ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም፡፡

ካህን

ይህች ቀን ምን ያህል የምታስፈራ ናት፤ ይህችስ ሰዓት ምን ያህል የምታስጨንቅ ናት፤ መንፈስ ቅዱስ ከሰማየ ሰማያት የሚወርድባት ናት፤ ይህን መስዋዕቱን የሚሰውርባትና የሚያከብርባት። በጽሞናና በመፍራት ቁሙ፤ የእግዚአብሔር ሰላም ከኔና ከናንተ ጋራ ይሆን ዘንድ ጸልዩ።

How awful is this day and how marvellous this hour wherein the Holy Spirit will descend from heaven and overshadow and hallow this sacrifice. In quietness and in fear stand up and pray that the peace of god be with me and with all of you.

እምነ በሐ፥ ቅድስት ቤተክርስቲያን፥ ሥርጉት አረፋቲሃ በዕንቁ ጳዝዮን፤ እምነ በሐ፥ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን፤

ሰላም ላንቺ ይሁን! እናታችን ክብርት ቤተ ክርስቲያን፤ ግድግዳዎችሽ በጳዝዮን ዕንቁ የተጌጡ ናቸው፤ ሰላም ላንቺ ይሁን እናታችን ክብርት ቤተ ክርስቲያን

Peace be unto you, our mother, O honorable church. Thy walls are embroidered with Topaz. Peace be unto you, out mother, O honorable church

መስቀል አብርሃ በከዋክብት አሠርገወ ሰማየ፤
አምኰሉሰ ፀሀየ አርአየ። መስቀል አብርሃ
በከዋክብት አሠርገወ ሰማየ።
መስቀል አበራ! በኮከቦች ሰማይን አስጌጠ፤
ከሁሉም ፀሀይን አሳየ። መስቀል አበራ፤
በኮከቦች ሰማይን አስጌጠ።
The cross shined and had the heavens embroidered with stars. Of all the sun is seen. The cross shined and had the heavens embroidered with stars.

## ሕዝብ

ኵሉ ዘገብራ ለጽድቅ ጻድቅ ውእቱ ወዘያከብር ሰንበተ ኢይበል ፈላሲ ዘገብአ ኀበ እግዚአብሔር ይፈልጠኒኑ እምሕዝቡ ኵሉ ዘገብራ ለጽድቅ፤ ጻድቅ ውእቱ ወዘያከብር ሰንበተ።

በጎን የሚያደርግ ሰንበትንም የሚያከብር ሁሉ ጻድቅ ነው። ወደ አግዚአብሔር አምልኮ የገባ መፃተኛ ከህዝቡ ሁሉ ይለየኝ ይሆን? አይበል በጎ ያደረገ ሰንበትንም የሚያከብር ጻድቅ ነው።

Blessed is he who does blessed deeds and honors the Sabbath. Let him not question whether he will be outcast from the multitudes if he was to enter into the worship of God. Blessed is he who does blessed deeds and honors the Sabbath.

ሃሌ ሉያ! አመቦ ብእሲ እምእመናን ዘቦአ ቤተ ክርስቲያን በጊዜ ቅዳሴ ወኢሰምዐ መጻሕፍተ ቅዱሳተ ወኢተዐገሠ እስከ ይፌጽሙ ጸሎተ ቅዳሴ

ሃሌ ሉያ በቅዳሴ ጊዜ ከምእመናን ወገን ወደ ቤተ ክርስቲያን የገባ ሰው ቢኖር ቅዱሳት መጻሕፍትን ሰምቶ የቅዳሴውን ጸሎት እስኪጨርሱ ባይታገሥ ከቁርባን ባይቀበል ከቤተ ክርስቲያን ይውጣ

Halleluiah! If there be anyone of the faithful that hath entered the church at the time of mass and hath not heard the holy Scriptures, and hath not waited until they finish the prayer of the Mass, and hath not received the holy communion, let him be driven out of the church:

ወኢተመጠወ እምቁርባን ይሰደድ እምቤተ ክርስቲያን እስመ አማሰነ ሕገ እግዚአብሔር ወአስተሐቀረ ቀመተ ቅድመ ንጉሥ ሰማያዊ ንጉሠ ሥጋ ወመንፈስ ከመዝ መሐሩነ ሐዋርያት በአብጥሊሶሙ

የእግዚአብሔርን ሕግ አፍርሷልና የነፍስና የሥጋ ንጉሥ በሚሆን በሰማያዊ ንጉሥ በክርስቶስ ፊት መቆምን አቃሏልና ሐዋርያት በሲኖዶሳቸው እንዲህ ሲሉ አስተማሩን

for he hath violated the law of God and disdained to stand before the heavenly King, the King of Body and Spirit. This the Apostles have taught us in their canons.

# ከትንሳኤ እስከ በአለ
# ሀምሳ

ሃሌ ሉያ ዮሴፍ ወኒቆዲሞስ ገነዝዎ ለኢየሱስ
በሰንዱናት ለዘተንስአ እሙታን በመንክር ኪን

ሃሌ ሉያ ዮሴፍና ኒቆዲሞስ ድንቅ በሚሆን ጥበብ
ከሙታን ተለይቶ የተነሳ ኢየሱስን በበፍታ ገነዙት

Halleluia, Joseph and Nicodiemus wrapped with
linen cloths Jesus who rose from the dead in
wondrous fashion

## ሕዝብ

አንቲ ውእቱ መሶበ ወርቅ ንጹሕ እንተ ውስቴታ መና ኅቡዕ ኅብስት ዘወረደ እምሰማያት ወሀቤ ሕይወት ለኵሉ ዓለም

የተሰወረ መና በውስጧ ያለባት የወርቅ መሶብ አንቺ ነሽ። ከሰማያት የወረደ ኅብስት ለሰው ሁሉ ድኅነት የሚሰጥ

Thou art the pot of pure gold wherein is hidden the manna, the bread which came down from heaven giving life unto all the world.

## ካህን

ኀሠሥኩ ገጸከ፡፡ ገጸ ዚአከ አኀሥሥ እግዚኦ፡፡ ወኢትሚጥ ገጸከ እምኔየ፡፡ ወኢትትገኃሥ እምገብርከ ተምዒዕከ ፡፡ ረዳኤ ኵንኒ ወኢትግድፈኒ ወኢትትሀየየኒ አምላኪየ ወመድኃንየ ፡፡

ፊትህን ሻሁ አቤቱ ያንተን ፊት እሻለሁ ፊትህን ከኔ አትመልስ ፡፡ ተቈጥተህ ከባርያህ አትለይ፤ ረዳት ሁነኝ አትጣለኝ አምላኬ መድኃኒቴም ቸል አትበለኝ ፡፡

**ካህን**

አውሎግዮስ ጌርዮስ ኢየሱስ ክርስቶስ ወልደ እግዚአብሔር ሕያው አግዮስ ማንጦን ፓንዋማንጦን አሳቲኖን በአማን አሜን ፡፡

የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ በእውነት አውሎግዮስ ጌርዮስ አግዮስ ማንጦን ፓንዋማንጦን አሳቲኖን ነው አሜን ፡፡

ክርስቶስ አምላክነ ዘበአማን ዕተብ በየማንከ ወባርክ
በእዴከ ወቀድስ በኃይልከ ወአጽንዕ በመንፈስከ
ዝንቱ ኅብስት ይኩን ለሥርየተ ኀጢአተ ሕዝብከ
አሜን ፡፡
በእውነት አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቀኝህ
እተብ በእጅህም ባርክ በሀይልህም አክብር
በመንፈስህም አጽና ይህ ህብስት የህዝብህ
የሀጢአታቸው ማስተስረያ ይሆን ዘንድ አሜን።
Christ, our very God, sign with thy right hand,
Bless with thy hand, sanctify with they power and
strengthen with thy Spirit, so that this bread will be
for the remission of the sins of thy people. Amen.

ኢየሱስ ክርስቶስ ሊቀ ካህናት በከመ ገነዙከ ዮሴፍ ወኒቆዲሞስ በልብሰ ሰንዱናት ወአፈዋት ወሠመርከ ሎሙ ከማሁ ሥመር ለነ ፡፡

የካህናት አለቃ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ዮሴፍና ኒቆዲሞስ በበፍታ ልብስና በሽቶ እንደገነዙህ እንደ ወደድህላቸውም እንዲሁ ውደድልን።

Jesus Christ, the High Priest, like as Joseph and Nicodemus wrapped thee in linen cloths and spices, and thou wast well-pleased in them, in like manner be well-pleased in us.

ቅዳሴ ውኩፍ ወአኰቴት ወዕበይ ለሥርየተ ኀጢአት እምኀበ እግዚአብሔር አብ፤ አሜን ፡፡ ኀይል ወበረከት ወብርሃን ዐቢይ ወቅዳሴ ለዛቲ ቤተ ክርስቲያን ፡፡

የሚቀበሉት ቅዳሴ ምስጋናና ክብር ለሀጢአት ማስተስረያ ከእግዚአብሔር አብ የተገኘ ነው አሜን። ኀይል በረከትና ደገኛ ብርሀን ለዚህች ቤተ ክርስቲያን ክብር ይሁን።

The hallowing and the thanksgiving and the exaltation, accepted be they of God the Father, for the remission of sin, Amen, power and blessing and great light and holiness be to this church.

እግዚአብሔር አምላክነ ዘተወከፍከ ቍርባነ አቤል በውስተ በድው ወለኖኅ በውስተ ታቦት ወለአብርሃም በውስተ ርእሰ ደብር

አምላካችን እግዚአብሔር በምድረ በዳ የአቤልን ቁርባን የተቀበልህ የኖህን በመርከብ ውስጥ የአብርሀምን በተራራ ላይ

Lord our God who didst accept the offering of Abel in the wilderness, and of Noah within the Ark, and of Abraham on the top of the mountain,

ወለኤልያስ በደብረ ቀርሜሎስ ወለዳዊት በዐውደ ኦርና ኢያቡሳዊት ወጸሪቀ መበለት በቤተ መቅደስ

የኤልያስንም በቀርሜሎስ ተራራ የዳዊትንም የኢየአቡስ ወገን በምትሆን በኦርና አደባባይ የድሃይቱንም መሀለቅ በቤተ መቅደስ የተቀበልህ

and of Elijah on the top of Carmel, and of David on the threshing floor of Ornan the Jebusite, and the widow's mite in the sanctuary:

ከማሁ ተወከፍ መባአ ወቍርባኖ ለኃጥእ ገብርከ ዘአብአ ለስምከ ቅዱስ፤ ወይኩን ቤዛ ኃጣውኢሁ፤ ወፍድዮ ፍዳ ሠናየ በዝ ዓለም ወበዘይመጽእ ይእዜኒ ወዘልፈኒ ወለዓለመ ዓለም፤ አሜን ።

ለቅዱስ ስምህ ያቀረበውን የሀጥእ ባርያህን መባና ቁርባን እንደርሱ ተቀበል። የሀጢአቱም ቤዛ ይሁን በዚህ አለም በጎ ዋጋን ስጠው በሚመጣውም አለም ዛሬም ዘወትርም ለዘላለሙ አሜን።

Accept likewise the oblation and offering of thy sinful servant which he has brought unto thy holy name, and let it be for the expiation of his sins: recompense in this world and in the world to come, both now and ever and world without end. Amen.

ክርስቶስ አምላክነ ዘበአማን እግዚእነ ዘሖርከ ውስተ ከብካብ፤ አመ ጸውዑከ በቃና ዘገሊላ ወባረከ ሎሙ ወረሰይኮ ለማይ ወይነ ከማሁ ረስዮ ለዝንቱ ወይን ዘንቡር በቅድሜከ።

እውነተኛ አምላካችን ጌታችን ክርስቶስ ሆይ የገሊላ አውራጃ በምትሆን በቃና በጠሩህ ጊዜ ወደ ሰርግ የሄድህ ውሓውንም ባርከህ ጠጅ ያደረግህላቸው በፊትህ የተቀመጠ ይህንን ወይን እንደርሱ አድርገው።

Christ our God, who art truly our Lord, who didst go to the wedding when they called thee in Cana of Galilee, and didst bless for them the water and change it into wine, do thou in like sort unto this wine which is set before thee.

ወይዜኒ ባርኮ ወቀድሶ ወአንጽሖ ይኩን ለሕይወተ ነፍስነ ወሥጋነ ወመንፈስነ በኵሉ ጊዜ ፡፡

አሁንም ባርከው አክብረውም አንጻውም ሁል ጊዜ የስጋችንና የነፍሳችን የልቡናችንም ሕይወት ይሆን ዘንድ ።

Now also let it be blessed, hallowed and pure, so that it may become the life of soul and body and Spirit at all times.

ሀሉ ምስሌነ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ወምላእ ወይነ ትፍሥሕት ወኀሤት ለሠናይ ወለሕይወት ወለመድኃኒት ወለሥርየተ ኃጢአት፤ ለልቡና ወለፈውስ ወለምክረ መንፈስ ቅዱስ ይእዜኒ ወዘልፈኒ ወለዓለም ዓለም፤ አሜን ፡፡

አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ከኛ ጋር ኑር ለተድላና ለደስታ የሚሆን ወይኑንም ለበጎ ነገር ምላው። ለሕይወትና ለመድኀኒት ለሐጢአትም ማስተስረያ ለማስተዋል ለደሕንነት ለመንፈስ ቅዱስም ምክር ዛሬ ዘወትርም ለዘላለሙ አሜን።

Father, Son and Holy Spirit, be with us; and fill the wine with Joy and happiness, for goodness, For life, for salvation and for the remission of sin, for understanding for healing, for the counsel of the Holy Spirit now and ever and world without end. Amen.

ንጹሕ ወጣዕም ወበረከት ለእለ ይሰትዩ
እምደምከ ክብር አላትዮን በአማን አሜን ፡፡

በእውነት ሰው የሆንህ አምላክ ሆይ ንጽህ
ጣዕም በረከትም ከክቡር ደምህ ለሚጠጡ
ይሁን አሜን።

Purity, sweetness and blessing be to them
that truly drink of thy precios blood. Amen.

ቡሩክ እግዚአብሔር አብ አኃዜ ኵሉ ዓለም አምላክነ ፡፡ አሜን

ዓለሙን ሁሉ የያዘ እግዚአብሔር አብ ቡሩክ ነው ፡፡ አሜን

Blessed be the Lord, Almighty Father, our God. Amen And blessed be the only Son, our Lord And our. Amen

ወቡሩክ ወልድ ዋሕድ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ መድኃኒነ ። አሜን

ጌታችን መድኅኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወልድ ዋህድም ቡሩክ ነው ። አሜን

Blessed be the only Son, our Lord and our Saviour Jesus Christ. Amen.

ወቡሩክ መንፈስ ቅዱስ ጳራቅሊጦስ መጽንዒ ወመንጽሔ ኵልነ ። አሜን

ሁላችንን የሚያነጻ የሚያጸና መንፈስ ቅዱስም ቡሩክ ነው ። አሜን

Blessed be the Holy Spirit, the Paraclete, the comforter and cleanser of us all. Amen.

ስብሐት ወክብር ይደሉ ለሥሉስ ቅዱስ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ዕሩይ ኵሎ ጊዜ ይእዜኒ ወዘልፈኒ ወለዓለመ ዓለም አሜን ፡፡

ልዩ ሦስት ለሚሆኑ ሁልጊዜም ለተካከሉ ለአብ ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስ ክብር ምስጋና ይገባል ዛሬም ዘወትርም ለዘላለሙ አሜን።

Glory and honour are due to the holy Trinity, the Father and the Son and the Holy Spirit, always coequal, both now and ever and world without end. Amen.

ጸልዩ አበውየ ወአኀውየ ሳዕሌየ ወሳዕለ ዝንቱ መሥዋዕት ።

አባቶቼና ወንድሞቼ በእኔ ላይመስዋእቱም ላይ ጸልዩ

My fathers and my brothers, pray for me and for this sacrifice.

እግዚአብሔር ይስማዕከ ኵሎ ዘሰአልከ ወይትወከፍ ሥዋዕተከ ወቊርባነከ ከመ መሥዋዕተ መልከ ጼዴቅ ወአሮን ወዘካርያስ ካህናተ ቤተ ክርስቲያኑ ለበኵር ፡፡

እግዚአብሔር የለመንከውን ሁሉ ይስማህ የበኲር የቤተ ክርስቲያኑ ካህናቱ የሚሆኑ የመልከ ጼዴቅንና የአሮንን የዘካርያስንም መስዋእት እንደ ተቀበለ መስዋእትህን ቁርባንህንም ይቀበልልህ።

May God hear thee in all that thou hast asked and accept thy sacrifice and offering like the sacrifice of Melchisedec and Aaron and Zacharias, the priests of the church of the First born;

## አቡነ ዘበሰማያት

Our father who art in heaven…


ካህናተ፡ሰማይ።
አጋዕዝተ፡ዓለም፡ሥላሴ።
ካህናተ፡ሰማይ።

አባታችን ሆይ በሰማያት የምትኖር ስምህ ይቀደስ
መንግስትህ ትምጣ ፈቃድህ በሰማይ እንደሆነች
እንድሁ በምድር ትሁን የእለት እንጀራችንን ስጠን ዛሬ
በደላችንንም ሁሉ ይቅር በለን እኛም የበደሉንን ይቅር
እንደምንል አቤቱ ወደ ፈተና አታግባን ከክፉ ሁሉ
አድነን እንጂ መንግስት ያንተ ናትና ሀይል ክብር
ምስጋና ለዘላለሙ አሜን።

Our father who art in heaven, hallowed be thy name, Thy Kingdom come, Thy will be done on earth as it is in heaven; Give us this ay our trespasses as we forgive them that trespass against us, and lead us not into temptation but delierer us and rescue us from all evil; for Thine is the kingdom, the power and the glory for ever and ever. Amen

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ሆይ በመልአኩ በቅዱስ ገብርኤል ሰላምታ ሰላም እንልሻለን በሀሳብሽ ድንግል ነሽ በስጋሽም ድንግል ነሽ የአሸናፊ የእግዚአብሔር እናት ሆይ ሰላምታ ለአንቺ ይገባሻል ከሴቶች ሁሉ ተለይተሽ አንቺ የተባረክሽ ነሽ የማህጸንሽም ፍሬ የተባረከ ነው ጸጋን የተመላሽ ድንግል ሆይ ደስ ይበልሽ እግዚአብሔር ከአንቺ ጋር ነውና ከተወደደው ልጅሽ ከጌታችን ከመድኀኒታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ዘንድ ይቅርታንና ምህረትን ለምኝልን ሀጢአታችንን ያስተስርይልን ዘንድ ለዘላለሙ አሜን።

O Our Lady, Virgin St. Mary! In St. Gabriel's greetings, Peace be unto you. Holy and pure, O mother of the almighty God! Peace be unto you. Blessed are thou amongst women and blessed is the fruit of thy womb. Hail Mary, full of Grace, the Lord is with Thee. Pray for us before our Lord Jesus Christ that he may forgive us our sins. Amen

ካህን

ተዘከረኒ ኦ አቡየ ቀሲስ በጸሎትከ ቅድስት፡፡

ቄሱ አባቴ ሆይ ክብርት በምትሆን በጸሎትህ አስበኝ፡፡

# ካህን

እግዚአብሔር ይዕቀባ ለክህነትከ ወይትወከፍ መሥዋዕተከ ወቍርባነከ በብሩህ ገጽ ሥመር እግዚኦ ከመ ታድኅነኒ ።

እግዚአብሔር ክህነትህን ይጠብቃት፤ መሥዋዕትህንና ቍርባንህንም በብሩህ ገጽ ይቀበልልህ አቤቱ እኔን ታድነኝ ዘንድ ማዳንን ውደድ ።

ካህን

አሐዱ አብ ቅዱስ
አሐዱ ወልድ ቅዱስ
አሐዱ ውእቱ መንፈስ ቅዱስ

አንዱ አብ ቅዱስ ነው፤
አንዱ ወልድ ቅዱስ ነው፤
አንዱ መንፈስ ቅዱስም ቅዱስ ነው።

One is the Holy Father,
One is the Holy Son,
One is the Holy Spirit.

## ሕዝብ

በአማን አብ ቅዱስ
በአማን ወልድ ቅዱስ
በአማን ውእቱ መንፈስ ቅዱስ።

አብ በእውነት ቅዱስ ነው፤
ወልድም በእውነት ቅዱስ ነው፤
መንፈስ ቅዱስም በእውነት ቅዱስ ነው።

Truly the Father is Holy, truly the Son is Holy, truly the Holy Spirit is holy.

## ካህን

ሰብሕዎ ለእግዚአብሔር ኵልክሙ አሕዛብ
ምዕመናን ሁላችሁም እግዚአብሔርን
አመስግኑት
Praise the Lord, all ye nations.

## ሕዝብ

ወይሴብሕዎ ኵሎሙ ሕዝብ
ሕዝብ ሁሉ ያመሰግኑታል
And praise Him, all ye people.

ካህን

እስመ ጸንዓት ምሕረቱ ላዕሌነ

ምሕረቱ በእኛ ላይ ጸንታለችና

For His merciful kindness is great toward us.

ሕዝብ

ጽድቀሰ ለእግዚአብሔር ይሄሉ ለዓለም

የእግዚአብሔር ቸርነት ለዘለዓለም ጸንቶ ኖሯልና

And the Truth of the Lord endureth forever.

ካህን (ካህኑን በመከተል ሕዝቡ ይህንን ይድገም)

ስብሐት ለአብ፣ ወወልድ፣ ወመንፈስ ቅዱስ

ለአብ ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስ ክብር ምስጋና ይገባል

Glory be to the Father and to the Son and to the Holy Spirit

ካህን (ካህኑን በመከተል ሕዝቡ ይህንን ይድገም)

ይእዜኒ ወዘልፈኒ ወለዓለመ ዓለም አሜን ሃሌ ሉያ

ዛሬም ዘወትርም ለዘለዓለሙ አሜን ሃሌ ሉያ

Both now and ever and world without end. Amen.

## ዲያቆን

ተንሥኡ ለጸሎት

ለጸሎት ተነሱ

Stand up for prayer.

## ሕዝብ

እግዚኦ ተሣሃለነ

አቤቱ ይቅር በለን

Lord have mercy upon us.

## ካህን

**ሰላም ለኲልክሙ**

**ሰላም ለሁላችሁ ይሁን**

Peace be unto you all.

## ሕዝብ

**ምስለ መንፈስከ**

**ከመንፈስህ ጋር**

And with Thy spirit.

## የቅዱስ ባስልዮስ የምስጋና ጸሎት

## *The "Prayer of Thanksgiving" of St. Basil.*

ለእኛ በጎ ነገርን ያደረገ ይቅር ባይ እግዚአብሔርን እናመሰግነዋለን። ይቅር ባይ የጌታችን የአምላካችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አባት ሰውሮናልና ረድቶናልና ጠብቆ አቅርቦናልና ወደ እርሱም ተቀብሎናልና አጽንቶ ጠብቆናልና እስከዚች ሰዓት አድርሶናልና።

We give thanks unto the doer of good things unto us, the merciful God, the Father of our Lord and our God and our Savior Jesus Christ: for He hath covered us and succored us, He hath kept us and brought us nigh and received us unto Himself, and undertaken our defense, and strengthened us, and brought us unto this hour.

አሁንም ክብርት በምትሆን በዚች ዕለት በሕይወታችን ዘመን ሁሉ በፍጹም ሰላም ሁሉን የሚይዝ አምላካችን እግዚአብሔር ይጠብቀን ዘንድ እንለምነው።

Let us therefore pray unto Him that the Almighty Lord our God keep us in this holy day and all the days of our life in all peace.

ዲያቆን

ጸልዩ

Pray ye.

## ካህን

ሁሉን የያዝህ ጌታችን እግዚአብሔር የጌታችንና የአምላካችን የመድሀኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አባት በስራው ሁሉ ላይ ስለ ስራው ሁሉ በስራውም ሁሉ ውስጥ እናመሰግንሀለን። ሰውረኸናልና ረድተኸናልና ጠብቀኸናልና ወዳንተ አቅርበህ ጠብቀኸናልና አጽንተህ ጠብቀኸናልና እስከዚችም ሰአት አድርሰኸናልና።

Master, Lord God Almighty, the Father of our Lord and our God and our Savior Jesus Christ, we render Thee thanks upon everything, for everything and in everything, for Thou hast covered us and succored us, hast kept us and brought us nigh, and received us unto Thyself, and undertaken our defense, and strengthened us and brought us unto this hour.

## ዲያቆን

ኅሡ ወአስተብቍኡ ከመ ይምሀረነ እግዚአብሔር ወይሳሃል ላዕሌነ ወይትወከፍ ጸሎተ ወስእለተ እምነ ቅዱሳኒሁ በእንቲአነ በዘይሴኒ ኩሎ ጊዜ ይረስየነ ድልዋነ ከመንንሳእ እምሱታፌ ምስጢር ቡርክ ወይስረይ ለነ ኃጣውኢነ

እግዚአብሔር ይምረን ዘንድ በእኛም ላይ ይቅር ይል ዘንድ እሹ ለምኑ። ስለእኛ ከቅዱሳን ጸሎትን ልመናንም ይቀበል ዘንድሁልጊዜ ባማረ ነገር ቡሩክ ከሚሆን ምስጢር አንድነተት እንድንቀበል የበቃን ያደርገን ዘንድ

Entreat ye and beseech that the lord have pity upon us and be merciful to us and receive prayer and supplication from his saints on our behalf according to what is expedient at all times, so that he may make us meet to partake of the communion of the blessed sacrament and forgive us our sins.

ሕዝብ

ኪርዬኤሌይሶን

Kyrie eleison.

ካህን/*Priest*

ስለዚህ እንለምንሃለን ከቸርነትህም እንሻለን ሰውን የምትወድ ሆይ ክብርት የምትሆን ይህችን እለት እንድንፈጽም ስጠን የሕይወታችንን ዘመን ሁሉ በፍጹም ሰላም አንተን ከመፍራት ጋር ቅንአትን ሁሉ መከራውንም ሁሉ የሰይጣንንም ስራ ሁሉ የክፎች ሰዎችንም ምክር የጠላትንም መነሳት የተሰወረውንና የተገለጸውን አቤቱ ከእኔ አርቅ ከህዝብሕም ሁሉ ያንተ ከሚሆን ከዚህም ቅዱስ ቦታ

For this cause we pray and entreat of thy goodness, O lover of man, grant us to complete this holy day and all the days of our life in all peace along with thy fear. All envy, all trial, all the working of Satan, the counsel of evil, and all the uprisings of adversaries, secret and open. Remove far from me and from all thy people and from this thy holy place.

በጎውን ነገር ሁሉ ያማረውንና የሚሻለውን እዘዝልን እባቡን ጊንጡንም የጠላትንም ኃይል ሁሉ እንረግጥ ዘንድ ስልጣንን የሰጠኸን አንተ ነህና። ወደ መከራ አታግባን ከክፉ ነገር ሁሉ አድነን እነጂ አንድ ልጅህ ጌታችንና አምላካችን መድሐኒታችንም ኢየሱስ ክርስቶስ ለሰው ፍቅር ብሎ ባደረገው ቸርነትና ይቅርታ በርሱ ያለ ምስጋና ክብር ጽንእ ከእርሱ ጋራ ላንተ ይገባል ካንተ ጋራ ትክክል ማህየዊ ከሚሆን ከመንፈስ ቅዱስም ጋራ ዛሬም ዘወትርም ለዘላለሙ አሜን።

All good things, that are expedient and excellent, command thou for us, for thou art He that hath given us power to tread upon serpents and scorpions and upon all the power of the enemy.  Lead us not into temptation, but deliver us and rescue us from all evil: in the grace and loving kindness which were shown by the love towards mankind of thy only-begotten son, our lord and our God and our savior Jesus Christ, through whom to thee with Him and with the holy spirit, the life-giver, who is coequal with thee are fitting glory and honor and dominion, both now and ever and world without end. Amen.

ዲያቆን

ተንሥኡ ለጸሎት

ለጸሎት ተነሱ

Stand up for prayer.

ሕዝብ

እግዚኦ ተሣሃለነ

አቤቱ ይቅር በለን

Lord have mercy upon us.

## ካህን

ሰላም ለኲልክሙ
ሰላም ለሁላችሁ ይሁን
Peace be unto you all.

## ሕዝብ

ምስለ መንፈስከ
ከመንፈስህ ጋር
And with Thy spirit.

## ንፍቅ ካህን፤ የሐዋርያት የመባ ጸሎት

ዳግመኛም ሁሉን የሚይዝ የጌታችንንና የመድኃኒታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን አባት እግዚአብሔርን እንማልዳለን ከሁሉ በላይ በምትሆን በከበረች በአንዲት ቤተ ክርስቲያን መባ ስለሚያገቡ መስዋዕቱን ቀዳምያቱን ከአስር አንዱን የመታሰቢያ ምስጋና ብዙውንና ጥቂቱን የተሰወረውንና የተገለጸውን ይሰጡ ዘንድ ሲወዱ የሚሰጡት ከሌላቸው ላይ ፈቃዳቸውን ተቀብሎ መንግስተ ሰማያትን ይሰጥ ዘንድ ለሁሉ በረከትን የሚያድልበት ስልጣን ገንዘቡ የሚሆን አምላካችን እግዚአብሔር።

## Asst. Priest:-"The prayer of Oblation" of the Apostles.

And again let us beseech the Almighty Lord, the Father of the Lord our Savior Jesus Christ, on behalf of those who bring an oblation within the one holy universal church, a sacrifice, first-fruits, tithes, a thank offering, a memorial, whether much or little, in secret or openly, and of those who wish to give and have not wherewith to give, that He accept their ready mind, that He vouchsafe to them the heavenly kingdom; power over all works of blessing belongs to the Lord our God.

ንፍቅ ዲያቆን

ጸልዩ በእንተ እለ ያበውኡ መባአ

መባ ስለሚያገቡ ሰዎች ጸልዩ

Pray for them who bring an oblation.

## ሕዝብ

ተወከፍ መባኦሙ ለአኃው ወተወከፍ መባኦን ለአኃት ለነኒ ተወከፍ መባአነ ወቍርባነነ

የወንዶችን መባ ተቀበል የሴቶችንም መባ ተቀበል። የኛንም መባችንን ቁርባናችንን ተቀበልልን።

Accept the oblation of our brethren, accept the oblation of our sisters, and ours also accept, our oblation and our offering.

## ንፍቅ ካህን/*Asst. Priest*

**ሁሉን የምትገዛ አምላካችን እግዚአብሔር ሆይ እንለምንሃለን እንማልድሃለንም ከሁሉ በላይ በምትሆን ባንዲት ቅድስት ቤተ ክርስትያን ውስጥ መባ ስለሚያገቡ ሰዎች መስዋእቱን መጀመሪያውን ካስር አንዱን የመታሰቢያ ምስጋናን ብዙውንና ጥቂቱን የተሰወረውንና የተገለጸውን ይሰጡም ዘንድ ሲወዱ የሚሰጡት ከሌላቸው ላይ ፈቃዳቸውን ተቀብለህ ለሁሉም የበረከት ዋጋን ስጥ እድል ፈንታ ትሆን ዘንድ በአንድ ልጅህ በርሱ ያለ ክብር ጽንእ ላንተ ይገባል ከርሱ ጋራ ከመንፈስ ቅዱስም ጋራ ዛሬም ዘወትርም ለዘላለሙ አሜን።**

Lord our God who art Almighty, we pray Thee and beseech Thee for them that bring an oblation within the one holy universal church, a sacrifice, first-fruits, tithes, a thank offering, a memorial, whether much or little, in secret or openly, and for those who wish to give and have not wherewith to give. Thy acceptance of their ready mind grant Thou unto every one: let the recompense of blessing be a portion to all of them: through Thy only begotten Son, through whom to Thee with Him and with the Holy Spirit be glory and dominion, both now and ever and world without end.

ዲያቆን

ተንሥኡ ለጸሎት

ለጸሎት ተነሱ

Stand up for prayer.

ሕዝብ

እግዚኦ ተሣሃለነ

አቤቱ ይቅር በለን

Lord have mercy upon us.

ካህን

ሰላም ለኵልክሙ
ሰላም ለሁላችሁ ይሁን
Peace be unto you all.

ሕዝብ

ምስለ መንፈስከ
ከመንፈስህ ጋር
And with Thy spirit.

# የኅብስት ጸሎት

## *''The prayer of Oblation.''*

መምህሬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ከቀዳማዊ አብ ጋራ አንድ የምትሆን፤ ንጹሕ የሚሆን የአብ ቃል፤ የማሕየዊ መንፈስ ቅዱስም ቃል፤ ከሰማያት የወረድህ የሕይወት ኅብስት አንተ ነህ ስለ ዓለሙ መዳን ነውር የሌለበት መስዋዕት እንድትሆን መናገርን አስቀደምህ

O my Master, Jesus Christ, co-eternal pure Word of the Father, and Word of the Holy Spirit, the life giver, Thou art the bread of life which didst come down from heaven, and didst foretell that Thou wouldest be the Lamb without Spot for the life of the world:

አሁንም ከበጎነትህ ቸርነት እንለምናለን እንማልዳለንም ሰው ወዳጅ ሆይ ያንተ በሚሆን በዚህ በመንፈሳዊ ታቦት ላይ ባኖርነው በዚህ ኅብስት ላይና በዚህ ጽዋ ላይ ፊትህን ግለፅ ይህንን ኅብስት ባርከው፤ ይህንንም ጽዋ አክብረው ሁለቱንም አንጻቸው ።

We now pray and beseech of Thine excellent goodness, O lover of man, make Thy face to shine upon this bread, and upon this cup, which we have set upon this spiritual ark of Thine: Bless this bread, and hallow this cup, and cleanse them both.

ይህ ኅጱሕ ሥጋህን ይሆን ዘንድ ለውጠው፤ በዚህ ጽዋ ውስጥ የተቀዳውም ወይን የከበረ ደምህን ይሁን ለሁላችንም ያረገ ለነፍሳችንና ለሥጋችን ለልቡናችንም ፈውስ ይሆን ዘንድ።

And change this bread to become Thy pure body, and what is mingled in this cup to become Thy precious blood, let them be offered for us all for healing and for the salvation of our soul and our body and our spirit.

አምላካችን ክርስቶስ የሁላችን ንጉሥ አንተ ነህ፤ ከፍ ያለ ምስጋናንና ክብርን ስግደትንም ለአንተ እንልካለን ቸር ከሚሆን ከሰማያዊ አባትህ ጋራ ከአንተ ጋራ ከሚተካከል ከማሕየዊ መንፈስ ቅዱስም ጋራ ዛሬም ዘወትርም ለዘላለሙ አሜን።

Thou art the King of us all, Christ our God, and to Thee we send up high praise and glory and worship, with Thy good heavenly Father and the Holy Spirit, the life giver, who is co-equal with Thee, both now and ever and world without end. Amen.

## ዲያቆን

ይህ የአባቶቻችን የሐዋርያት ትእዛዝ ነው። ሰው በልቦናው ቂምንና በቀልን ቅንዓትንና ጠብን በባልንጀራው ላይ በማንም ላይ ቢሆን አይያዝ።

## Deacon

This is the order of our fathers the Apostles: Let none Keep in his heart malice or revenge or envy or hatred towards his neighbor, or towards any other body.

ዲያቆን

ስግዱ ለእግዚአብሔር በፍርሃት

በፍርሃት ሆናችሁ ለእግዚአብሔር ስገዱ

Worship the Lord with fear.

ሕዝብ

ቅድሜከ እግዚኦ ንሰግድ ወንሴብሐከ

አቤቱ እያመሰገንህ ከፊትህ እንሰግዳለን

Before Thee, Lord, we worship, and
Thee do we glorify.

ተንበርከኩ

bow

# ጸሎት (ፍትሐት ዘወልድ)

## The Absolution of the son.

**አቤቱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወልድ ዋሕድ የእግዚአብሔር አብ ቃል፤ ማሕየዊት መድኃኒትም በምትሆን በሕማምህ ከእኛ የኃጢአታችንን ሁሉ ማሰርያ ያጠፋህ፡፡ ንጹሓን በሚሆኑ ደቀ መዛሙርትህና በንጹሓን አገልጋዮችህ ፊት እፍ ያልህባቸው መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ፤ ይቅር ላላችኋቸው ኃጢአታቸው ይቀርላቸዋል፤ ይቅርም ላላላችኋቸው ኃጢአታቸው አይቀርላቸውም ያልካቸው፡፡**

Master, Lord Jesus Christ, the Only-begotten Son, the Word of God the Father, who hast broken off from us all the bonds of our sins through Thy life-giving and saving sufferings, who didst breathe upon the face of Thy holy disciples and pure ministers saying to them: Receive the Holy Spirit: whatsoever man's sins ye remit they are remitted unto them, and whatsoever sins ye retain they are retained:

አሁንም በክብርት ቤተ ክርስቲያንህ ሁልጊዜ የክህነትን ሥራ ለሚሠሩ ለንጹሓን አገልጋዮችህ አቤቱ አንተ ክህነትን ሰጠህ፤ በምድር ላይ ኃጢአትን ይቅር ይሉ ዘንድ፡፡ ያስሩ ዘንድ የበደልንም ማሰሪያ ሁሉ ይፈቱ ዘንድ፡፡ አሁንም አቤቱ ሰው ወዳጅ ሆይ፤ ደግመኛ ከቸርነትህ እንለምናለን እንሻለንም፡፡ ስለነዚህ ስለ ወንዶችም ስለ ሴቶችም ባሮችህ፤ አባቶቼና ወንድሞቼ እኅቶቼም፤ ደካማ ስለምሆን ስለ እኔም ስለ ባርያህ፤ በቅዱስ መሠዊያህም ፊት ራሳቸውን ዝቅ ስለ አደረጉ ሰዎች የምሕረትህን ጐዳና ጥረግልን፤

Thou therefore, O Lord, hast now granted the priesthood to Thy pure ministers that do the priests; office at all times in Thy holy church that they may remit sin on earth, may bind and loosen all the bonds of iniquity. Now again we pray and entreat of Thy goodness, O lover of man, on behalf of these Thy servants and handmaids, my fathers and my brothers and my sisters, and also on my own behalf, on me Thy feeble servant, and on behalf of them that bow their heads before Thy holy altar: prepare for us the way of Thy mercy,

የኃጢአታችንን ማሰሪያም ሁሉ ፈጽመህ አጥፋልን፤ አቤቱ አንተን ብንበድል በማወቅ ወይም ባለማወቅ በተንኰልም ቢሆን በልቡና ክፋትም ቢሆን በመሥራትም ቢሆን በመናገርም ቢሆን በዕውቀት ማነስም ቢሆን፤ የሰውን ድካሙን አንተ ታውቃለህና። ቸር ሰው ወዳጅ ሆይ የፍጥረቱ ሁሉ ጌታ አቤቱ የኃጢአታችንን ሥርየት ስጠን፤ ባርከን፤ አክብረንም ነጻም አድርገን፤ አንጻን የተፈታን ነጻም የወጣን አድርገን፤ ሕዝቡንም ሁሉ ፍታቸው። ስምህን መፍራትንም የተመላን አድርገን። ቅዱስ ፈቃድህንም በመፍራት አጽናን።

break and sever all the bonds of our sins, whether we have trespassed against Thee, O Lord, wittingly or unwittingly or in deceit or in evilness of heart, whether in deed or in work or through smallness of understanding, for Thou knowest the feebleness of man. O good lover of man and Lord of all creation, grant us, O Lord, forgiveness of our sins, bless us and purify us and set us free and absolve all Thy people and fill us with the fear of Thy name, and establish us in the doing of Thy holy will.

ቸር ሆይ ጌታችንና አምላካችን መድኃኒታችን አንተ ኢየሱስ ክርስቶስ ነህና ። ምስጋናንና ክብርን ላንተ እናቀርባለን ። ሰማያዊ ከሚሆን ከቸር አባትህ ጋራ፤ ማሕየዊ ከሚሆን ከመንፈስ ቅዱስም ጋራ ትክክል የሚሆን ዛሬም ዘወትርም ለዘላለሙ፤ አሜን ።
በዚህች ቀን ያገለገሉህ ባሮችህ ቄሱና ዲያቆኑ ካህናቱም ሕዝቡም ሁሉ እኔም ድኃው ባርያህ የተፈቱና ነጻ የወጡ የነጹ ይሁኑ።

O Good, for Thou art our Lord and our God and our Savior Jesus Christ, to Thee we send glory and honor with Thy good heavenly Father, and Holy Spirit, the life-giver, who is co-equal with Thee, both now and ever and world without end. Amen.
May Thy servants who serve on this day, the priest and the deacon and the clergy and all the people, and I myself Thy poor servant, be absolved and set free,

ልዩ ሦስት በሚሆን በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ አፍ፤ ሐዋርያት በሰበሰቧት በቅድስት ቤተ ክርስቲያን አፍ፤ በዓሥራምስቱ ነቢያት አፍ፤ በዓሥራ ሁለቱ ሐዋርያት አፍ፤ ሥልጣን አገልጋዮች በሆኑ በሰባ ሁለቱ አርድእት አፍ መለኮትን በተናገረ ወንጌላዊ ሐዋርያና ሰማዕትም በሆነ በማርቆስ አፍ። ንጹሕ ክቡር አባት በሚሆን በጳጳሳቱ አለቃ በሳዊሮስና በቅዱስ ዲዮስቆሮስ በቅዱስ አትናቴዎስም በቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅና በቅዱስ ቄርሎስ በቅዱስ ጎርጎርዮስና በቅዱስ ባስልዮስ ቃል።

and cleansed out of the mouth of the Holy Trinity, the Father and the Son and the Holy Spirit, and out of the mouth of the one holy apostolic church, and out of the mouths of the fifteen prophets, and out of the mouths of the twelve apostles, and out of the mouths of the seventy-two disciples the ministers, and out of the mouth of the speaker of divinity, the evangelist Mark the apostle and martyr: and out of the mouths of the honored Patriarchs St. Serverus and St. Dioscorus and St. Athanasius and St. John Chrysostom and St. Cyril and St. Gregory and St. Basil:

አርዮስን ለማውገዝ በኒቅያ በተሰበሰቡ ሃይማኖታቸው በቀና በሦስት መቶ ዐሥራ ስምንት ሊቃውንትም ቃል፡፡ መቅዶንዮስን ለማውገዝ በቊስጥንጥንያ በተሰበሰቡ በመቶ አምሳው ሊቃውንትም ቃል ንስጥሮስን ለማውገዝ በኤፌሶን በተሰበሰቡ በሁለት መቶ ሊቃውንትም ቃል በክቡር የሊቃነ ጳጳሳቱ አለቃ በአባ ---፯ ንዑድ ክቡር በሚሆን በሊቀ ጳጳሳችን አባ ---፯ ቃል ድኃ ምስኪን በምሆን በኔም በኃጥኡ ቃል የተፈቱ ነጻም የወጡ ይሁኑ፡፡

and out of the mouths of the 318 orthodox that assembled in Nicaea to condemn Arius, and out of the mouths of the 150 that assembled in Constantinople to condemn Macedonius, and out of the mouth of the 200 that assembled in Ephesus to condemn Nestor, and out of the mouth of the honored Patriarch and the blessed Archbishop, and out of the mouth of me also the sinful and miserable and poor,

አምላክን በወለደች በሁለት ወገን ድንግል በሆነች ባዲሲቱ መሣሪያ በክብርት እመቤታችን በማርያም ቃል። የቅዱስ ስምህ ምስጋና ቡሩክ ፍጹም ነውና፤ ልዩ ሦስት የምትሆን አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ሆይ፤ ዛሬም ዘወትርም ለዘለዓለሙ፤ አሜን።

O may they be absolved and set free, and out of the mouth of our Lady Holy Mary, of twofold virginity, mother of God, the new loom; for Thy holy name is blessed and full of glory, O holy Trinity, Father and Son and Holy Spirit, both now and ever and world without end. Amen.

ዲያቆኑ ሲጸልይ ሕዝቡ በመከተል በየምዕራፉ «አሜን ኪርዬኤሌይሶን አቤቱ ይቅር በለን» ይበል

ዲያቆን

አንድ ስለምታደርግ ሥጋውና ደሙ እግዚአብሔር በይቅርታው አንድ ያደርገን ዘንድ ሰላምን እንማልዳለን

For the peace holy things we beseech, that God may grant us peace through His Mercy

እግዚአብሔር የሱን ሃይማኖት በንጹሕ እንድንጠብቅ ይሰጠን ዘንድ ስለ ሃይማኖታችን እንማልዳለን

For our Faith we beseech, that God may grant us to keep the faith in purity.

እስከ ፍጻሜያችን ድረስ እግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ አንድነት ይጠብቀን ዘንድ ስለ አንድነታችን እንማልዳለን

For our congregation we beseech, that God may keep us unto the end in the communion of the Holy Spirit.

በመከራችን ሁሉ እግዚአብሔር የትዕግሥትን ፍጻሜ ይሰጠን ዘንድ ስለ ነፍሳችን ትዕግሥት እንማልዳለን

For patience of soul we beseech, that God may vouchsafe us perfect patience in all our tribulation

ቅዱሳን ስለሚሆኑ ነቢያት ከሳቸው ጋራ እግዚአብሔር ይቈጥረን ዘንድ እንማልዳለን

For the holy prophets we beseech, that God may number us with them.

እነሱ ደስ እንዳሰኙት ደስ ልናሰኘው እግዚአብሔር (ማገልገሉን) ይሰጠን ዘንድ እድል ፈንታቸውንም ያድለን ዘንድ አገልጋዮች ስለሚሆኑ ሐዋርያት እንማልዳለን

For the ministering Apostles we beseech, that God may grant us to be well pleasing even as they were well pleasing, apportion unto us a lot with them.

እግዚአብሔር ለኛ የሰማዕትነትን ሥራ ይሰጠን ዘንድ ቅዱሳን ስለሚሆኑ ሰማዕታት እንማልዳለን

For the Holy martyrs we beseech, that God may grant us to perfect the same conversation.

የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች እነሱ ናቸውና
እግዚአብሔር እነሱን ለረጅም ወራት ይሰጠን
ዘንድ ያለ ነውር በንጽሕና ሆነው በእውቀት
የሃይማኖትን ቃል ያቀኑ ዘንድ ስለ ርእሰ
ሊቃነ ጳጳሳቱ ብፁዕ ስለሚሆን ስለ ሊቀ
ጳጳሳችንም እንማልዳለን

For our Patriarch and the blessed Archbishop we beseeech, that grant them length of days to be over us, that with understanding they may rightly speak the word of faith in purity without spot for that they are the defenders of the church.

የክህነትን ሥልጣን ከእነሱ እግዚአብሔር እን ዳያርቅ መትጋትን እሱን መፍራትንም እስከ ፍጻሜ ይሰጥልን ዘንድ ድካማቸውንም ይቀበል ዘንድ ስለ ቀሳውስት እንማልዳለን

For the priests we beseech, that God may never take from them the spirit of priesthood, and may give them the grace of zeal and fear of Him unto the end and accept their labor.

ፈጽመው ሲፋጠኑ መፋጠንን እግዚአብሔር ሰጣቸው ዘንድ በቅድስናም ይቀርቡ ዘንድ ድካማቸውንና ፍቅራቸውንም ያስብ ዘንድ ስለ ዲያቆናት እንማልዳለን

For the deacons we beseech, that God may grant them to run a perfect course, and draw them high unto Him in holiness, and remember their labor and their love.

የሃይማኖታቸውን ትጋት ሲፈጽሙ እግዚአብሔር ይሰጣቸው ዘንድ ስለ ንፍቀ ዲያቆናት ስለ አንባቢዎችም ስለ መዘምራንም እንማልዳለን

For the assistant deacons and the anagnosts and the singers we beseech, that God grant them to perfect the diligence of their faith.

ልመናቸውን ይሰማቸው ዘንድ ይልቁንም የመንፈስ ቅዱስን ሀብት በልቡናቸው ያሳድርባቸው ዘንድ ድካማቸውንም ይቀበል ዘንድ ስለ ባልቴቶች ረዳትም ስለሌላቸው እንማልዳለን

For the widows and the bereaved we beseech, that God may hear their prayers and vouchsafe them abundantly in their hearts the grace of the Holy Spirit and accept their labor.

እግዚአብሔር የድንግልናቸውን ዋጋ (አክሊል) ይሰጣቸው ዘንድ ለእግዚአብሔርም ወንዶችም ሴቶች ልጆች ይሆኑት ዘንድ ድካማቸውንም ይቀበል ዘንድ ስለ ደናግል እንማልዳለን

For the virgins we beseech, that God may grant them the crown of virginity, and that they may be unto God sons and daughters and that He may accept their labor.

በመታገሣቸው ዋጋቸውን ይቀበሉ ዘንድ እግዚአብሔር እንዲሰጣቸው ስለ ሚታገሡ ሰዎች እንማልዳለን

For those who suffer patiently we beseech, that God grant them to receive their rewards through patience.

በንጽሕና ሆነው ይጠብቁ ዘንድ እግዚአብሔር ሃይማኖትን እንዲሰጣቸው ስለ ሕዝባውያንና ስለ መሃይምናን እንማልዳለን

For the laity and faithful we beseech, that God may grant them complete faith which they may keep in purity.

በጎውን ዕድል ኃጢአትን ለማስተሥረይ ሁለተኛ መወለድ የሚገኝበትን ሕጽበት እግዚአብሔር ይሰጣቸው ዘንድ በቅድስት ሥላሴም ማኅተም ያከብራቸው ያትማቸው ዘንድ ስለ ንኡሰ ክርስቲያን እንማልዳለን

For the catechumens we beseech, that God may grant them a good portion and the washing of regeneration for the remission of sin, and seal them with the seal of the Holy Trinity.

በዘመኑ ፍጹም ሰላምን እግዚአብሔር ይሰጣት
ዘንድ እግዚአብሔርን ስለምትወድ
ስለ አገራችን ኢትዮጵያ እንማልዳለን

For our country Ethiopia we beseech, that God may give her peace forever.

እውቀትን እሱን መፍራትንም እግዚአብሔር
ይሰጣቸው ዘንድ ስለ መኳንንትና ሥልጣን
ስላላቸው እንማልዳለን

For the rulers and those in authority we beseech, that God may grant them of His wisdom and His fear.

ስለዓለሙ ሁሉ እግዚአብሔር ማሰብን ያስቀድም ዘንድ ለእያንዳንዱም የሚያስፈልገውን ያማረውን የሚሻውንም ያስብ ዘንድ ስለ ዓለም ሁሉ እንማልዳለን

For the whole world we beseech, that God should hasten His purpose and put into the mind of all and each to desire that which is good and expedient.

እግዚአብሔር ይቅርታ ባለው ቀኝ መርቶ ፍቅርና በደኅንነት ወደ ማደሪያቸው ይመልሳቸው ዘንድ በባሕርና በደረቅ ስለሚሄዱ ሰዎች እንማልዳለን

For them that travel by sea and by land we beseech, that God should guide them with a merciful right hand and let them enter their home in safety and peace.

እግዚአብሔር የዕለት የዕለት ምግባቸውን ይሰጣቸው ዘንድ ስለ ተራቡና ስለ ተጠሙ ሰዎች እንማልዳለን

For the hungry and the thirsty we beseech, that God should grant them their daily food.

እግዚአብሔር ፈጽሞ ያረጋጋቸው ዘንድ ስለ አዘኑና ስለ ተከዙ ሰዎች እንማልዳለን

For the sad and the sorrowful we beseech, that God may give them perfect consolation

እግዚአብሔር ከእሥራታቸው ይፈታቸው ዘንድ ስለ ታሰሩ ሰዎች እንማልዳለን

For the prisoners we beseech, that God may loose them from their bonds.

እግዚአብሔር በሰላም ወደ አገራቸው ይመልሳቸው ዘንድ ስለ ተማረኩ ሰዎች እንማልዳለን

For the captives we beseech, that God may restore them to their county in peace.

እግዚአብሔር ትዕግሥትን በጎ ትምህርትንም ይሰጣቸው ዘንድ የድካማቸውንም ፍጹም ዋጋ ይሰጣቸው ዘንድ ስለ ተሰደዱ ሰዎች እንማልዳለን

For those who were sent away we beseech, that God should grant them patience and good instruction, and give them complete reward for their labor.

እግዚአብሔር ፈጥኖ ያድናቸው ዘንድ ይቅርታውንና ቸርነቱንም ይልክላቸው ዘንድ ስለ ታመሙትና ስለ ድውያኑ እንማልዳለን

For the sick and the diseased we beseech, that God should heal them speedily and send upon them mercy and compassion.

ከቅድስት ቤተ ክርስቲያን ወገን ስለ ሞቱ ሰዎች እግዚአብሔር የዕረፍት ቦታ ይሰጣቸው ዘንድ እንማልዳለን

For those who have fallen asleep in his holy church we beseech, that God may vouchsafe them a place to rest.

እግዚአብሔር እንዳይቀየማቸው ከመዓትም ተመልሶ ፍጹም ዕረፍትን ይሰጣቸው ዘንድ ስለ በደሉ አባቶቻችንና ወንድሞቻችን እንማልዳለን

For those who have sinned, our fathers and our brothers we beseech, that God cherish not anger against them, but grant them rest and relief from His wrath.

በሚሻበት ቦታ እግዚአብሔር ዝናቡን ያዘንብ ዘንድ ስለ ዝናብ እንማልዳለን

For the rains we beseech, that God may send rain on the place that needs it.

የወንዙን ውኃ ሙላልን ብለን እግዚአብሔር እነሱን እስከ ልካቸውና እስከ ወሰናቸው ይሞላ ዘንድ ስለ ወንዝ ውኃ እንማልዳለን

For the water of the rivers we beseech, that God should fill them unto their due measure and bounds.

ስዘርና ስመከር ሲሆን እግዚአብሔር ስምድር ፍሬዋን ይሰጣት ዘንድ ስለ ምድር ፍሬ እንማልዳለን

For the fruits of the earth we beseech, that God may grant to the earth her fruit for sowing and for harvest.

በጸሎት የምንለምንና የምንማልድ ሁላችንንም በሰላም በመንፈስ ይጠብቀን፤ ፍቅርንም ይስጠን ዓይነ ልቡናችንንም ያብራልን፤ ፈቃዱም ሆኖ ጸሎታችንን ይቀበል ዘንድ ቀርበን እግዚአብሔርን እንለምነው

And all of us who ask and beseech in prayer, may He cover us with the spirit of peace, and give us grace, and enlighten the eyes of our hearts. Let us draw high and ask God to accept our prayers according to His will.

አውቀን በሀብቱ እናድግ ዘንድ በእርሱም ስም እንመካ ዘንድ በነቢያት በሐዋርያትም መሠረት ላይ እንታነጽ ዘንድ እንግዲህ በመንፈስ ቅዱስ እንነሣ ቀርበን አምላካችን እግዚአብሔርን እንለምነው ወዶ ጸሎታችንን ይቀበል ዘንድ

Let us therefore rise in the Holy Spirit, growing in His grace, with understanding, glorying in His name and built upon the foundation of the prophets and the apostles. Let us draw high and ask Lord God to accept our prayers according to His will.

ንስእለከ እግዚኦ ወስናስተበቍዕከ ከመ ትዘከራ ለቅድስት አሐቲ ቤተ ክርስቲያን ጉባኤ እንተ ሐዋርያት እንተ ሀለወት እምጽንፍ እስከ አጽናፈ ዓለም።

ሐዋርያት የሰበሰቡዋትን፤ ከዳርቻ እስከ ዓለም ዳርቻ ያለች አንዲት ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ታስባት ዘንድ አቤቱ እንለምንሃለን እንማልድሃለንም።

ይ.ዲ.

ጸልዩ በእንተ ሰላመ ቤተ ክርስቲያን
አሐቲ ቅድስት ጉባኤ እንተ ሐዋርያት
ርትዕት ኀበ እግዚአብሔር

ሐዋርያት ስለ ሰበሰቡዋት፤ በእግዚአብሔር
ዘንድ የቀናች ስለ ሆነች ስለ አንዲት ቤተ
ክርስቲያን ሰላም ጸልዩ።

ይ.ሕ.

አሜን ኪርያላይሶን እግዚኦ ተሣሃለነ።
አሜን ኪርያላይሶን አቤቱ ይቅር በለን።

ይ.ካ.

ተዘክሮ እግዚኦ ለአብ ክቡር ብፁዕ ወቅዱስ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት አባ --- ወብፁዕ ሊቀ ጳጳስነ አባ ---- ተዘከር እግዚኦ ጳጳሳተ ኤጲስ ቆጶሳተ ቀሳውስተ ወዲያቆናተ ርቱዓነ ሃይማኖት፡፡ ኦ እግዚኦ አዕርፍ ነፍሰ አቡነ ---- ወአኅድሮ በውስተ መንግሥተ ሰማያት ምስለ ጻድቃን ፡፡ ወአንብር ለነ ዲበ መንበሩ ህየንቴሁ ኖላዌ፤ ኄረ ኢንኩን ከመ መርዔት ዘአልቦ ኖላዊ ወኢይምሥጠነ ተኵላ ወሣጢ፡፡ ወኢይጽዐሉነ ሕዝብ ነኪራን እለ ዉፁኣን እምኔነ፡፡

አቤቱ ክቡር ብፁዕ ቅዱስም ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳችንን አባ ---- ብፁዕ ወክቡር ሊቀ ጳጳሳችን አባ ---- አስበው አቤቱ ሃይማኖታቸው የቀና ጳጳሳቱን ኤጲስ ቆጶሳቱን ቀሳውስቱን ዲያቆናቱንም አስብ፡፡ አቤቱ ያባታችንን ----- ነፍስ አሳርፍ ከጻድቃንም ጋራ በመንግሥተ ሰማያት አሳድረው፡፡ ጠባቂ እንደድሌለው መንጋ እንዳንሆን ነጣቂ ተኵላም እንዳይነጥቀን ከእኛ የተለዩና የወጡ ወገኖችም እንዳይነቅፉን በመንበሩ ላይ በርሱ ፈንታ ቸር ጠባቂ አኑርልን፡

ይ.ዲ.

ጸልዩ በእንተ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ---- ወብፁዕ ሊቀ ጳጳስነ ---- ወኵሎሙ ጳጳሳት ኤጲስ ቆጶሳት ቀሳውስት ወዲያቆናት ወኵሎሙ ሕዝበ ክርስቲያን ርቱዓነ ሃይማኖት፡

ስለ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳችን ስለ -----ስለ ብፁዕ ሊቀ ጳጳሳችን ስለ ----- ስለ ኤጲስ ቆጶሳቱም ሁሉ ስለ ቀሳውስትና ስለ ----- ዲያቆናትም፤ ሃይማኖታቸው ስለ ቀና ስለ ክርስቲያን ወገኖችም ሁሉ ጸልዩ፡፡

ይ.ካ.

ተዘከር እግዚኦ አበዊነ ወአኀዊነ ወአኃቲነ እለ ኖሙ ወአዕረፉ በርትዕት ሃይማኖት፡፡ተዘከር እግዚኦ ማኅበረነ፡፡ ባርኮሙ ወጸግዎሙ ከመ ይኩኑ ለከ ዘእንበለ ክልዓት ወኢጽርዓት ይግበሩ ፈቃደከ ቅድስተ ወብፅዕተ፡፡ ወረስዮሙ ቤተ ጸሎት ወቤተ ንጹሕ ወቤተ በረከት፡፡ ጸግወነ እግዚኦ ለነ ለአግብርቲከ ውለእለ ይመጽኡ እምድኅረነ ወእስከ ለዓለም መዋዕለ ጸጉ፡፡

አቤቱ በቀናች ሃይማኖት ሁነው የሞቱትንና ያረፉትን አባቶቻችንና ወንድሞቻችንን እኆቻችንንም አስብ፡፡ አቤቱ አንድነታችንን አስብ፡፡ ባርካቸው ያለመከላከል ያለማቋረጥም ላንተ ይሆኑ ዘንድ ንኸድት ክብርት ፈቃድህንም ይሠሩ ዘንድ ስጣቸው፡፡ የጸሎት ቤትና የንጽሕና ቤት የበረከትም ቤት አድርጋቸው፡፡ አቤቱ ለኛ ለባሮችህ ይህን ስጠን ከኛም በኋላ ለሚመጡ እስከ ዘለዓለምም ዘመንን ስጥ፡፡

ይ.ዲ.

ጸልዩ በእንተ ማኅበርነ ወዕቅበተ ለኵልነ፡፡

ስለ አንድነታችን ለሁላችንም መጠበቅን ለምኑ፡፡

ይ.ካ.

ተንሥእ እግዚኦ አምላኪ.ያ ወይዘረው ፀርከ፡፡ ወይጉየዩ ኵሎሙ እምቅድመ ገጽከ እለ ይጸልዑ ቅዱሰ ወቡሩከ ስመከ፡፡ ወሕዝብከሰ ይኲኑ ቡሩካነ በበረከተ ፻ አእላፋት ወትእልፊተ አእላፋት እለ ይገብሩ ፈቃድከ በኵሉ ጊዜ፡፡ በ1 ወልድከ ዘቦቱ ለከ ምስሌሁ ወምስለ ቅዱስ መንፈስ ስብሐት ወእኂዝ ይእዜኒ ወዘልፈኒ ወለዓለመ ዓለም አሜን፡፡

አቤቱ አምላኬ ተነሥ ጠላቶችህም ይበተኑ፡፡ ክቡር ምስጉን ስምህን የሚጠሉ ሰዎች ሁሉም ከፊትህ ይሽሹ፡፡ ወገኖችህ ግን ሁልግዜ ፈቃድህን በሚሠሩ በመላእክት በረከት የተባረኩ ይሁኑ፡፡ በአንድ ልጅህ ከርሱ ያለ ክብር ጽንዕ ላንተ ይገባል ከርሱ ጋራ ከመንፈስ ቅዱስም ጋራ ዛሬም ዘወትርም ለዘላለሙ አሜን፡፡

## ዲያቆን

ተንሥኡ ለጸሎት
ለጸሎት ተነሡ
Stand up for prayer.

## ሕዝብ

እግዚኦ ተሣሃለነ
አቤቱ ይቅር በለን
Lord have mercy upon us.

ካህን

ሰላም ለኵልክሙ

ሰላም ለሁላችሁ ይሁን

Peace be unto you all.

ሕዝብ

ምስለ መንፈስከ

ከመንፈስህ ጋር

And with thy spirit.

## ካህን

**ንስግድ (፫ ጊዜ)**

**እንስገድ (3 ጊዜ)**

Let's worship (to be repeated thrice)

## ሕዝብ

**ስአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ**

**እንዘ ሠለስቱ አሐዱ (፫ ጊዜ)**

**ሦስት ሲሆኑ አንድ ለሚሆኑ ለአብና ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስም (3 ጊዜ)**

The Father and the Son and the Holy Spirit, three in one. (to be repeated thrice)

## ካህን

ሰላም ለኪ

ሰላምታ ይገባሻል

Peace be unto thee:

## ሕዝብ

ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ማኅደረ መለኮት

የመለኮት ማደሪያ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን

Holy church, dwelling-place of the Godhead.

ካህን

ሰአሊ ለነ

ለምኝልን

Ask for us:

ሕዝብ

ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ

አምላክን የወለድሽ ድንግል ማርያም

Virgin Mary, mother of God

ካህን

አንቲ ውእቱ

አንቺ ነሽ

Thou art

## ሕዝብ

**ማእጠንተ ዘወርቅ አንተ ፀርኪ ፍሕመ እሳት ቡሩክ ዘነሰኣ እመቅደስ**

**ብሩክ ከቤተ መቅደስ የተቀበላት የእሳትን ፍህም የተሸከምሽ የወርቅ ጥና አንቺ ነሽ**

The golden censer which didst bear the coal of fire which the blessed took from the sanctuary

ዘይሠሪ ኃጢአተ ወይደመስስ ጌጋየ
ዝውእቱ ዘእግዚአብሔር ቃል ዘተሰብአ
እምኔኪ ዘአዕረገ ለአቡሁ ርእሶ ዕጣነ
ወመስዋዕተ ስሙረ

ኃጢአትን የሚያስተሠርይ በደልንም
የሚያጠፋ ይኸውም ካንቺ ሰው የሆነ
የእግዚአብሔር ቃል ነው ።

and which forgiveth sin and blotteth out error, who is God's Word that was made man from thee, who offered Himself to his Father for incense and an acceptable sacrifice.

ንሰግድ ለከ ክርስቶስ ምስለ አቡከ ኄር
ሰማያዊ ወመንፈስከ ቅዱስ ማሕየዊ
እስመ መጻእከ ወአድኀንከነ
ክርስቶስ ሆይ ቸር ከሚሆን ከሰማያዊ
አባትህ ጋራ መድኃኒት ከሚሆን
ከመንፈስ ቅዱስም ጋራ እንሰግድልሃለን
መጥተህ አድኸናልና
We worship Thee, Christ, with thy good
heavenly Father and thy Holy Spirit, the
life-giver, for Thou didst come and save us.

## ዲያቆን

ተንሥኡ ለጸሎት
ለጸሎት ተነሱ
Stand up for prayer.

## ሕዝብ

እግዚኦ ተሣሃለነ
አቤቱ ይቅር በለን
Lord have mercy upon us.

## ካህን

ሰላም ለኩልክሙ
ሰላም ለሁላችሁ ይሁን
Peace be unto you all.

## ሕዝብ

ምስለ መንፈስከ
ከመንፈስህ ጋር
And with thy spirit.

(በመቀባበል ይደገማል)

ካህን

ስብሐት ወክብር ለሥሉስ ቅዱስ ይደሉ

ዲ/ሕ

ይደልዎሙ ለአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ

ካህን

አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ኵሎ ጊዜ ይእዜኒ ወዘልፈኒ ወለዓለመ ዓለም

ሕዝብ

አሜን

ልዩ ሦስት ለሚሆን ለአብና ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስም ሁልጊዜ ክብር ምስጋና ይገባቸዋል ዛሬም ዘወትርም ለዘላለሙ አሜን

Glory and honor are meet to he Holy Trinity, the Father and the Son and the Holy Spirit at all times. Both now and ever and world without end. Amen

# የሐዋርያው

# ቅዱስ ጳውሎስ መልእክት

## ፩ኛ ቆሮንቶስ ፭ ፥ ፫ - ፍጻሜ

## Reading the Epistle of St. Paul

## 1st Choronthians - 5 : 3 -END

ዲያቆን

ቅድስት በምትሆን በጽርሐ ጽዮን በሐዋርያት ሳይ የወረደ የአብ በረከት የወልድም ፍቅር የመንፈስ ቅዱስም ሀብት በሁላችንም ይውረድ እጽፍ ድርብም ይሁን

Deacon

The blessing of the father and the love of the son and the gift of the holy spirit who came down upon the apostles in the upper room of Holy Zion, in like sort come down and be multiplied upon me and all of you.

## ሕዝብ

ቅዱስ ሐዋርያ ጳውሎስ ሠናየ መልእክት ፈዋሴ ዱያን ዘነሣእከ አክሊለ ሰአል ወጸሊ በእንቲአነ ያድኅን ነፍሳተነ በብዝኃ ሣህሉ ወምሕረቱ በእ ተስሙ ቅዱስ

አክሊልን የተቀበልህ ድውያንን የምታድን መልእክትህ የበጀ ቅዱስ ሐዋርያ ጳውሎስ ሆይ በይቅርታውና በቸርነቱ ብዛት ስለ ቅዱስም ስሙ ሰውነታችንን ያድን ዘንድ ስለእኛ ለምን ጸልይም

Holy Apostle Paul, good messenger, healer of the sick, who hast received the crown, ask and pray for us in order that he may save our souls in the multitude of his mercies and in his pity for his holy name's sake.

## ዲያቆን

ተንሥኡ ለጸሎት
ለጸሎት ተነሱ
Stand up for prayer.

## ሕዝብ

እግዚኦ ተሣሃለነ
አቤቱ ይቅር በለን
Lord have mercy upon us.

## ካህን

**ሰላም ለኩልክሙ**
**ሰላም ለሁላችሁ ይሁን**
Peace be unto you all.

## ሕዝብ

**ምስለ መንፈስከ**
**ከመንፈስህ ጋር**
And with thy spirit.

## ካህን

ኦ አምላክ ዘለዓለም ቀዳሚ ወደኃሪ ዘአ ልብከ ጥንት ወኢተፍጻሜት ዘዐቢይ በተኪንዎቱ ወኃይል በምግባሩ ወጠቢብ በምክሩ ወጽኑዕ በኃይሉ ዘህልው ውስተ ኵሉ፡፡ ንስእለከ ወናስተበቍዕከ ከመ ተህሉ ምስሌነ በዛቲ ሰዓት አርኢ ገጸከ ላዕሌነ ወንበር ምስሌነ ማእከሌነ፡፡

የዘላለም አምላክ ሆይ ቀዳማዊ ደኃራዊ የምትሆን ጥንትም ፍጻሜም የሌለህ በመፍጠሩ ገናና የሚሆን በስራውም ኃያል የሚሆን በሁሉ አድሮ የሚኖር በዚች ሰአት ከኛ ጋራ ትኖር ዘንድ እንለምንሃለን እንማልድሃለንም ለኛ ፊትህን ግለጽልን ከኛም ጋራ በመካከላችን ኑር

ወአንጽሕ አልባበነ ወቀድስ ነፍስተነ ወሥረይ ኃጢአተነ ዘገበርነ በፈቃድነ ዘእንበለ ፈቃደከ ወረስየነ እግዚኦ ናቅርብ ኀቤከ መሥዋዕተ ንጹሐ ቊርባነ ነባቤ ወዕጣነ መንፈሳዌ ይባእ ውስተ ጽርሐ ቅዱስ ቅዱሳቲከ በዋሕድ ወልድከ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘምስለ መንፈስ ቅዱስ።

ልቡናችንንም አንጻ ሰውነታችንንም አክብር ያለፈቃድህ በፈቃዳችን የሰራነውንም ኃጢአታችንን አስተስርይ ንጹሑን መስዋእት ነባቢውን ቁርባንና መንፈሳዊውን እጣን አቤቱ ወዳንተ እንድናቀርብ አድርገን ወደ ልዩ ምስጋናህ አዳራሽ ይገባ ዘንድ በአንድ ልጅህ በጌታችን በእየሱስ ክርስቶስ ከመን ፈስ ቅዱስ ጋራ

የዕለቱ መልእክት ከጴጥሮስ ከዮሐንስ ከያዕቆብ ከይሁዳ ወይም ከዮሐንስ ራእይ ይነበባል

# ፪ኛ ዮሐንስ ምዕራፍ ፩ ፤ ፬ - ፍፃሜ

The daily verses reading from the Epistle of Peter, John, Jacob, Judah, or Revelation of John

# 2nd Jons Chapter 1 : 4 - END

ወንድሞቼ ይህን ዓለም አትውደዱት በዓለሙ ውስጥ ያለውንም። ዓለሙም አላፊ ነው ፈቃዱም አላፊ ነው ሁሉም አላፊ ነውና

O my bretheren, love not the world neither the things that are in the world. The world passeth away and the lust thereof, for all is passing

## ሕዝብ

ቅዱስ ሥሉስ ዘኅቡር ህላዌከ እቀብ ማኅበረነ በእንተ ቅዱሳን ኅሩያን አርዳኢከ ናዝዘነ በሳህልከ በእንተ ቅዱስ ስምከ

ባህርይህ አንድ የሚሆን ልዩ ሦስት ሆይ አን ድነታችንን ጠብቅ ስለ ተመረጡ ክቡራን ደቀ መዛሙርትህ በይቅርታህ አጽናን ክቡር ስለሚሆን ስለ ስምህ ብለህ።

Holy con substantial Trinity, preserve our congregation for Thy holy elect disciples' sake: comfort us in Thy mercy, for Thy holy name's sake.

ዲያቆን

ተንሥኡ ለጸሎት

ለጸሎት ተነሱ

Stand up for prayer.

ሕዝብ

እግዚኦ ተሣሃለነ

አቤቱ ይቅር በለን

Lord have mercy upon us.

## ካህን

ሰላም ለኵልክሙ
ሰላም ለሁላችሁ ይሁን
Peace be unto you all.

## ሕዝብ

ምስለ መንፈስከ
ከመንፈስህ ጋር
And with Thy spirit.

## ካህን

እግዚእነ ወአምላክነ አንተ ውእቱ ለሐዋርያቲከ ቅዱሳን ከሠትከ ሎሙ ምሥጢረ ስብሐተ ወንጌለ መሢሕከ ወወሀብኮሙ ዐቢየ ሀብተ እንተ አልባቲ ኍልቍ እንተ ይእቲ እምጸጋከ ወፈነውኮሙ ይስብኩ ውስተ ኵሉ አጽናፈ ዓለም ብዕለ ጸጋከ ዘኢይትዐወቅ ምሕረትከ።

ጌታችን አምላካችን ሆይ የመሢሕን የወንጌል ክብር ምሥጢር ቅዱሳን ለሚሆኑ ለሐዋርያት የገለጽህላቸው አንተ ነህ። ከቸርነትህ የምትሆን ስፍር ቍጥር የሌላት ደገኛ ሀብትንም የሰጠሃቸው ይህቺውም ከቸርነትህ የተገኘች ናት። የማይታወቅ የቸርነትህን ብዛት በዓለሙ ሁሉ ዳርቻ ያስተምሩ ዘንድ የሰደድሃቸው።

# ካህን

ወንሕነኒ እግዚኦ ንስእለከ ወናስተበቍዕ ዐከ ከመ ትረስየነ ድልዋነ ለርስቶሙ ወለመክፈልቶሙ ንሑር በፍናዊሆሙ ወንትሉ በዐሠሮሙ ወጸግወነ በኵሉ ጊዜ ንትመሰል ኪያሆሙ ወንጽናዕ በፍቅሮሙ፡፡ ወንኩን ክፍለ ምስሌሆሙ በውስተ ፃማሆሙ በሠናይ አምልኮ፡፡

አቤቱ እኛም ለዕድላቸውና ለርስታቸው የበቃን ታደርገን ዘንድ እንለምንሃለን እንማልድሃለን፡፡ በመንገዳቸው እንሂድ ዘንድ፤ ፍለጋቸውንም እንከተል ዘንድ፤ ሁለግዜም እነሱን እንመስል ዘንድ መምሰሉን ስጠን በፍቅራቸውም እንጸና ዘንድ ባማረ አምልኮ በድካማቸው ከሳቸው ጋር የታደልን እንሆን ዘንድ መሆኑን ስጠን፡፡

## ካህን

ወዕቀባ ለቤተ ክርስቲያንከ ቅድስት እንተ ሣረርካ በእንቲአሆሙ፡፡ ወባርክ ላዕለ አባግዐ መርዔትከ ፡፡ ወአብዝኃ ለዛቲ ዐፀደ ወይን፡፡ እንተ ተከልካ በየማንከ ቅዱስ በኢየሱስ ክርስቶስ እግዚእነ ዘቦቱ ለከ ምስሌሁ ወምስለ ቅዱስ መንፈስ ስብሐት ወእኂዝ ይእዜኒ ወዘልፈኒ ወለዓለመ ዓለመ፤ አሜን፡፡

ስለነሱ የሠራሃትን ቤተ ክርስቲያንንም ጠብቃት፡ኛ የመንጋህንም በጎች ባርክ ጽኑ በሚሆን ቀኝህ የተከልካት ይህችንም የወይን ቀንድ ባርክ፡፡ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ከሱ ጋራ ከመንፈስ ቅዱስም ጋራ ምስጋና ጽንዕ ያለህ ዛሬም ዘወትርም ለዘላለሙ አሜን፡፡

## የሐዋርያት ሥራ ይነበባል

*Reading the Acts of the Apostles*

# የሐዋ. ሥራ ፲፱ ፥ ፲፯ - ፳፩

# Acts -19 : 17 - 21

የእግዚአብሔር ቃል ፈጽሞ መላ። ከፍ ከፍ አለ። በቅድስት ቤተ ክርስቲያንም በዝቶ ተጨመረ ምስጋና ገንዘቡ በሚሆን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ያመኑት ሕዝብም በዙ ለዘለዓለሙ አሜን።

Full the great and exalted is the word of God, and it hath increased in the holy church, and many are they that believe in out Lord Jesus Christ to whom be glory, world without end. Amen.

## ሕዝብ

ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ አንተ አምላክ
አብ አኃዜ ኩሉ

ሁሉን የያዝህ አብ ሆይ ቅዱስ
ቅዱስ ቅዱስ አንተ ነህ

Holy Holy Holy art Thou, only-
begotten Son

## ሕዝብ

ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ አንተ ወልድ ዋህድ ዘአንተ ቃለ አብ ሕያው

የሕያው አብ ቃል የምትሆን ወልድ ዋህድ ሆይ ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ አንተ ነህ

Holy Holy Holy art Thou, only-begotten Son, who art the Word of the living Father.

ሕዝብ

ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ አንተ መንፈስ ቅዱስ ዘተአምር ኵሎ

ሁሉን የምታውቅ መንፈስ ቅዱስ ሆይ ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ አንተ ነህ።

Holy Holy Holy art Thou, Holy Spirit who knowst all things.

ይ.ካ.

እግዚአብሔር አምላክነ ዘተወከፍከ መሥዋዕተ አቡነ አብርሃም፤ ወህየንተ ይስሐቅ ወልዱ ዘአስተዳሎከ ወአውረድከ ሎቱ ቤዛሁ በግዐ ከማሁ ተወከፍ እግዚኦ መሥዋዕተነ ወመዓዛ ዝንቱ ዕጣንነ ወፌኑ ለነ ህየንቴሁ እምላዕሉ ብዕለ ሣህልከ ምሕረትከ ከመ ንኩን ንጹሓነ እምኲሉ ጌና ፂዓተ ኃጣውኢነ፡፡

የአባታችንን የአብርሃምን መሥዋዕት የተቀበልህ አምላካችን እግዚአብሔር ስለ ልጁ ስለ ይስሐቅም ፈንታ ቤዛ ሊሆነው በጉን አዘጋጅተህ ያወረድህለት አቤቱ እንዲሁ መሥዋዕታችንና የዚህን የዕጣናችንን መዓዛ ተቀበል በርሱም ፈንታ የይቅርታህንና የቸርነትህን ብዛት ከላይ ላክልን ከክፉ ኃጢአታችን ሽታ ሁሉ ንጹሓን እንሆን ዘንድ፡፡

ይ.ካ.

ወረስየነ ድልዋነ ከመ ንትለአክ ቅድመ ውዳሴ ንጽሕከ ኦ መፍቀሬ ሰብእ በጽድቅ ወበንጽሕ በኵሉ መዋዕለ ሕይወትነ በትፍሥሕት ወበኀሤት ።

ሰውን የምትወድ ሆይ በንጽሕናህ ምስጋና ፊት እናገለግል ዘንድ የበቃን አድርገን።

በሕይወታችን ዘመን ሁሉ በእውነትና በንጽሕና በደስታና በኀሤት።

**ዲያቆን**

ተንሥኡ ለጸሎት

ለጸሎት ተነሱ

Stand up for prayer.

**ሕዝብ**

እግዚኦ ተሣሃለነ

አቤቱ ይቅር በለን

Lord have mercy upon us.

## ካህን

ሰላም ለኩልክሙ
ሰላም ለሁላችሁ ይሁን
Peace be unto you all.

## ሕዝብ

ምስለ መንፈስከ
ከመንፈስህ ጋር
And with thy spirit.

ንስእለከ እግዚኦ ወስናስተበቍዕከ ከመ ትዘከራ ለቅድስት አሐቲ ቤተ ክርስቲያን ጉባኤ እንተ ሐዋርያት እንተ ህለወት እምጽንፍ እስከ አጽናፈ ዓለም፡፡

ሐዋርያት የሰበሰቡዋትን፤ ከዳርቻ እስከ ዓለም ዳርቻ ያለች አንዲት ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ታስባት ዘንድ አቤቱ እንለምንሃለን እንማልድሃለንም፡፡

ይ.ዲ.

ጸልዩ በእንተ ሰላመ ቤተ ክርስቲያን
አሐቲ ቅድስት ጉባኤ እንተ ሐዋርያት
ርትዕት ኀበ እግዚአብሔር

ሐዋርያት ስለ ሰበሰቡዋት፤ በእግዚአብሔር
ዘንድ የቀናች ስለ ሆነች ስለ አንዲት ቤተ
ክርስቲያን ሰላም ጸልዩ።

ይ.ሕ.

አሜን ኪርያላይሶን እግዚኦ ተሣሃለነ።
አሜን ኪርያላይሶን አቤቱ ይቅር በለን።

ይ.ካ.

ተዘክሮ እግዚኦ ለአብ ክቡር ብፁዕ ወቅዱስ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት አባ --- ወብፁዕ ሊቀ ጳጳስነ አባ ---- ተዘከር እግዚኦ ጳጳሳተ ኤጲስ ቆጶሳተ ቀሳውስተ ወዲያቆናተ ርቱዓነ ሃይማኖት፡፡ ኦ እግዚኦ አዕርፍ ነፍሰ አቡነ ---- ወአኅድሮ በውስተ መንግሥተ ሰማያት ምስለ ጻድቃን ፡፡ ወአንብር ለነ ዲበ መንበሩ ህየንቴሁ ኖላዌ፤ ኄረ ኢንኩን ከመ መርዔት ዘአልቦ ኖላዊ ወኢይምሥጠነ ተኩላ ወሣጢ፡፡ ወኢይጽዐሉነ ሕዝብ ነኪራን እለ ዉፁኣን እምኔነ፡፡

አቤቱ ክቡር ብፁዕ ቅዱስም ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳችንን አባ ---- ብፁዕ ወክቡር ሊቀ ጳጳሳችን አባ ---- አስበው አቤቱ ሃይማኖታቸው የቀና ጳጳሳቱን ኤጲስ ቆጶሳቱን ቀሳውስቱን ዲያቆናቱንም አስብ፡፡ አቤቱ ያባታችንን ----- ነፍስ አሳርፍ ከጻድቃንም ጋራ በመንግሥተ ሰማያት አሳድረው፡፡ ጠባቂ እንደሌለው መንጋ እንዳንሆን ነጣቂ ተኲላም እንዳይነጥቀን ከእኛ የተለዩና የወጡ ወገኖችም እንዳይነቅፉን በመንበሩ ላይ በርሱ ፈንታ ቸር ጠባቂ አኑርልን፡

ይ.ዲ.

ጸልዩ በእንተ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ---- ወብፁዕ ሊቀ ጳጳስነ ---- ወኵሎሙ ጳጳሳት ኤጲስ ቆጶሳት ቀሳውስት ወዲያቆናት ወኵሎሙ ሕዝበ ክርስቲያን ርቱዓነ ሃይማኖት፡

ስለ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳችን ስለ -----ስለ ብፁዕ ሊቀ ጳጳሳችን ስለ ----- ስለ ኤጲስ ቆጶሳቱም ሁሉ ስለ ቀሳውስትና ስለ ዲያቆናትም፤ ሃይማኖታቸው ስለ ቀና ስለ ክርስቲያን ወገኖችም ሁሉ ጸልዩ፡፡

## ይ.ካ.

ተዘከር እግዚኦ አበዊነ ወአኀዊነ ወአኃቲነ እለ ሙ ወአዕረፉ በርትዕት ሃይማት፡፡ተዘከር እግዚኦ ማኅበረነ፡፡ ባርኮሙ ወጸግዎሙ  ከመ ይኩኑ ለከ ዘእበለ ክልዓት ወኢጽርዓት ይግበሩ ፈቃደከ ቅድስተ ወብፅዕተ፡፡ ወረስዩሙ ቤተ ጸሎት ወቤተ ጹሕ ወቤተ በረከት፡፡ ጸግወነ እግዚኦ ለነ ለአግብርቲከ ውለእለ ይመጽኡ እምድኅረነ ወእስከ ለዓለም መዋዕለ ጸጉ፡፡

አቤቱ በቀች ሃይማት ሁነው የሞቱት ያረፉት አባቶች ወድሞች እኃቶችም አስብ፡፡ አቤቱ አድነታች አስብ፡፡ ባርካቸው ያለመከላከል ያለማቋረጥም ላተ ይሆኑ ዘድ ዕድት ክብርት ፈቃድህም ይሠሩ ዘድ ስጣቸው፡፡ የጸሎት ቤት የጽሕ ቤት የበረከትም ቤት አድርጋቸው፡፡ አቤቱ ለኛ ለባሮችህ ይህ ስጠ ከኛም በኋላ ለሚመጡ እስከ ዘለዓለምም ዘመ ስጥ፡፡

ይ.ዲ.

ጸልዩ በእንተ ማኅበርነ ወዕቅበተ ለኵልነ፡፡

ስለ አንድነታችን ለሁላችንም መጠበቅን ለምኑ፡፡

ይ.ካ.

ተንሥእ እግዚኦ አምላኪ.ያ ወይዘረው ፀርከ፡፡ ወይጕየዩ ኵሎሙ እምቅድመ ገጽከ እለ ይጸልዑ ቅዱሰ ወቡሩከ ስመከ፡፡ ወሕዝብከሰ ይኩኑ ቡሩካነ በበረከተ ፻ አእላፋት ወትእልፊተ አእላፋት እለ ይገብሩ ፈቃድከ በኵሉ ጊዜ፡፡ በ1 ወልድከ ዘቦቱ ለከ ምስሌሁ ወምስለ ቅዱስ መንፈስ ስብሐት ወእኂዝ ይእዜኒ ወዘልፈኒ ወለዓለመ ዓለም አሜን፡፡

አቤቱ አምላኬ ተነሥ ጠላቶችህም ይበተኑ፡፡ ክቡር ምስጉን ስምህን የሚጠሉ ሰዎች ሁሉም ከፊትህ ይሽሹ፡፡ ወገኖችህ ግን ሁልግዜ ፈቃድህን በሚሠሩ በመላእክት በረከት የተባረኩ ይሁኑ፡፡ በአንድ ልጅህ ከርሱ ያለ ክብር ጽንዕ ላንተ ይገባል ከርሱ ጋራ ከመንፈስ ቅዱስም ጋራ ዛሬም ዘወትርም ለዘላለሙ አሜን፡፡

ካህን

ደኅንነትን የምንለምንሽ ክብርን የተሞላሽ ቅድስት ሆይ ደስ ይበልሽ

Rejoice, O thou of whom we ask healing, O holy full of honor.

ሕዝብ

ደስ ይበልሽ

Rejoice.

ካህን

ሁልጊዜ ድንግል የምትሆኚ አምላክን የወለድሽ የክርስቶስ እናት ሆይ ኃጢአታችንን ያስተሠርይልን ዘንድ ወደ ልጅሽ ወደ ወዳጅሽ ወደ ላይ ጸሎታችንን አሳርጊ

Ever-Virgin, parent of God, mother of Christ, offer up our prayer on high to thy beloved Son that He may forgive us our sin.

ሕዝብ

አሜን

Amen.

## ካህን

**በእውነት የፅድቅ ብርሃን የሚሆን አምላካችንን ክርስቶስን የወለድሽልን (ንጽሕት) ሆይ ደስ ይበልሽ**

Rejoice, O thou who didst bear for us the very light of righteousness, even Christ our God.

## ሕዝብ

**ደስ ይበልሽ**

Rejoice.

**ካህን**

ንጽሕት ድንግል ሆይ ለነፍሳችን ይቅርታን ያደርግ ዘንድ ኃጢአታችንንም ያስተሠርይልን ዘንድ ወደ ጌታችን ለምኝልን

O Virgin pure, plead for us unto our Lord that He may have mercy upon our souls and forgive us our sin.

**ሕዝብ**

አሜን

Amen.

**ካህን**

በእውነት ለሰው ወገን አማላጅ የምትሆኝ አምላክን የወለድሽ ንጽሕት ቅድስት ድንግል ማርያም ሆይ ደስ ይበልሽ

Rejoice, O Virgin Mary, parent of God, holy and pure, very pleader for the race of mankind.

**ሕዝብ**

ደስ ይበልሽ

Rejoice.

**ካህን**

**የኃጢአታችንን ሥርየት ይሰጠን ዘንድ በልጅሽ በክርስቶስ ፊት ለምኝልን**

Plead for us before Christ thy Son, that He may vouchsafe us remission of our sins.

**ሕዝብ**

**አሜን**

Amen.

ካህን

በእውነት ንግሥት የምትሆኝ ንጽሕት ድንግል ሆይ ደስ ይበልሽ

Rejoice, O Virgin pure, very Queen.

ሕዝብ

ደስ ይበልሽ

Rejoice.

ካህን

የባሕርያችን መመኪያ ሆይ ደስ ይበልሽ

Rejoice, O pride of our kind.

ሕዝብ

ደስ ይበልሽ

Rejoice.

ካህን

አምላካችን አማኑኤልን የወለድሽልን ሆይ ደስ ይበልሽ

Rejoice, O thou that barest for us Emmanuel our God.

ሕዝብ

ደስ ይበልሽ

Rejoice.

ካህን

በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ፊት እውነተኛ አስታራቂ ሆነሽ ታስቢን ዘንድ እንለምን ሻለን ለነፍሳችን ይቅርታን ያደርግልን ዘንድ ኃጢአታችንንም ያስተሠርይልን ዘንድ

We ask thee to remember us, O true Mediatrix, before our Lord Jesus Christ that He may have mercy upon our souls and forgive us our sins.

ሕዝብ

አሜን

Amen.

# ካህናት

ዝውእቱ ጊዜ ባርኮት ወዝ ውእቱ ጊዜ ዕጣን ኅሩይ ጊዜ ሰብሆቱ ለመድኃኒነ መፍቀሬ ሰብእ ክርስቶስ

የማመስገን ጊዜ ይህ ነው፥ የተመረጠ የዕጣን ጊዜም ይህ ነው፤ ሰውን ወዳጅ መድኃኒታችንን ክርስቶስን ማመስገኛ ጊዜ

This is the time of blessing; this is the time of chosen incense, the time of the praise of our Savior, lover of man, Christ.

# ሕዝብ

**ዕጣን ይእቲ ማርያም ዕጣን ውእቱ እስመ ዘውስተ ከርሳ ዘይትሜዓዝ እምኵሉ ዕጣን ዘወለደቶ መጽአ ወአድኅነነ**

**ማርያም ዕጣን ናት፤ ዕጣን እርሱ ነው በማኅፀንዋ ያደረው ከዕጣን ሁሉ የሚሸት ነውና የወለደችው መጥቶ አዳነን።**

Mary is the incense, and the incense is He, because he who was in her womb is more fragrant than all chosen incense. He whom she bare came and saved us.

# ካህናት

ዕፍረት ምዑዝ ኢየሱስ ክርስቶስ ንዑ ን ስግድ ሎቱ ወንዕቀብ ትእዛዛቲሁ ከመ ይሥረይ ለነ ኃጣውኢነ

ኢየሱስ ክርስቶስ መዓዛ ያለው ሽቱ ነው ኑ እንስገድለት ትእዛዞቹንም እንጠብቅ ኃጢአታችንን ያስተሠርይልን ዘንድ

The fragrant ointment is Jesus Chris. O come let us worship Him and keep His commandments that He may forgive us our sins.

# ሕዝብ

**ተውህቦ ምሕረት ለሚካኤል ወብሥራት ለገብርኤል ወሀብተ ሰማያት ለማርያም ድንግል**

**ለሚካኤል ምሕረት ተሰጠው ለገብርኤልም ማብሠርን ለድንግል ማርያምም ሰማያዊ ሀብት**

To Michael was given mercy, and glad tidings to Gabriel, and a heavenly gift to the Virgin Mary.

# ካህናት

**ተውህቦ ልቡና ለዳዊት ወጥበብ ለሰሎሞን ወቀርነ ቅብዕ ለሳሙኤል እስመ ውእቱ ዘይቀብዕ ነገሥተ**

**ለዳዊት ልቦና ለሰሎሞንም ጥበብ ለሳሙኤልም ነገሥታቱን የቀባ እርሱ ነውና የሽቱ ቀንድ ተሰጠው**

To David was given understanding, and wisdom to Solomon, and an horn of oil to Samuel for he was the anointer of kings.

# ሕዝብ

ተውህቦ መራኁት ለአቡነ ጴጥሮስ ወድንግልና ለዮሐንስ ወመልእክት ለአቡነ ጳውሎስ እስመ ውእቱ ብርሃና ለቤተ ክርስቲያን

ለአባታችን ለጴጥሮስ መክፈቻ ለዮሐንስም ድንግልና ለአባታችን ለጳውሎስም የቤተ ክርስቲያን ብርሃኗ እርሱ ነውና መልእክት ተሰጠው

To our father Peter were given the keys, and virginity to John, and apostleship to our father Paul, for he was the light of the church.

# ካህናት

**ዕፍረት ምእዝት ይእቲ ማርያም እስመ ዘውስተ ከርሣ ዘይትሌዐል እምኩሉ ዕጣን መጽአ ወተሠገወ እምኔሃ**

**መዓዛ ያሳት ሽቱ ማርያም ናት በማኅፀንዋ ያለው ከዕጣን ሁሉ የሚበልጥ ነውና መጥቶ ከእርስዋ ሰው ሆነ**

The fragrant ointment is Mary, for he that was in her womb, who is more fragrant than all incense, came and was incarnate of her.

# ሕዝብ

ለማርያም ድንግል ንጽሕት ሰምራ አብ ወአሠርገዋ ደብተራ ለማኅደረ ፍቁር ወልዱ

ንጽሕት ድንግል ማርያምን አብ ወደዳት ለተወደደ ልጁ ማደሪያ ልትሆነው አስጌጣት

In Mary virgin pure the Father was well-pleased, and he decked her to be a tabernacle for the habitation of his beloved Son.

# ካህናት

ተውህቦ ሕግ ለሙሴ ወክህነት ለአሮን ተውህቦ ዕጣን ኅሩይ ለዘካርያስ ካህን

ለሙሴ ሕግ ለአሮን ክህነት ተሰጠው ለካህኑ ለዘካርያስም የተመረጠ ዕጣን ተሰጠው

To Moses was given the law, and priesthood to Aaron. To Zacharias the priest was given chosen incense.

## ሕዝብ

ደብተራ ስምዐ ገብርዋ በከመ ነገረ እግዚእ ወአሮን ካህን በማእከላ የዐርግ ዕጣን ኅሩየ

የምስክር ድንኳን አደረጓት ጌታ እንደተናገረ ካህኑ አሮንም በመካከሏ የተመረጠ ዕጣን ያሳርጋል

They made a tabernacle of testimony according to the word of God; and Aaron the priest, in the midst thereof, made the chosen incense to go up.

ካህናት

ሱራፌል ይሰግዱ ሎቱ ወኪሩቤል
ይሴብሕዎ ይጸርሑ እንዘ ይብሉ
ሱራፌል ይሰግዱለታል ኪሩቤልም
ያመሰግኑታል። እንዲህ እያሉ
ይዘምራሉ።

The seraphim worship him, and
cherubim praise him and cry saying:

## ሕዝብ

ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር በኀበ አእላፍ ወክቡር በውስተ ረበዋት ።

እግዚአብሔር በአእላፍ መላእክት ዘንድ ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ ነው ። በአለቆችም ዘንድ ክቡር ነው ።

Holy Holy Holy is the Lord among the thousands and honored among the tens of thousands.

አንተ ውእቱ ዕጣን ኦ መድኃኒነ እስመ
መጻእከ ወአድኃንከነ ተሣሀለነ።
መድኃኒታችን ሆይ! ዕጣን አንተ ነህ፤
መጥተህ አድነኸናልና። ይቅር በለን።
Thou art the incense, O our savior, for Thou didst come and save us. Have mercy upon us.

## ከትንሳኤ እስከ በአለ ሐምሳ (በመቀባበል ይደገማል)

ክርስቶስ ተንሥአ እሙታን ሞተ ወኬዶ ለሞት ለእለ ውስተ መቃብር ወሀበ ሕይወተ ዘለዓለም ዕረፍተ

ክርስቶስ ከሙታን ተለይቶ ተነሳ ሞትን በሞቱ  አጠፋው በመቃብር ላሉ ሁሉ የዘለዓለም ዕረፍት የሚሆን ሕይወትን ሰጠ

Christ rose from the dead. He died and trampled death  under foot. He gave the life of eternal rest to those who were in the grave. (3 times)

ካህን

ቅዱስ

ሕዝብ

እግዚአብሔር ቅዱስ ኃያል ቅዱስ ሕያው ዘኢይመውት ዘተወልደ እማርያም እምቅድስት ድንግል ተሣሃለነ እግዚኦ።

እግዚአብሔር ልዩ ኃያል ልዩ ሕያው የማይሞት ከቅድስት ድንግል ማርያም የተወለደ፥ አቤቱ ይቅር በለን

God, holy Mighty, holy Living, Immortal, who was born from the holy Virgin Mary, have mercy upon us, Lord.

ቅዱስ እግዚአብሔር ቅዱስ ኃያል ቅዱስ ሕያው ዘኢይመውት ዘተጠምቀ በዮርዳኖስ ወተሰቅለ ዲበ ዕፀ መስቀል ተሣሃለነ እግዚኦ።

ልዩ እግዚአብሔር ልዩ ኃያል ልዩ ሕያው የማይሞት በዮርዳኖስ የተጠመቀ በመስቀል ላይ የተሰቀለ፥ አቤቱ ይቅር በለን

Holy God, holy Mighty, Holy Living, Immortal, who was baptized in Jordan and crucified on the tree of the cross, have mercy upon us, Lord.

ቅዱስ እግዚአብሔር ቅዱስ ኃያል ቅዱስ ሕያው ዘኢይመውት ዘተንሥአ እሙታን አመ ሣልስት

ልዩ እግዚአብሔር ልዩ ኃያል ልዩ ሕያው የማየሞት በሦስተኛው ቀን ከሙታን ተለይቶ የተነሳ

Holy God, holy Mighty, holy Living, Immortal, who didst rise from the dead on the third day,

ዕለት አርገ በስብሐት ውስተ ሰማያት ወነበረ በየማነ አቡሁ ዳግመ ይመጽእ በስብሐት ይኰንን ሕያዋነ ወሙታነ፤ ተሣሃለነ እግዚኦ።

በምስጋና ወደ ሰማይ ወጣ በአባቱም ቀኝ ተቀመጠ ዳግመኛም ይመጣል በሕያዋንና በሙታን ይፈርድ ዘንድ፥ አቤቱ ይቅር በለን

ascend into heaven in glory, sit at the right hand of thy Father and again wilt come in glory to judge the quick and the dead, have mercy upon us, Lord.

ስብሐት ለአብ ስብሐት ለወልድ ስብሐት ለመን
ፈስ ቅዱስ ይእዜኒ ወዘልፈኒ ወለዓለመ ዓለም
አሜን ወአሜን ለይኩን ለይኩን

ለአብ ምስጋና ይሁን ለወልድም ምስጋና ይሁን
ለመንፈስ ቅዱስ ምስጋና ይሁን ዛሬም ዘወትርም
ለዘለዓለሙ አሜን አሜን ይሁን ይሁን

Glory be to the Father, glory be to the Son, glory be to the Holy Spirit, both now and ever and world without end. Amen and Amen, so be it, so be it.

ቅዱስ ሥሉስ እግዚአብሔር ሕያው ተሣሃለነ

ልዩ ሦስት ሕያው እግዚአብሔር ሆይ ይቅር በለን

O Holy Trinity, living God have mercy upon us.

ካህን

ጸጋ ዘእግዚአብሔር የሃሉ ምስሌክሙ
የእግዚአብሔር ጸጋ ከናንተ ጋራ ይሁን
The grace of God be with you.

ሕዝብ

ምስለ መንፈስከ
ከመንፈስህ ጋር
And with Thy spirit

ካህን

ንሴብሖ ለአምላክነ

ፈጣሪያችንን እናመስግን

Let us glory our God.

ሕዝብ

ርቱዕ ይደሉ

እውነት ነው ይገባል

It is right, it is just.

ካህን

አጽንዑ ሕሊና ልብክሙ

የልባችሁን አሳብ አጽኑ

Strengthen the thought of your heart.

## ሕዝብ

ብነ ኀበ እግዚአብሔር አቡነ ዘበሰማያት
አቡነ ዘበሰማያት፤ አቡነ ዘበሰማያት፤
ኢታብአነ እግዚኦ ውስተ መንሱት።

ከእግዚአብሔር ዘንድ አለን ። አባታችን
ሆይ አባታችን ሆይ አባታችን ሆይ አቤቱ
ወደ ፈተና አታግባን

We lift them unto the Lord our God. Our Father who art in heaven, Our Father who art in heaven, Our Father who art in heaven, lead us not into temptation.

## ይ.ካ.

እግዚአብሔር አብ ወሀቤ ብርሃ ዘለኵሉ ኃይል፤ ወለኵሉ ነፍስ ሐዋጺ ብርሃ ዘእምቅድመ ዓለም ሐታሚ መራሔ ሕይወት ወበቋዔ ተድላ ዘኢይመውት፡፡

ብርሃ የሚሰጥ እግዚአብሔር አብ፡፡ ለሁሉ ኃይል የሚሆ፡፡ ነፍስ ሁሉ የሚጐበኝ ከቀድሞ ጀምሮ የነበረ ብርሃ፡፡ ዓለም የፈጠረ፤ ወደ ሕይወት የሚመራ የማያልፈው ተድላ የሚሰጥ ነው፡፡

O God the Father, giver of light, the power of all, visitor of all souls, light which was before, creator of the world, the leader of life and giver of immortal happiness:

ይ.ካ.

ዘአውፃእከነ እምዕቅፍተ ጽልመት፤ ወብርሃነ ዘኢይትረከብ ጸጎከነ፡፡

ከጨለማ መሰክል አውጥተህ የማይገኝ ብርሃ የሰጠኸ፤

Thou hast taken us out of the snares of darkness, and granted us the unsearchable light.

## ይ.ካ.

ዘእማዕሠር ለእለ የአምኑ ብከ ፈቲሐከ በሃይማኖት ከለልከነ ፡፡ ዘኢይርኅቅ እምአግብርቲሁ ወትረ ዘምስሌሆሙ ይሄሉ ኢይጸመም ለዘበፍርሃት ወበረዓድ ትስእሎ ነፍስ እምቅድመ ሕሊና ኵሎ የአምር ወእምቅድመ ሕሊና ይፈትን ፡፡

ያመንብህ እኛን ከማዕሠረ ክሕደት አውጥተህ በሃይማኖት ያከበርከን፡፡ ከአገልጋዮቹ የማይርቅ የማይለይ፤ ዘወትር ከነርሱ ጋራ የሚኖር፤ በፍርሃት በረዓድ የምትለምነውን ነፍስ ቸል የማይል፤ ከሕሊና አስቀድሞ ሁሉን የሚያውቅ፤ ከአሳብ አስቀድሞ የሚመረምር

Thou hast loosed us, we who believe in thee, and covered us with faith. Thou art not far from Thy servants but art always with them. Thou dost not neglect the soul which supplicates thee with fear and trembling. Thou knowest all before the thought, and examinest all before the thought. Through Thy will Thou suppliest our needs before we ask;

ወዘእንበለ ንስአሎ ይሁብ ፍትወተነ ዘእምፈቃዱ፤ ወይሰምዐነ እለ እንበለ ኑፋቄ ንጼውዖ፡፡ ዘኢይትነገር ብርሃን ንጉሠ ሠራዊተ ሰማያት ሰማዒ ስብሐተ ማኅሌት ዘሊቃነ መላእክት ዘዲቤሆሙ ያዐርፍ፡፡

ሳንለምነው የምንሻውን ዐውቆ የሚሰጠን ሳንጠራጠር የምንለምነውን የሚሰማን፤ የማይመረመር ብርሃን፡፡ በሰማያት ያሉ የመላእክት ንጉሥ አድሮባቸው የሚኖር ሊቃነ መላእክት ያቀረቡትን ምስጋና የሚቀበል፡፡

O Lord, we pray thee to hear us. Grant us the unceasing word in trust. We glorify thee, we thank thee, and we bless thee; O Lord, we, Thy servants, glorify thee because we depend upon thee.

ስምዐነ ንስእለከ እግዚኦ፡፡ ሀበነ በትውክልት ቃለ ዘኢያረምም፡፡ ኪያከ ንሰብሕ ኪያከ ናእኵተ ወኪያከ ንባርክ፤ ወከመ ብከ ንፀወን ንሕነ አግብርቲከ ንሴብሐከ እግዚኦ፡፡

አቤቱ የምንለምንህን ስማን፤ አርምሞ የሌለበትን ቃል በሃይማኖት ስጠን፤ አንተን ፈጽሞ እናመሰግን ዘንድ አንተን እናከብር ዘንድ፤ በአንተም ጸንተን እንኖር ዘንድ፤ አቤቱ እኛ አገልጋዮችህ እናመሰግንሃለን፡፡

O Lord, we pray thee to hear us. Grant us the unceasing word in trust. We glorify thee, we thank thee, and we bless thee; O Lord, we, Thy servants, glorify thee because we depend upon thee.

ይ.ሕ.

ኪያከ ንሴብሕ እግዚኦ፡፡

አቤቱ አንተን እናመሰግናለን፡፡

O Lord, we glorify thee.

ይ.ካ.

እግዚኦ ኢየሱስ ክርስቶስ ሰምዐነ ቅዱስ፡፡ ለበሐማን ኮኖሙ ቃለ ለስቡራን ምርጕዘ ወለዕውራን ብርሃነ ወለሐንካሳን ፍኖተ ወለዘለምጽ መንጽሒ፡፡ እኁዛተ ሕማማት እግዚእ ፈወስከ ለጽሙማን መፈውስ፡፡

አቤቱ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ቀኍርጥ ልመናችንን ስማን፡፡ ድዳ ለነበሩት ቃል ለተሰበሩት ምርጕዝ፤ ለዕውራን ብርሃን፤ ለሐንካሶች መሂጃ፤ ለምጻሙን የሚያነጻ ሆናቸው፡፡ በደዌ የተያዙትን አቤቱ አዳንህ ደንቆሮችን ፈወስህ፡፡

O Lord, Jesus Christ, holy, Thou hast heard us. Thou didst become a word to the dumb, a staff to the broken ones, light to the blind, a way to the lame, and the purifier of the lepers. O Lord, Thou didst heal the sick and cure the deaf.

ይ.ካ.

ለሞት ዘለፎ ወለጽልመት ሣቀዮ፡፡ ዘገብረ ብርሃነ፤ ፀሓይ ዘኢየዐርብ ወማኅቶት ዘኢይጠፍእ፡፡

ሞትን ዘለፈው፡፡ ጨለማንም ሣቀየው፤ ብርሃንን የፈጠረ ኅልፈት የሌለበት፡፡ ፀሓይ የማይጠፋ ፋኖስ፤

Thou didst rebuke death and destroy the darkness. Thou didst create the light of the sun which does not set, the unquenchable light,

ይ.ካ.

ፀሓይ ዘዘልፈ ያበርህ ዲበ ቅዱሳን ወኲሎ ተከለ ለሠርጐ ዓለም በሥምረት እቁም፡፡ ገሃደ ለኲሉ ሠረቀ ለሰብእ መድኃኒት መያጢሃ ለነፍስ ወኲሎ በዘይደሉ አቅደምከ ሐልዮ፡፡

በቅዱሳን ላይ ዘወትር የሚያበራ ፀሓይ፤ በተወሰነ በቍርጥ ፈቃድ ለዓለም ጌጥ ሁሉን የፈጠረ፡፡ ሰውን ለማዳን ለሁሉ ተገለጽህ፤ ነፍስን የመለስሃት አንተ ነህ፡፡

The Sun which always shineth over the holy ones, Thou didst establish all through Thy fixed will for the decoration of the world. Thou didst appear clearly to all to save man, Thou art the restorer of the soul,

ይ.ካ.

ገባሬ መላእክት አበ ኵሉ ሠርጐ ዓለም ሣራሪሃ ለምድር፡፡

ሁሉን እንደሚገባ ማሰብን አስቀደምህ፡፡ መላእክትን የፈጠርህ፤ የሁሉ አባት፤ የሁሉ ጌታ የዓለም ጌጥ፤ ምድርን የፈጠርሃት፡፡

and Thou wert beforehand in determining all things rightly. O Thou, Creator of angels, Father of all, the adornment of the world and the maker of earth,

ጥበብ ወአእምሮ እምአብ ዘሀሎ እምቅድም ውስተ ዓለም ተፈነወ ዝ ህሉና ዘኢይትነሣት ወዘኢይተረጐም መንፈስ ዘኢያስተርኢ። ዜናዊ ስቡሕ አንተ ወመንክር ስምከ ወበእንተ ዝንቱ ንሕነ አግብርቲከ ንዌድሰከ እግዚኦ።

ዓለም ሳይፈጠር የነበረ ጥበብና ዕውቀት ከአብ ወደዚህ ዓለም ተላከ። ይህ አኗዋር የማይለወጥ የማይፈርስ፤ የማይመረመር ነው የማይታይ መንፈስ ነው። ይህን የተናገርህ አንተ ምስጉን ነህ፤ ምስክርነትህም የተደነቀ ነው። ስለዚህ እኛ አገልጋዮችህ እናመሰግንሃለን።

Wisdom and Knowledge I were sent to the world by the Father who was before. This existence is unchangeable and unsearchable and invisible Spirit. Thou art the glorious announcer and Thy name is wonderful. For this reason we, Thy servants, praise thee, O Lord.

ይ.ሕ.

ኪያከ ንዌድስ እግዚኦ፡፡

አቤቱ አንተን እናመሰግንሃለን፡፡

O Lord, we praise thee.

ይ.ካ.

ንሤልስ ለከ ዘንተ ቅዱሰ ስብሐተ ዘወሀብከነ ዚአከ ሃይማኖተ ዘኢይትነሠት ወቦቱ ገበርከ ለነ ንማዕ ማዕሠሪሁ ለሞት፡፡

የማይለወጥ ባንተ ማመንን የሰጠኸን አቤቱ ይህን ክቡር ምስጋና ሦስተኛ ጊዜ እናቀርብልሃለን፡፡ የሞት ማሠርያ ክሕደትን በሃይማኖት ድል እንድንነሣው ያደረግህል

Thrice over do we offer this holy glory to thee, who hast given us Thy unchangeable faith with which Thou hast made us break the bonds of death.

ይ.ካ.

ዘፈጠርከ ሕሊናተ ርቱዓተ ለእለ የአምኑ ብከ ከመ እምሰብእ ይኩኑ አማልክተ ዘወሀብከነ በመንፈስ ንኪድ ኵሎ ኀይሎ ለጸላኢ ከመ ንፍታሕ ዘኢይትፈታሕ ፍቅረ ለነ ኀበ አቡከ ገብርከ ወዐረቀ ማእከሌነ።

ለሚያምኑብህ ቅን ልቡናን የፈጠርህ፤ ከሰው ወገን አማልክት ይባሉ ዘንድ በመንፈስ የጠላትን ኃይል ሁሉ እንረግጥ ዘንድ የሰጠኸን የማይፈታውን እንፈታ ዘንድ ከአባትህ ዘንድ ፍቅርን አደረግህልን በመካከላችንም ሆነህ አስታረቅኸን።

Thou didst create the up right minds of those who believe in thee that they may be called gods among men. Thou hast granted us to tread down all the powers of the .enemy through the Spirit, so that we may loosen that which cannot be loosened. Thou hast made effectual for us love towards Thy Father and made reconciliation between us and him.

ስማዕ እግዚኦ እለ ኪያከ ይስእሉ፡፡ እግዚኦ እለ ንስእለከ ኢንስተት አላ በስክየት ዲበ ጸላኢነ ነህሉ፡፡ ሀበነ ዘወትር ጸሎተነ እምኒጠተ ጸላኢ ንትዐቀብ፡፡

አቤቱ የሚለምኑህን ስማቸው አቤቱ የምንለምንህ እኛ አንከሰስ በመከሰስ ጊዜ በጠላታችን ላይ እንኑርበት እንጂ፡፡ ዘወትር እንድንጸልይ አድርገን ከጠላታችን ማታለል እንጠበቅ ዘንድ ፡፡

O Lord, hear those who supplicate thee. O Lord, let not us, who supplicate thee, fall into sin, but vindicate us against our enemies, our accusers. Grant us continuous prayer that we may be kept from being swallowed up by the enemy.

ስማዕ ዘዓለም ንጉሥ መዓስበ ናዝዝ እጓለ ማውታ ተወከፍ ሲሩያነ በምሕረትከ አንጽሕ አብዳነ አጥበብ ወኅጉላነ ሚጥ እለ ውስተ ሞቅሕ አድኅን ወለኵልነ ኩን ፀወነ እስመ ለከ እግዚኦ አምላክነ መንግሥት ቡሩክ።

የዘለዓለም ንጉሥ ሆይ ስማ ባልቴቲቱን አረጋጋት አባት እናት የሞቱበትን ልጅ ተቀበል። የታለሉትን በቸርነትህ አንጻ ሰነፎችን አስብ አዋቂ አድርጋቸው የጠፉትን መልስ በግዞት ያሉትን አድናቸው ለሁላችንም መጸጊያ ሁነን። አቤቱ አምላካችን ክቡር መንግሥት ያንተ ነውና።

O eternal King, hear; comfort the widows, accept the orphans, purify the unclean through Thy mercy, grant wisdom to the foolish, restore the lost, save the prisoners, and be a refuge to all of us, for Thine is the blessed kingdom, O Lord our God.



**ይ.ሕ.** አሜ። Amen.

## ሕዝብ

አባታችን ሆይ በሰማያት የምትኖር ስምህ ይቀደስ መንግስትህ ትምጣ ፈቃድህ በሰማይ እንደሆነች እንድሁ በምድር ትሁን የእለት እንጀራችንን ስጠን ዛሬ በደላችንንም ሁሉ ይቅር በለን እኛም የበደሉንን ይቅር እንደምንል አቤቱ ወደ ፈተና አታግባን ከክፉ ሁሉ አድነን እንጂ መንግስት ያንተ ናትና ሀይል ክብር ምስጋና ለዘላለሙ አሜን።

Our father who art in heaven, hallowed be thy name, Thy Kingdom come, Thy will be done on earth as it is in heaven; Give us this ay our trespasses as we forgive them that trespass against us, and lead us not into temptation but deliver us and rescue us from all evil; for Thine is the kingdom, the power and the glory for ever and ever. Amen

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ሆይ በመልአኩ
በቅዱስ ገብርኤል ሰላምታ ሰላም እንልሻለን በሀሳብሽ
ድንግል ነሽ በስጋሽም ድንግል ነሽ የአሸናፊ
የእግዚአብሔር እናት ሆይ ሰላምታ ለአንቺ ይገባሻል
ከሴቶች ሁሉ ተለይተሽ አንቺ የተባረክሽ ነሽ የማህጸንሽም
ፍሬ የተባረከ ነው ጸጋን የተመላሽ ድንግል ሆይ ደስ
ይበልሽ እግዚአብሔር ከአንቺ ጋር ነውና ከተወደደው
ልጅሽ ከጌታችን ከመድኀኒታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ዘንድ
ይቅርታንና ምህረትን ለምኝልን ሀጢአታችንን
ያስተስርይልን ዘንድ ለዘላለሙ አሜን።

O Our Lady, Virgin St. Mary! In St. Gabriel’s greetings, Peace beunto you. Holy and pure, O mother of the almighty God! Peace be unto you. Blessed are thou amongst women and blessed is the fruit of thy womb. Hail Mary, full of Grace, the Lord is with Thee. Pray for us before our Lord Jesus Christ that he may forgive us our sins. Amen

# ሕዝብ

ኦ ሥሉስ ቅዱስ መሐረነ
ኦ ሥሉስ ቅዱስ መሐከነ
ኦ ሥሉስ ቅዱስ ተሣሃለነ

ልዩ ሦስት ሆይ ማረን
ልዩ ሦስት ሆይ ራራልን
ልዩ ሦስት ሆይ ይቅር በለን

O! Holy Trinity, Pity us, O! Holy Trinity, Spare us, O! Holy Trinity, have mercy upon us.

# ከትንሳኤ እስከ በአለ ሀምሳ
# (በመቀባበል ይደገማል)

ክርስቶስ ተንሥአ እሙታን
በአብይ ኃይል ወስልጣን
አሰሮ ለሰይጣን
አግአዞ ለአዳም
ሰላም
እም ይእዜሰ
ኮነ ፍስሀ ወሰላም

## ካህን

ተፈሥሒ ተፈሥሒ ተፈሥሒ
ኦ ማርያም ድንግል ምልዕተ ጸጋ፤

ጸጋን የተሞላሽ ድንግል ማርያም ሆይ ደስ ይበልሽ ደስ ይበልሽ ደስ ይበልሽ

Rejoice rejoice rejoice, O! Virgin Mary, full of grace

## ሕዝብ

እግዚአብሔር ምስሌኪ

እግዚአብሔር ካንቺ ጋራ ነው

The Lord is with Thee.

ካህን

ቡሩክት አንቲ እምአንስት

ከሴቶች ተለይተሽ የተባረክሽ ነሽ።

Blessed art Thou among women:

ሕዝብ

ወቡሩክ ፍሬ ከርሥኪ

የማኅፀንሽም ፍሬ የተባረከ ነው።

And blessed is the fruit of thy womb.

ካህን

ሰአሊ ለነ ኀበ ክርስቶስ ወልድኪ

ከልጅሽ ከክርስቶስ ዘንድ ለምኚልን።

Pray for us to Christ thy Son.

ሕዝብ

ከመ ይስረይ ለነ ታጣውኢነ

ታጢአታችንን ያስተሰርይልን ዘንድ።

To forgive us our sins.

## ካህን

ስብሐት ወክብር ለሥሉስ ቅዱስ ይደሉ
አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ኵሎ
ጊዜ ይእዜኒ ወዘልፈኒ ወለዓለመ ዓለም

ልዩ ሦስት ለሚሆን ለአብና ለወልድ
ለመንፈስ ቅዱስም ሁልጊዜ ክብር
ምስጋና ይገባቸዋል ዛሬም ዘወትርም
ለዘላለሙ አሜን።

Glory and honor are meet to the Holy Trinity, the Father and the Son and the Holy Spirit at all times, both now and ever and world without end. Amen

## ዲያቆን

ተንሥኡ ለጸሎት

ለጸሎት ተነሱ

Stand up for prayer.

## ሕዝብ

እግዚኦ ተሣሃለነ

አቤቱ ይቅር በለን

Lord have mercy upon us.

## ካህን

ሰላም ለኲልክሙ
ሰላም ለሁላችሁ ይሁን
Peace be unto you all.

## ሕዝብ

ምስለ መንፈስከ
ከመንፈስህ ጋር
And with Thy spirit.

## ጸሎተ ወንጌል/ Pray for the Holy Gospel

አቤቱ አምላካችን እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ! ቅዱሳን የሚሆኑ ደቀ መዛሙርትህንና ንጹሐን ሐዋርያትን እንዲህ ያልካቸው እናንተ የምታዩትን ያዩ ዘንድ ብዙ ነቢያት ጻድቃን ወደዱ፤ አላዩም። እናንተ ዛሬ የምትሰሙትንም ይሰሙ ዘንድ ወደዱ፤ አልሰሙም

Lord Jesus Christ, our God, who didst say to Thy holy disciples and Thy pure apostles: Many prophets and righteous men have desired to see the things which Ye see and have not seen them, and have desired to hear the things which Ye hear and have not heard them,

የእናንተ ያዩ ዓይኖቻችችሁና የሰሙ ጆሮቻችሁ ግን የተመሰገኑ ናቸው። እኛንም እንደ እነሱ የበቃን አድርገን፤ በቅዱሳን ጸሎት የከበረ የወንጌልን ቃል ሰምተን እንሠራ ዘንድ።

but You, blessed are Your eyes that have seen and you ears that have heard, Do Thou make us also like them meet to hear and to do the word of Thy Holy Gospel through the prayer of the saints.

## ዲያቆን

ጸልዩ በእንተ ወንጌል ቅዱስ

ክቡር ስለሚሆን ወንጌል ጸልዩ

Pray for the Holy Gospel

## ሕዝብ

ይረስየነ ድልዋነ ለሰሚዐ ወንጌል ቅዱስ

ወንጌልን ለመስማት የበቃን ያድርገን

May He make us meet to hear the Holy Gospel.

ካህን

ዳግመኛ አቤቱ ካንተ ዘንድ የምንሻውን በምንለምንበትና በምንጸልይበት ጊዜ እናስባቸው ዘንድ አስቡን ያሉንን ዳግመኛ አስብ

Remember again, Lord them that have bidden us to remember them at the time of our prayers and supplications where with we make request of Thee.

አቤቱ አምላካችን እግዚአብሔር ሆይ ከኛ አስቀድመው የሞቱትን አሳርፋቸው የታመሙትንም ፈጥነህ አድናቸው። የሁላችን ሕይወት የሁላችንም ተስፋ የሁላችንም አዳኝ የሁላችንም አስነሽ አንተ ነህና። ላንተ ምስጋና እስከ አርያም ድረስ እንልካለን።

O Lord our God, give rest to them that have fallen asleep before us, heal speedily them that are sick, for Thou art the life of us all, the hope of us all, the deliverer of us all and the raiser of us all, and to Thee we lift up thanksgiving unto the highest heaven, world without end.

የዕለቱን ምስባክ ህዝቡ ከዲያቆኑ ጋር እየተቀባበሉ በዜማ ያሰሙ

The Deacon shall sing from the Psalms a text which suits the day

- ቀተሉ እቤረ ወእጋለ ማውታ
ወተሉ ፈላሴ
ወይቤሉ ኢይሬኢ እግዚአብሄር

- ባልቴቲቱንና ድሀ አደጉን ገደሉ
ስደተኛውንም ገደሉ
እግዚአብሄር አያይም
የያእቆብ አምላክ አይመለከትም አሉ
መዝ - 93 ፤ 6 - 7

# <u>የእለቱ ምስባክ</u> መዝሙር ፵፬ ፥ ፱

ወትቀውም ንግሥት በየማንከ
በአልባሰ ወርቅ ዑጽፍት ወኁብርት
ስምዒ ወለትየ ወርእዪ ወአጽምዒ እዝነኪ።

<u>ትርጉም፦</u>

በወርቅ ልብስ ተጎናጽፋና ተሸፋፍና
ንግሥቲቱ በቀኝህ ትቆማለች
ልጄ ሆይ ስሚ እዩ ጆሮሽንም አዘንብዪ
ወገንሽን የአባትሽንም ቤት እርሺ።

<u>Responsorial</u> Psalm Ch. 45 Vers 9

At your right hand standing the queen in gold from Ophir.
Listen, O daughter, Consider and incline your ear;
Forget your own people also and your father's house

<u>የእለቱ ምስባክ</u>   መዝሙር ፺፩ ፥ ፲፪

ጻድቅሰ ከመ በቀልት ይፈሪ
ወይበዝኅ ከመ ዘግባ ዘሊባኖስ
ትክሉካን እሙንቱ ውስተ ቤተ እግዚአብሔር።

<u>ትርጉም፦</u>

ጻድቅ እንደ ዘንባባ ያፈራል
እንደ ሊባኖስ ዝግባም ያድጋል
በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ ተተክለዋል።

<u>Responsorial</u>   Psalm Ch. 92   Vers 12

The righteous shall flourish like a palm tree.
He shall grow like a cedar in Lebanon.
those who are planted in the house of the Lord.

የዕለቱ ምስባክ      መዝሙር ፵፫ ፥ ፳፪

እስመ በእንቲአሁ ይቀትሉነ ኩሎ አሚረ
ወኮነ ከመ አባግዕ ዘይጠብሑ
ንቃህ እግዚኦ ለምንት ትነውም።

ትርጉም፦

ስለ አንተ ሁል ጊዜ ተገድለናል
እንደሚታረዱም በጎች ሆነናል
አቤቱ ንቃ ለምንስ ትተኛለህ?

Responsorial      Psalm 44 Verse 22

Yet for your sake we are killed all day long.
We are accounted as sheep for the slaughter
Awake! Why do you sleep, O Lord?

ካህኑ አራቱን ማእዘን እንዲህ እያለ ይባርክ

ልዑል እግዚአብሔር ሁላችንን ይባርክ በመንፈሳዊም በረከት ሁሉ ያክብረን። ወደ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን መግባታችንንም ዘወትር በመፍራትና በመንቀጥቀጥ ከሚያገለግሉት ከቅዱሳን መላእክት ጋራ በአንድነት ያድርግ። በየጊዜውና በየሰዓቱም ሁሉ ከሚያመሰግኑት ከቅዱሳን መላእክት ጋራ በአንድነት ያድርግ ዛሬም ዘወትርም ለዘላለሙ።

The priest, while blessing the four quarters of the world, shall say the following :

O God, most high, bless us all and sanctify us with every spiritual blessing, and bring us into the holy church to be joined with his holy angels who serve Him always in fear and trembling, and glorify him at all times and all hours, both now and ever and world without end.

አምላካችንና መድኀኒታችን ሰውንም የምትወድ እግዚአብሔር ሆይ ቅዱሳን የሚሆኑ ደቀ መዛሙርትህንና አገልጋዮችህን ንጹሀን ሐዋርያትን ወደ አለም ሁሉ ዳርቻ የሰደድሃቸው አንተ ነህ። የመንግስትህን ወንጌል ይሰብኩና ያስተምሩ ዘንድ በሕዝብህ ውስጥ ያለውን ደዌውን ሁሉ በሽታውንም ሁሉ ያድኑ ዘንድ ከአለም አስቀድሞ የነበረውን የተሰወረውን ምስጢርህንም ያስተምሩ ዘንድ።

Lord our God and our Savior and lover of man, though art He who didst send thy holy disciples and ministers, and thy Pure apostles unto all the ends of the world to preach and teach the gospel of thy kingdom, and to heal all the diseases and all the sicknesses which are among thy people, and to proclaim the mystery hidden from before the beginning of the world.

አሁንም ጌታችን አምላካችን ሆይ ብርሀንህንና ጽድቅህን ላክልን የአሳባችንና የልቡናችንን አይኖች አብራልን የከበረ የወንጌልህን ቃል በመጨከን እንሰማ ዘንድ የበቃን አድርገን የምንሰማ ብቻ አይደለም እንደሰማን ልንሰራም ነው እንጂ ስለ አንዱ ፈንታ ሰላሳና ስልሳ መቶም ያማረ ፍሬ በላያችን ያፈራ ዘንድ የወገኖችህን ሀጢአት ታስተሰርይ ዘንድ ለመንግስተ ሰማያትም የበቃን እንሆን ዘንድ።

Now also, our Lord and our God, send upon us thy light and thy righteousness, and enlighten the eyes of our hearts and of our understanding, make us meet to persevere in hearing the word of thy holy gospel, and not only to hear but to do according to what we hear, so that it may bear good fruit in us, remaining not one only but increasing thirty, sixty, and an hundred fold, and forgive us out sins, us thy people, so that we may be worthy of the kingdom of heaven.

ካህን

ቡሩክ እግዚአብሔር አብ አኃዜ ኵሉ።

አእኵትዎ ለአብ

ሁሉን የያዘ እግዚአብሔር አብ ቡሩክ ነው

አብን አመስግኑት

Blessed be God, almighty father

Give thanks unto the father

ካህን

ወቡሩክ ወልድ ዋህድ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ። አእኲትዎ ለወልድ

ወልድ ዋህድ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ቡሩክ ነው ወልድን አመስግኑት

And blessed be the only begotten son Our Lord Jesus Christ. Give thanks unto the Son.

ካህን

ወቡሩክ መንፈስ ቅዱስ ጰራቅሊጦስ።

አእኰቶዎ ለመንፈስ ቅዱስ

መንፈስ ቅዱስም ቡሩክ ነው

መንፈስ ቅዱስን አመስግኑት

And blessed be the Holy Spirit the paraclete.

Give thanks unto the Holy Spirit

## ዲያቆን

**ሃሌ ሉያ ቁሙ ወአጽምኡ ወንጌለ ቅዱሰ ዜናሁ ለእግዚእነ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ**

**ሃሌ ሉያ! ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተናገረውን ቅዱስ ወንጌል ቁማችሁ ስሙ**

Halleluia, stand up and hearken to the Holy Gospel, the message of our Lord and Savior Jesus Christ.

ካህን

እግዚአብሔር ምስለ ኵልክሙ
እግዚአብሔር አድሮባችሁ ይኑር
The Lord be with you all.

ሕዝብ

ምስለ መንፈስከ
ከመንፈስ ጋር
And with Thy spirit

ካህን

ወንጌል ቅዱስ፤ ዘዜነወ ማቴዎስ/ማርቆስ/ሉቃስ/ ዘሰበከ ዮሐንስ ቃለ ወልደ እግዚአብሔር

ማቴዎስ/ማርቆስ/ሉቃስ የተናገረው ወይም ዮሐንስ የሰበከው የእግዚአብሔር ልጅ ቃል የሚሆን ቅዱስ ወንጌል

The Holy gospel which: Matthew/Mark/Luke/John preached the Word of the Son of God.

**ሕዝብ**

ስብሐት ለከ ክርስቶስ እግዚእየ ወአምላኪየ ኵሎ ጊዜ

ጌታዬ አምላኬ ክርስቶስ ሆይ ሁልጊዜ ለአንተ ምስጋና ይገባል።

Glory be to Thee, Christ my Lord and my God, at all times.

ተፈስሑ በእግዚአብሔር ዘረድአነ ወየብቡ ለአምላከ ያዕቆብ ንሥኡ መዝሙረ ወሀቡ ከበሮ መዝሙር ሐዋዝ ዘምስለ መሰንቆ።

ጌታዬ አምላኬ ክርስቶስ ሆይ ሁልጊዜ ለአንተ ምስጋና ይገባል። በረዳን በእግዚአብሔር ደስ ይበላችሁ የያዕቆብንም አምላክ አመስግኑ መዝሙሩን ያዙ ከበሮውንም ስጡ ከበገና ጋራ የተስማማ ነው።

Sing aloud unto God our strength: make a joyful noise unto the God of Jacob. Take a psalm, and bring hither the timbrel, the pleasant harp with the psaltery.

## በጾም ጊዜ በተፈስሁ ፈንታ

**During the fast the following will be said instead of the "Sing aloud"**

ሕዝብ

**በወንጌል መራህከነ ወበነቢያት ናዘዝከነ ዘለ ሊከ አቅረብከነ ስብሐት ለከ**

**በወንጌል መራኸን በነቢያትም አጸናኸን አንተ ቅሉ ሳቀረብከን ክብር ምስጋና ይገባል።**

Thou hast guided us with the Gospel, comforted us with the prophets, and drawn us nigh unto thee. Glory be to Thee

# የዕለቱ የወንጌል ምንባብ

## ከማርቆስ ወንጌል 12 ፤ 1 - 22

## READING FROM THE GOSPEL OF SAINT MARK

CHAPTER - 12 : 1 – 22

# የቅዱስ ሉቃስ ወንጌል
# ምዕራፍ ፩ ፥ ፴፱ - ፶፯

## READING FROM THE GOSPEL OF SAINT LUKE

# CHAPTER - 1 : 39 – 57

# የዕለቱ የወንጌል ምንባብ

# የቅዱስ ማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ ፲ ፥ ፲፮ - ፍጻሜ

## READING FROM THE GOSPEL OF SAINT MATTHEW

# CHAPTER - 10 : 16 – END

# ማቴዎስ ወንጌል ከተነበበ በኋላ

## ሕዝብ

ነአምን አበ ዘበአማን ወነአምን ወልደ ዘበአማን ወነአምን መንፈሰ ቅዱሰ ዘበአማን ህልወ ሥላሴሆሙ ነአምን

አብን በእውነት እናምናለን ወልድንም በእውነት እናምናለን መንፈስ ቅዱስንም በእውነት እናምናለን የማይለወጥ ሦስትነታቸውን እናምናለን

We believe in the very Father, We believe in the very Son, and we believe in the very Holy Spirit, we believe in their unchangeable Trinity.

# የማርቆስ ወንጌል ከተነበበ በኋላ

## ሕዝብ

እሉ ኪሩቤል ወሱራፌል ያዐርጉ ሎቱ ስብሐት እንዘ ይብሉ ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ አንተ እግዚአብሔር አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ

እሊህ ኪሩቤልና ሱራፌል ምስጋናን ያቀርቡለታል አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስን ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ አንተ እግዚአብሔር ነህ እያሉ

Those cherubim and seraphim offer to Him glory saying;Holy Holy Holy art thou God, Father, Son and the Holy Spirit.

## የሉቃስ ወንጌል ከተነበበ በኋላ

**ሕዝብ**

መኑ ይመስለከ እምነ አማልእክት እግዚኦ አንተ ውእቱ ዘትገብር መንክረ አርአይኮሙ ለሕዝብከ ኃይለከ ወአድኃንኮሙ ለሕዝብከ በመዝራዕትከ

አቤቱ ከአማልክት ወገን የሚመስልህ ማነው ታምራቱን የምታደርግ አንተ ነህ ፤ ለወገኖችህ ኃይልህን አሳየሃቸው ወገኖችህንም በክንድህ አዳንሃቸው

Who is like unto thee, O lord, among the gods? Thou art the God that doest wonders: thou hast declared thy strength among the people. Thou hast with Thine arm redeemed Thy people.

# የሉቃስ ወንጌል ከተነበበ በኋላ

## ሕዝብ

ሖርከ ውስተ ሲያል ወአዕረገ ፄዋ እምህየ ወጸጎከነ ምዕረ ዳግመ ግዕዛነ እስመ መጻእከ ወአድኀንከነ በእንተ ዝንቱ ንሴብሓከ ወንጸርሕ ኀቤከ እንዘ ንብል ቡሩክ አንተ እግዚኦ ኢየሱስ ክርስቶስ እስመ መጻእከ ወአድኃንከነ

ወደ ሲያል ሄደህ ከዚያ ምርኮን አወጣህ ፤ ዳግመኛም አንድ ጊዜ ነጻነትን ሰጠኸን መጥተህ አድነኸናልና ስለዚህ እናመሰግንሃለን አቤቱ ኢየሱስ ሆይ ብሩክ ነህ እያልን እንጮኻለን መጥተህ አድነኸናልና

Thou didst go into Kades and the Captives rose up from there, and thou didst grant us again to be set free, for thou didst come and save us. For this cause we glorify thee and cry unto thee saying, Blessed art thou, Lord Jesus Christ, for thou didst come and save us.

# የዮሐንስ ወንጌል ከተነበበ በኋላ

## ሕዝብ

ቀዳሚሁ ቃል ውእቱ ቃል ቃለ እግዚአብሔር ውእቱ ቃል ሥጋ ኮነ ወኀደረ ላዕሌነ ወርኢነ ስብሐቲሁ ከመ ስብሐተ ፩ዱ ዋህድ ለአቡሁ ቃለ አብ ሕያው ወቃል ማሕየዊ ቃለ እግዚአብሔር ተንሥአ ወሥጋሁኒ ኢማሰነ

ቃል በቅድምና ነበረ ይህ ቃል የእግዚአብሔር ቃል ነው ያ ቃል ሥጋ ሆነ ባህርያችንን ተዋሀደ ለአባቱ እንደ አንድ ልጅ የሚሆን ክብሩንም አየን የሕያው የአብ ቃል ነው ያ ቃልም መድኃኒት ነው የእግዚአብሔር ቃል ተነሳ ሥጋውም አልጠፋም

In the beginning was the Word, the Word was the Word of God: The Word was made flesh, and dwelt among us, and we he held his glory, the glory as of the only-begotten of the Father, the Word of the living Father, and the life-giving Word, the Word of God, rose again and his flesh was not corrupted.

## ንፍቅ ካህን

**ክቡር የሚሆን የወንጌልን ቃል እንሰማ ዘንድ እንሳለመውም ዘንድ በእርሱም ደስ ይለን ዘንድ ለዚህ የበቃን ያደረግኸን ሁሉን የያዝህ አምላካችን እግዚአብሔር ሆይ ላንተ ምስጋና ይገባል ዳግመኛም ክቡር የሚሆን የወንጌልህን ቃል በልቦናችን ትጽፍ ዘንድ እንለምናለን እንማልዳለንም**

Glory be to thee, Lord our God almighty, who hast made us meet to hear the word of thy holy Gospel and greet it and rejoice in it, again we ask and beseech that thou shouldest write the word of Thy holy gospel in our hearts, and accept our prayers

ንፍቅ ካህን

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በገባበት በዚህ በመሰዊያህ ልመናችንን ተቀበል በእኛም በወገኖቻችንም ላይ ይቅርታህንና ቸርነትህን ላክ በአንድ ልጅህ ላንተ ምስጋና ከሃሊነትም ይገባሃልና ለዘላለሙ አሜን

in this thy Temple wherein our Lord Jesus Christ hath entered, and send thy mercy and thy compassion upon us and upon thy people, through thy only begotten Son, for thine is the glory and power, world without end. Amen.

ዲያቆን

ፃኡ ንኡሰ ክርስቲያን

የክርስቲያን ታናናሾች የሆናችሁ ውጡ

Go forth, Ye catechumens.

ተንሥኡ ለጸሎት

ለጸሎት ተነሱ

Stand up for prayer.

ሕዝብ

እግዚኦ ተሣሃለነ

አቤቱ ይቅር በለን

Lord have mercy upon us.

ካህን

ሰላም ለኵልክሙ
ሰላም ለሁላችሁ ይሁን
Peace be unto you all.

ሕዝብ

ምስለ መንፈስከ
ከመንፈስህ ጋር
And with Thy spirit.

ካህን

ወካዕበ ናስተበቍዕ ዘኵሎ ይእኅዝ እግዚአብሔር አብ ለእግዚእ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ ንስእል ወንኅሥሥ እምነ ኂሩትከ መፍቀሬ ሰብእ።

ዳግመኛም ሁሉን የሚይዝ የጌታችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን አባት እግዚአብሔርን እንማልዳለን ሰው ወዳጅ ሆይ ከቸርነትህ እንሻለን እንለምናለን።

Again we beseech the almighty God, the Father of our Lord and our Savior Jesus Christ, we ask and entreat of thy goodness.

ተዘከር እግዚኦ ሰላመ ቤተ ክርስቲያን ቅድስት አሐቲ ጉባኤ እንተ ሐዋርያት እንተ ሀለወት እምጽንፍ እስከ አጽናፈ ዓለም።

አቤቱ ሐዋርያት የሰበሰቡዋት አንዲት የምትሆን የቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ሰላም አስብ ከዳርቻ እስከ ዓለም ዳርቻ ድረስ ያለች።

O lover of man, remember, Lord, the peace of the one holy apostolic church which reacheth from one end of the world to the other.

## ዲያቆን

ጸልዩ በእንተ ሰላመ ቤተ ክርስቲያን አሐቲ ቅድስት ጉባኤ እንተ ሐዋርያት ርትዕት በኀበ እግዚአብሔር

ሐዋርያት ለሰበሰቡዋት በእግዚአብሔር ዘንድ ስለቀናች፤ ክብርት ስለምትሆን አንዲት ቤተ ክርስቲያን ጸልዩ

Pray for the peace of the one holy apostolic church orthodox in the Lord.

ይ.ካ.

ኵሎ ሕዝበ ወኵሎ መራዕየ ባርኮሙ ቡራኬ ሳዕለ ሕዝብ። ኵሎ ሰላመ እንተ እምሰማያት ፈኑ ውስተ አልባቢነ ለኵልነ ወሰላመ ወሕይወተነ ጸግወነ ባቲ

ሕዝቡን ሁሉ መንጋዎችንም ሁሉ ባርካቸው። ከሰማይ የሚገኝ ሰላምን ሁሉ በሁላችን ልቡና አሳድርብን። በርስዋም የሕይወትን ሰላም ስጠን።

All the people and the whole flock bless thou, all the peace that is from heaven send thou into the hearts of us all and vouchsafe us the safety of our life therein.

ጸግዋ ሰላመ ለሀገሪትነ ኢትዮጵያ ለታዕካሃ
ወለሠራዊታ ለመኳንንታ ወለሕዝባ፡፡

ለአገራችን ለኢትዮጵያ ለአንድነቷ
ለሠራዊቷም ለመኳንንቷም ለሕዝቧም
ሰላምን ስጣት፡፡

ወጉባኤ አግዋርነ ዘአፍኣ ወውስጥ አሠርግዎሙ በኵሉ ሰላም ኦ ንጉሠ ሰላም ሰላመበ ሀበነ እስመ ኵሎ ወሀብከነ፡፡ አጥር የነ እግዚአብሔር ወዕሥየነ እስመ ዘእንበሌከ ባዕድ አልቦ ዘነአምር፡፡

በእዳሪና በውስጥ ያሉትን ጎረቤቶቻችንን ሁሉ በፍጹም ሰላም አስጊጻቸው፡፡ የሰላም ንጉሥ ሆይ ሰላምህን ስጠን፤ ሁሉን ሰጥተኸናልና፡፡ እግዚአብሔር ሆይ ጥሪት አድርገን፤ ዋጋችነንም ስጠን፤ ካንተ በቀር ሌላ የምናውቀው የለምና፤

And to the multitude of our neighbors at home and abroad adorn them with all peace: O King of peace, grant us thy peace for thou hast granted us all things. Posses us, O Lord and requite us, for beside thee we know none other:

ስምከ ቅዱስ ንሰሚ ወንጼውዕ ከመ ትሕየው ነፍስነ በመንፈስ ቅዱስ ወኢይትኀየል ሞት ኃጢአተ ላዕሌነ ለአግብርቲከ ወለኵሉ ሕዝብከ።

ቅዱስ የሚሆን ስምህን ፈጽመን እንጠራለን ነፍሳችን በመንፈስ ቅዱስ ትድን ዘንድ በኃጢአት የመጣ ሞትም በኛ ባገልጋዮችህ ላይ በወገኖችህም ሁሉ እንዳይበረታታ።

we make mention of thy holy name and call upon it, that our souls may live through the Holy Spirit and that the death of sin may not have dominion over us thy servants and all thy people:

በ፩ ወልድከ ዘቦቱ ለከ ምስሌሁ ወምስለ ቅዱስ መንፈስ ስብሐት ወእኂዝ ይእዜኒ ወዘልፈኒ ወለዓለም ዓለም አሜን።

ባንድ ልጅህ ከርሱ ያለ ክብር ጽንዕ ላንተ ይገባል። ከርሱ ጋራ ከመንፈስ ቅዱስም ጋራ ዛሬም ዘወትርም ለዘላለሙ አሜን።

Through thy only-begotten Son to whom with thee and with the Holy Spirit be glory and dominion, both now and ever and world without end. Amen.

ሕዝብ

ኪርያላይሶን

Kyrie eleison.

ዲያቆን

ተንሥኡ ለጸሎት

ለጸሎት ተነሱ

Stand up for prayer.

ሕዝብ

እግዚኦ ተሣሃለነ

አቤቱ ይቅር በለን

Lord have mercy upon us.

ካህን

ሰላም ለኩልክሙ

ሰላም ለሁላችሁ ይሁን

Peace be unto you all.

ሕዝብ

ምስለ መንፈስከ

ከመንፈስህ ጋር

And with Thy spirit.

ይ.ካ.

ወካዕበ ናስተበቍዕ ዘኰሎ ይእኅዝ እግዚአብሔር አብ ለእግዚእ መድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ ንስእል ወንኅሥሥ እምኀ ጊሩትከ ኦ መፍቀሬ ሰብእ፡፡
ተዘከር እግዚኦ ማኅበረነ ባርኮሙ፡፡

ዳግመኛም፤ ሁሉን የያዘ የጌታችንና መድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን አባት እግዚአብሔርን እንማልዳለን፤ ሰው ወዳጅ ሆይ ከቸርነትህ እንሻለን እንለምናለን፡፡
አቤቱ አንድነታችንን አስብ ባርካቸው፡፡

and again we make our supplication to the almighty God, the Father of our Lord and our Savior Jesus Christ; we ask and entreat of thy goodness, O lover of man:
Remember, Lord, our congregation; bless them.

## ዲያቆን

ጸልዩ በእንተ ዛቲ ቤተ ክርስቲያን ቅድስት ወማኅበርነ ውስቴታ

ክብርት ስለምትሆን ስለዚች ቤተ ክርስቲያን ልዩ በውስጥዋ ስላለ አንድነታችንም ጸልዩ

Pray for this holy church and our congregation therin.

## ሕዝብ

ማኅበረነ ባርክ ዕቀብ በሰላም

አንድነታችንን አጽንተህ በፍቅር ጠብቅ

Bless our congregation and keep us in peace.

ይ.ካ.

ጸግዎሙ ከመ ይኩኑ ለከ ዘእንበለ ጽርዓት ወኢክልዓት ይገበሩ ፈቃደከ ቅድስተ ወብፅዕት ቤተ ጸሎት ቤተ ንጽሐ ወቤተ በረከት ጸግወነ እግዚኦ ለነኒ ለአግብርቲከ ወለእለ ይመጽኡ እምድኅሬነ ወእስከ ለዓለም መዋዕለ ጸጉ።

የተደነቀችና የከበረች ፈቃድህን ያለማቋረጥና ያለመከልከል እንዲሠሩ ያንተ ይሆኑ ዘንድ የጸሎትን ቤት የንጽሕናንም ቤት የበረከትንም ቤት ስጣቸው። ለኛም ለባሮችህ ከኛም በኋላ ለሚነሡ፤ አቤቱ ስጠን። እስከ ዘላለምም ዘመንን ስጥ።

Grant that they may be Thine that without slothfulness or hindrance they may do thy holly and blessed will, a house of prayer, a house of purity and a house of blessing. Give us also, Lord, us thy servants, and to them that shall come after us, vouchsafe us to the end of the world, length of days.

ይ.ካ.

ተንሥእ እግዚኦ አምላኪየ ወይዘረው ፀርከ ወይጒየዩ ኵሎሙ እምቅድመ ገጽከ፤ እለ ይጸልዑ ቅዱስ ወቡሩከ ስመከ።

አቤቱ አምላኬ ሆይ ተነሥ ጠላቶችህም ይበተኑ፤ ቅዱስ ምስጉን የሚሆን ስምህን የሚጠሉ ሁሉም ከፊትህ ይሽሹ።

Arise Lord My God and let thy enemies be scattered and let them that hate thy holy and blessed name flee before thee.

ይ.ካ.

ወሕዝብከሰ ይኩኑ ብሩካነ በበረከተ እልፍ
ወአእላፈ አእላፋት እለ ይገብሩ ፈቃደከ
በኵሉ ጊዜ። በ፩ዱ ወልድከ ዘቦቱ ለከ ምስሌሁ
ወምስለ ቅዱስ መንፈስ ስብሐት ወእ’ጊዝ ይእዜኒ
ወዘልፈኒ ወለዓለመ ዓለም አሜን።

በጊዜው ሁሉ ፈቃድህን የሚሠሩ ወገኖችህ ግን
እልፍ አእላፋት በሚሆኑ መላእክት በረከት
የተባረኩ ይሁኑ። ባንድ ልጅህ በርሱ ያለ ክብር
ጽንዕ ላንተ ይገባል። ከርሱ ጋራ ከመንፈስ
ቅዱስም ጋራ ዛሬም ዘወትርም ለዘላለሙ፤ አሜን።

But let thy people who do thy will at all times be blessed with blessings a thousand thousand and ten thousand times ten thousand, through thy only-begotten Son through whom to thee with him and with the Holy Spirit be glory and dominion. both now and ever and world[253] without end. Amen.

ዲያቆን

ንበል ኲልነ በጥበበ እግዚአብሔር ጸሎተ ሃይማኖት

በእግዚአብሔር ጥበብ ሁነን በሰላም ሁላችን የሃይማኖት ጸሎት እንበል

Let us all say, in the wisdom of God, the prayer of faith.

ጸሎተ ሃይማኖት

(በዜማ) ነአምን በአሀዱ አምላክ እግዚአብሔር አብ አኃዜ ኲሉ ገባሬ ሰማያት ወምድር ዘያስተርኢ ወዘኢያስተርኢ

# ጸሎተ ሃይማኖት

ሁሉን በያዘ ሰማይንና ምድርን የሚታይና የማይታየውን በፈጠረ በአንድ አምላክ በእግዚአብሔር አብ እናምናለን።

## The Prayer of Faith

We Believe in one God the Father almighty, maker of heaven, earth and all things visible and invisible.

ዓለም ሳይፈጠር ከርሱ ጋር በነበረ የአብ አንድ
ልጁ በሚሆን በአንድ ጌታ በኢየሱስ ክርስቶስም
እናምናለን። ከብርሃን የተገኘ ብርሃን፣ ከእውነተኛ
አምላክ የተገኘ አምላክ፣ የተፈጠረ ያይደለ
የተወለደ፣ በመለኮቱ ከአብ ጋር የሚተካከል፤

And we believe in one Lord Jesus Christ, the only-begotten Son of the Father who was with Him before the creation of the world: Light from light, true God from true God, begotten not made, of one essence with the Father:

ሁሉ በእርሱ የሆነ ያለ እርሱ ግን ምንም የሆነ የለም። በሰማይም ያለ በምድርም ያለ። ስለ እኛ ስለሰው ስለ መዳናችን ከሰማይ ወረደ ከመንፈስ ቅዱስ የተነሣ ከቅድስት ድንግል ማርያም ፈጽሞ ሰው ሆነ።

By whom all things were made, and without Him was not anything in heaven or earth made: Who for us men and for our salivation came down from heaven, was made man and was incarnate from the Holy Spirit and from the holy Virgin Mary.

ሰው ሆኖ በጴንጤናዊ ጲላጦስ ዘመን ስለ እኛ ተሰቀለ። ታመመ፤ ሞተ፤ ተቀበረም። በሦስተኛውም ቀን ከሙታን ተለይቶ ተነሣ፤ በቅዱሳት መጻሕፍት እንደተጻፈ በክብር ወደ ሰማይ አረገ፤ በአባቱም ቀኝ ተቀመጠ።

Became man, was crucified for our sakes in the days of Pontius Pilate, suffred, died, was buried and rose from the dead on the third day as was written in the holy scriptures: Ascended in glory into heaven, sat at the right hand of His Father,

ዳግመኛ ሕያዋንን ሙታንንም ይገዛ ዘንድ በጌትነት ይመጣል። ለመንግሥቱም ፍጻሜ የለውም፤ ጌታ ማህየዊ በሚሆን ከአብ በሰረፀ በመንፈስ ቅዱስም እናምናለን። እንሰግድለት እናመሰግነውም ዘንድ፥ ከአብና ከወልድ ጋራ በነቢያት የተናገረ

and will come again in glory to judge the living and the dead; there is no end of His reign. And we believe in the Holy Spirit, the life- giving God, who proceedeth from the Father; we worship and glorify Him with the Father and the Son; who spoke by the prophets;

ከሁሉ በላይ በምትሆን ሐዋርያት በሰበሰቧት በአንዲት ቅድስት ቤተ ክርስቲያንም እናምናለን። ኃጢአት ለማስተሥረይ በአንዲት ጥምቀት እናምናለን። የሙታንንም መነሣት ተስፋ እናደርጋለን የሚመጣውንም ሕይወት ለዘለዓለሙ አሜን።

And we believe in one holy, universal, apostolic church; And we believe in one baptism for the remission of sins, and wait for the resurrection from the dead and the life to come, world with out end. Amen!

## ሕዝብ

(በዜማ) ወንሴፎ ትንሣኤ ሙታን ወሕይወተ ዘይመጽእ ለዓለመ ዓለም፤ አሜን

የሙታንንም መነሳት ተስፋ እናደርጋለን የሚመጣውንም ሕይወት ለዘለዓለሙ፤ አሜን፤

And wait for the resurrection from the dead and the life to come, world with out end. Amen!

## ካህን

እጄን ከአፍአዊ እድፍ ንጹሕ እንዳደረግሁ እንደዚሁም ከሁላችሁ ደም ንጹሕ ነኝ፤ ደፍራችሁ ወደ ክርስቶስ ሥጋና ደም ብትቀርቡ ከርሱ ስለመቀበላችሁ መተላለፍ የለብኝም። ኃጢአታችሁ በራሳችሁ ይመለሳል እንጂ በንጽሕና ሆናችሁ ባትቀርቡ እኔ ከበደላችሁ ንጹሕ ነኝ።

As I have cleansed my hands from outward pollution, so also I am pure from the blood of you all. If you presumptuously draw nigh to the body and blood of Christ I will not be responsible for your reception thereof. I am pure of your wickedness, but your sin will return upon your head if you do not draw nigh in purity.

## ዲያቆን

ይህን የካህኑን ቃል ያቃለለ ወይም የሳቀና የተነጋገረ ወይም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በክፋት የቆመ ቢኖር ጌታችንን ኢየሱስ ክርስቶስን እንዳሳዘነው በርሱም እን ደተነሳሳ ይወቅ ይረዳ፤ ስለ በረከት ፈንታ መርገምን፤ ስለ ኃጢአት ሥርየት ፈንታም ገሃነመ እሳትን ከእግዚአብሔር ዘንድ ይቀበላል

If there be any who disdains this word of the priest or laughs or speaks or stands in the church in an evil manner, let him know and understand that he is provoking to wrath our Lord Jesus Christ, and bringing upon himself a curse instead of a blessing, and will get from God the fire of hell instead of the remission of sin.

ካህን

ኦ እግዚእየ ወአምላኪየ ገባሬ ሥርዓት ወሃቤ ሰላም ወፍቅር አሰስል እማላዕሌየ ኵሎ ሕሊና እኩየ ቂመ ወቅንዓተ ወኵሎ ፍትወታተ ሥጋውያተ፡፡ ወክፍለኒ እደመር ምስለ አግብርቲከ ቅዱሳን እለ አሥመሩከ በሥነ ሕይወቶሙ በመዋዕለ ፍቅር ወሰላም፡፡

አቤቱ ጌታዬ አምላኬ ሆይ ሥርዓትን የሠራህ ሰላምንና ፍቅርን የምትሰጥ፤ ክፉውን ሕሊና ሁሉ ቂምን ቅንዓትንም ሥጋዊ ፈቃድንም ሁሉ ከኔ አርቅልኝ፡፡ በበጎ ሕይወታቸው በሰላምና በፍቅር ወራት ካገለገሉህ ከክቡራን ባሮችህ ጋራ አንድ እንድሆን አድለኝ፡፡

O my Lord and God, author of the law, giver of peace and love, take away from me every evil thought, revenge, envy, and all the lusts of the flesh, Make me meet to be added to thy holy servants who pleased thee by the beauty of their lives in the days of love and peace:

ካህን

እስመ አንተ ውእቱ ዘወረድከ እምሰማይ ወገበርከ ሰላመ ምስለ ሰማያውያን ወምድራውያን ወአስተጋባእከሙ ለኵሎሙ ሕዝብከ ከመ ይሰብሑ ኪያከ፤ እስመ ለከ ስብሐት ለዓለመ ዓለም፤ አሜን።

ከሰማይ የወረድህ፤ ከሰማያውያንና ከምድራውያንም ጋራ ሰላምን ያደረግህ፤ አንተንም ያመሰግኑ ዘንድ ወገኖችህን ሁሉ የሰበሰብሃቸው አንተ ነህና፤ ምስጋና የሚገባህ ስለ ሆነ፤ ለዘላለሙ አሜን።

Because it is thou who didst came down from heaven and make peace between the inhabitants of heaven and the inhabitants of earth, and didst gather together all thy people to glorify thee, for Thine is the glory, world without end. Amen.

ዲያቆን

ተንሥኡ ለጸሎት

ለጸሎት ተነሱ

Stand up for prayer.

ሕዝብ

እግዚኦ ተሣሃለነ

አቤቱ ይቅር በለን

Lord have mercy upon us.

## ካህን

ሰላም ለኩልክሙ
ሰላም ለሁላችሁ ይሁን
Peace be unto you all.

## ሕዝብ

ምስለ መንፈስከ
ከመንፈስህ ጋር
And with Thy spirit.

## ጸሎተ አምኃ ዘባስልዮስ /ባስልዮስ የተናገረው የአምኃ ጸሎት/። Prayer of Salutation

ለዘላለሙ ገናና የምትሆን እግዚአብሔር ሆይ ሰውን ያለጥፋት የፈጠርኸው። አስቀድሞ በሰይጣን ቅንኣት የገባውን ሞት ህያው በሚሆን ልጅህ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ መምጣት አጠፋህ።

God, great eternal, who didst form a man uncorrupt, Thou didst abolish death that came first through the envy of Satan, by the advent of Thy living Son our Lord and our God and our Savior Jesus Christ,

የሰማይ ሰራዊት እንዲህ እያሉ አንተን የሚያመሰግኑባትን፥ ከሰማይ የተገኘች ሰላምን በምድር ሁሉ መላህ፤ በሰማይ ለእግዚአብሔር ምስጋና ይገባል፤ በምድርም ሰላም የሰው ፈቃድ

and Thou didst fill all the earth with Thy peace which is from heaven, wherein the armies of heaven glorify Thee saying: Glory to God in heaven and on earth peace, his goodwill toward men.

ሕዝብ

ስብሐት ለእግዚአብሔር በሰማያት
ወሰላም በምድር ሰምረቱ ለሰብእ

በሰማይ ለእግዚአብሔር ምስጋና ይገባል
በምድርም ሰላም፤ የሰው ፈቃድ

Glory to God in heaven and on earth
peace, His goodwill toward men.

ካህን

አቤቱ ፈቃድህን በሁላችን ልቡና ሙላ፤ ከኃጢአትም ሁሉ ከጽርዓትም ሁሉ አንጻን። ከቂምና ከቅንዓትም ሁሉ ከክፉም ስራ ሁሉ፤ ሞትን ከምታለብስ ክፉን ነገር ከማሰብም አንጻን በተለየች ሰላምታ እርስ በርሳችን እጅ እንነሳሳ ዘንድ ሁላችንንም የበቃን አድርገን።

O Lord, in Thy goodwill fill the hearts of us all purify us from all corruption and from all excess, and from all revenge and envy and from all wrong-doing and from the remembrance of ill which clothes with death. And make us all meet to salute one another with a Holy salutation.

## ዲያቆን

ጸልዩ በእንተ ሰላም ፍጽምት ወፍቅር ተአምኁ በበይናቲክሙ በአምኃ ቅድሳት

ፍጽምት ስለምትሆን ሰላምና ፍቅር ጸልዩ እርስ በርሳችሁ በተለየች ሰላምታ እጅ ተነሳሱ

Pray for the perfect peace and love. Salute one another with a holy salutation.

## ሕዝብ

ክርስቶስ አምላክነ ረስየነ ድልዋነ ከመ ንትአማኅ በበይናቲነ በአምኃ ቅድሳት

አምላካችን ክርስቶስ ሆይ እርስ በርሳችን በተለየች ሰላምታ እጅ እንነሳሳ ዘንድ የበቃን አድርገን

Christ our God, make us meet to salute one another with a holy salutation.

ካህን

ክብርት ከምትሆን ስጦታህ ሳይፈረድብን እንቀበል፤ ይህችው፥ የማታልፍ ሰማያዊት ናት፤ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ። በርሱ ያለ ክብር ጽንእ ከርሱ ጋራ ከመንፈስ ቅዱስም ጋራ ለአንተ ይገባል።ዛሬም ዘወትርም ለዘላለሙ አሜን።

And to partake without condemnation, of Thy Holy immortal heavenly gift, through Jesus Chris our Lord: through whom to Thee with Him and with the Holy Spirit be glory and dominion, both now and ever and world without end. Amen.

ካህን

አኰቴተ ቍርባን ዘ318ቱ ርቱዓነ ሃይማኖት ጸሎቶሙ ወበረከቶሙ የሀሉ ምስለ ርዕሰ ጸሎቱሙ ወበረከቶሙ የሀሉ ምስለ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳቲነ አባ ---- ወምስለ ሊቀጳጳሰነ አባ ---- ወምስለ ኵልነ ሕዝበ ክርስቲያን ወይዕቀባ ለሀገሪትነ ኢትዮጵያ፡፡ ለዓለመ ዓለም አሜን፡፡

ሃይማኖታቸው የቀና 318 ሊቃውንት የተናገሩት የቍርባን ምስጋና ጸሎታቸውና በረከታቸው ከጳጳሳቱ አለቃ አባ ----ና ከጳጳሳችን አባ ----ኀ ከሁላችንም ጋራ ይሁን አገራችን ኢትዮጵያንም ይጠብቃት፡፡ ለዘለዓለሙ አሜን፡፡

The Anaphora of the Three Hundred and Eighteen Orthodox; may their prayers and their the blessings be with our congregation world without end. Amen.

ካህን

እግዚአብሔር ምስለ ኲልክሙ
እግዚአብሔር ከሁላችሁም ጋር ይሁን
The Lord be with you all.

ሕዝብ

ምስለ መንፈስከ
ከመንፈስህ ጋር
And with Thy spirit

ካህን

አእኰትዎ ለአምላክነ
አምላካችንን አመስግኑት
Give Ye thanks unto our God.

ሕዝብ

ርቱዕ ይደሉ
እውነት ነው ይገባል
It is right, it is just.

## ካህን

አልዕሉ አልባቢክሙ

ልቦናችሁን ከፍ ከፍ አድርጉ

Lift up your hearts.

## ሕዝብ

ብነ ኀበ እግዚአብሔር አምላክነ

በአምላካችን በእግዚአብሔር ዘንድ አለን

We have lifted them up unto the Lord our God.

# ካህን

ግሩም በውስተ ደመናት ወልዑል እምሰማያት፡፡ እግዚአብሔር ስቡሕ በኵሉ ፍናዊሁ አምላከ አማልክት ፀባዖት ፍጹም፡፡

በደመናት ግሩም ነው ከሰማያትም ይልቅ ከፍ ያለ ነው፡፡ እግዚአብሔር በመንገዱ ሁሉ ምስጉን ነው የአማልክት አምላክ ፍጹም አሸናፊ ነው፡፡

# ካህን

አልቦ አመ ኢሀሎ ወአልቦ አመ ተኀጥአ ወአልቦ አመ አስተርአየ ፍጹመ በመለኮቱ፡፡ አልቦ ዘይክል ርእዮቶ ወአልቦ ዘየአምር ዘከመ እፎ ህላዌሁ፡፡

የሌለበት ጊዜ የለም የታጣበትም ጊዜ የለም፡፡ በመለኮቱ ግን ፈጽሞ የታየበት ጊዜ የለም፡፡ እርሱን ማየት የሚችል የለም አነዋወሩም እንደምን እንደሆነ የሚያውቅ የለም፡፡

# ካህን

ዘኪያሁ ይሴብሑ ሰማያት ወምድር ምስለ ኵሉ ዓለሞሙ ባሕር ወአፍላግ ወኵሉ ዘውስቴቶሙ፡፡ ዘበጸጋሁ ተፈጥረ ኵሉ ወበኂሩቱ ይበይት ኵሉ፡፡ ዘውእቱ ዋሕድ አበ ዋሕድ አበ እግዚእ አበ መሢሕ ዘበአማን ብርሃን ምስለ ዘወለዶ፡፡

ሰማይና ምድር ከዓለማቸው ሁሉ ጋራ ባሕርና ወንዞች በውስጣቸውም ያሉ ሁሉ እርሱን የሚያመሰግኑ፡፡ በጸጋው ሁሉ የተፈጠረ በቸርነቱም ሁሉ የሚያድር፡፡ ይኸውም አንድ የሚሆን ያንድ አባት የጌታ አባት ከወለደው ጋራ እውነተኛ ብርሃን የሚሆን የመሢሕ አባት ነው፡፡

ዲያቆን

ተሰጥኦውን መልሱ

Answer Ye.

ሕዝብ

ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር ጸባዖት ፍጹም ምሉዕ ሰማያተ ወምድረ ቅድሳተ ስብሐቲከ።

ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ ፍጹም አሸናፊ እግዚአብሔር የጌትነትህ ምስጋና በሰማይ የመላ ነው

Holy Holy Holy, perfect Lord of hosts, heaven and earth are full of the Holiness of Thy Glory.

# ካህን

ንቤኑ ህላዌሁ ለአብ ምስለ ወልዱ ወህላዌሁ ለወልድ ምስለ አቡሁ፡፡ እምቅድመ ፍጥረት ወእምቅድመ ግብረተ ሰማያት እምቅድመ ትሣረር ምድር፡፡

የአብን ከልጁ ጋራ አነዋወሩን የወልድንም ከአባቱ ጋራ አነዋወሩን እንናገራለን፡፡ ከፍጥረት ሁሉ በፊት ከሰማያትም መፈጠር በፊት ምድር ሳትፈጠር፡፡

# ካህን

ወእምቅድመ ይቁሙ አድባር ወአውግር
ወእምቅድመ ያስተርኢ ኑኀ አየር ወእምቅድመ
ይንፋሕ ኃይለ ነፋስ፡፡

ተራራዎችና ኮረብቶች ሳይቆሙ የአየርም
ርዝመት ሳይታይ የነፋስ ኃይል ሳይነፍስ፡፡

# ካህን

ወእምቅድመ ያንበስብስ ፀዓዕ ወእምቅድመ ያስተርኢ ብልሐተ መብረቅ ወእምቅድመ ይድምፅ ነጐድጓድ ወይሰፍሑ ደመናት፡፡

ብልጭልጭታም ሳይመላለስ የመብረቅም ፍጥነት ሳይታይ ነጐድጓድም ሳይሰማ ደመናትም ሳይዘረጉ፡፡

# ካህን

ወእምቅድመ ፍጥረተ መላእክት እምቅድመ ኵሉ ስም ዘይሰመይ በታሕተ ሰማይ ወምድር፡፡

ከመላእክትም መፈጠር በፊት ከሰማይ በታች ከምድርም ከሚጠራ ስም ሁሉ በፊት፡፡

# ካህን

ወኢመኑሂ ሐሊዩ ወአዕሚቆ ኢይክል ረኪበ ህላዌሁ እመሂ ተለዐለ እስከ ሰማያት ወኀለፈ እምኀበ አጋዕዝት፡፡ ወረከበ 4ተ እንስሳ ምሉዓነ አዕይንተ ዘኵለንታሆሙ ፀዳል ወእምአፉሆሙ ይወፅእ አምሳለ ነደ እሳት፡፡

ማንም አስቦ አጥልቆም አነዋወሩን ማግኘት አይችልም ምንም እስከ ሰማይ ቢወጣ ከአጋዕዝትም ዘንድ ቢያልፍ፡፡ ዓይንን የተመሉ ሁለንተናቸው ብርሃን የሚሆን ከአንደበታቸው ነደ እሳት የሚመስል ቅዳሴ የሚወጣ አራቱ እንስሳንም ቢያገኝ፡፡

# ካህን

ወካዕበ ለእመ ወረደ ምድረ ወኀለፈ ባሕረ ነፋስ ወእሳተ፡፡ ወካዕበ ለእመ ወፅአ እምህየ ወነሠሠ የማነ ወፀጋመ፡፡ ወኢበምክሕ ወኢበጸቢተ ሕሊና፡፡

ዳግመኛም ወደ ምድር ቢወርድ ባሕርንና ነፋስን እሳትንም አልፎ ቢሄድ ዳግመኛም ከዚያ ወጥቶ በመመካትም ሆኖ በሕሊናም በመዋኘት ቀኙንና ግራውን ቢመረምር፡፡

ዲያቆን

የተቀመጣችሁ ተነሱ

Ye that are sitting, stand up.

ካህን

ኢይክል ይባእ ማእከለ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ከመ ያእምር ዘከመ እፎ ህላዌሁ።

አነዋወሩ እንዴት እንደ ሆነ ያውቅ ዘንድ በአብና በወልድ በመንፈስ ቅዱስም መካከል ሊገባ አይችልም።

# ካህን

ወለዶ አብ ለወልዱ ኢይትበሀል ዘ ጊዜ ወበዘከመዝ መዋዕል ወለዶ፡፡

አብ ልጁን ወለደው በዚህ ጊዜ እንዲህ ባለ ዘመንም ወለደው አይባልም፡፡

# ካህን

ኢይትአመር ልደቱ እምአብ እስመ ዕፁብ ውእቱ ወኢይትዐወቅ ህላዌሁ እሰመ ሥውር ውእቱ፡፡ ውእቱ ለአቡሁ የማኑ እደ መዝራዕቱ ወልዱ ወፍቁሩ ዘከማሁ አምሳሊሁ፡፡

ከአብ መወለዱ አይታወቅም ጭንቅ ነውና፡፡ አነዋወሩም አይታወቅም የተሠወረ ነውና፡፡ ላባቱ ቀኙ ነው፡፡ ክንዱ ልጁ ወዳጁም፤ እንደርሱ የሚሆን የሚመስለው ነው፡፡

ዲያቆን

ወደ ምሥራቅ ተመልከቱ።

Look to the east.

ካህን

ወለዶ አብ ለወልዱ አኮ በምክንያት ዘወለዶ ለመርድአ ግብር ከመ ይትለአኮ ዘከመ ተፀንሰ፡፡ ወአመ ፈጠረ ሰማያተ ወምድረ አልቦ ዘረድኦ እስመ ከሃሊ ውእቱ፡፡

አብ ልጁን ወለደው፡፡ እንደ ተቸገረ ሰው ያገለግለው ዘንድ ለሥራ ርዳታ በምክንያት፡፡ የወለደው አይደለም፡፡ ሰማይንና ምድርን በፈጠረም ጊዜ የረዳው የለም ከሃሊ ነውና፡፡

## ካህን

አኮ ከመ ብእሲ ዘፃመወ ወአዕረፈ አላ ሰይፈ እሳት ይወፅእ እምአፉሁ ዘነበበ በጊዜሃ ይገብር ወዘሐለየ በቅጽበት ይከውኖ ዘውእቱ ሐሊና ሐሊናት ጠቢብ ወኬንያ።

እንደ ሰው ደክሞት ያረፈ አይደለም። የእሳት ሰይፍ ከአፉ ይወጣል እንጂ። የተናገረውን በዚያው ጊዜ ያደርጋል፤ ያሰበውም በቅጽበት ይሆንለታል፤ የሐሊናት ሐሊና ጥበበኛም ብልሃተኛም እርሱ ነው።

## ካህን

መኑ ከማሁ ይጼዕን ቀመረ ወየሐንፅ መሠረተ ይጸውር ድደ ወይነብር ጠፈረ፡፡ ይሣርር ዲበ ማይ ወየሐንፅ በደቃቅ ወይጠበልል በረቂቅ ይዌስን በኖፃ ወይዔምድ በነፋስ ይሰቀል ማየ ወይሰሚ ሰማየ፡፡

እንደርሱ በቀመር የሚቀመጥ፤ መሠረትን የሚሠራ፤ መሠረትን ተሸክሞ በጠፈር የሚኖር ማነው፤ በውኃ ላይ ይመሠርታል፤ በጥቃቅን ይሠራል፤ በረቂቅ ይጠቀልላል በአሸዋ ይወስናል፡፡ በነፋስ ያጸናል፤ ውኃውን ሰቅሎ ሰማይ ይለዋል፡፡

# ካህን

የዐቍር ማየ በማኅፀን ወያረግዕ ከመ ይኩን ሥጋ የዐሥር በአሥራው ወያጸንዕ በአምትንት ይኄልቍ አሥዕርተ፡፡ ይፈትን ልበ ወየአምር ኵልያተ፡፡

ውኃን በማኅፀን ይቋጥራል፡፡ ሥጋም ይሆን ዘንድ ያረጋዋል፤ በሥር ያሥረዋል፤ በጅማትም ያጸናዋል ጠጕርን ይቈጥራል፡፡ ልብን ይመረምራል ኵላሊትንም ያውቃል፡፡

# ካህን

ወለዶ አብ ለወልዱ አልቦ ዕለት ወአልቦ ሰዓት፡፡ ወአመ ወለዶ ኢተባሕተወ አቡሁ ሎቱ እምቅድመ ይፍጥር መላእክተ ለቅዳሴ አኮ ስብሐቲሁ ዘተፀርዐ አላ ምሉዕ ውእቱ ስብሐቴተ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ፡፡

አብ ልጁን ወለደው ዕለት ግን የለም፤ ሰዓትም የለም፡፡ በወለደውም ጊዜ አባቱ ከርሱ ብቸኛ አልሆነም፡፡ መላእክትንም ለምስጋና ሳይፈጥር ምስጋናው የተቋረጠ አይደለም፡፡ የአብ የወልድና የመንፈስ ቅዱስ ምስጋና የመላ ነው እንጂ፡፡

## ዲያቆን

እናስተውል ።

Let us give heed.

## ካህን

ወአመ ፈጠሮ ለአቡነ አዳም አኮ ዘአንሶሰወ ከመ ያምጽእ መሬተ ወማየ ነፋሰ ወእሳተ፡፡ አላ እመንበሩ ኢተሐውሰ ወኢያንቀልቀለ ፍጹመ፡፡

አባታችንን አዳምን በፈጠረውም ጊዜ መሬትንና ውኃን ነፋስንና እሳትን ያመጣ ዘንድ የተመላለሰ አይደለም፡፡ ከዙፋኑ ሳይነቃነቅ ፈጽሞ ሳይነዋወጽም ነው እንጂ፡፡

# ካህን

ወእንዘ ሀሎ ህየ ነሥአ 4ተ ጠባይዐ 2ተ እምዘይትገሠሥ ወ2ተ እምዘኢይትገሠሥ 3ተ እዘይትረእይ ወ1ደ እምዘኢይትረአይ።

በዚያም ሳለ አራቱን ባሕርያት ነሣ። ሁለቱን ከሚዳሰስ ሁለቱን ግን ከማይዳሰስ፤ ሦስቱን ከሚታይ አንዱን ከማይታይ።

## ካህን

ቦቱ ለሐኮ ወአሠነዩ በእደዊሁ ቅዱሳት ሰዐሞ ወአፍቀሮ። ወነፍሐ ላዕሌሁ መንፈሰ ሕይወት እምቅድመ ይሕንፅ አየራተ ወአርያ ማተ አኮ ዘተትሕተ አሳ ጽኑዐ መንበር ወእዙዘ መንግሥት።

ቅዱሳት በሚሆኑ እጆቹ በርሱ አሳምሮ ፈጠረው ሳመው ወደደውም። የሕይወትንም መንፈስ በርሱ ላይ እፍ አለ፤ አየራትንና ሰማያትንም ሳይፈጥር የተዋረደ አይደለም፤ በዙፋን የጸና፤ በመንግሥቱም የጸና ነው እንጂ።

# ካህን

ዘበላዕሉ አንጐድጐደ ወዘበታሕቱ አርዐደ፤ ወደመናተ ኬደ ዘእንበለ እሳት አንደደ፤ ወዘእንበለ ማይ አብረደ።

በላይ ላሉት ድምፅን አሰማ በታች ያሉትንም አንቀጠቀጠ ደመናትንም ረገጠ። ያለ እሳት አቃጠለ። ያለውኃም አቀዘቀዘ።

# ካህን

ወአመ ፈጠረ ፀሓየ ወወርኀ አኮ ከመ ያብሩሁ ሎቱ ከመ ዘጸልሞ አላ ጸገዎሙ ንስቲተ እምዘዚአሁ ብርሃን መጠነ ኅጠት ሥርናይ፡፡ ወበእንተዝ አብርሁ ዲበ ሰብእ፡፡

ፀሓይንና ጨረቃን በፈጠረም ጊዜ እንደ ጨለመበት ሰው ሊያበሩለት አይደለም ከርሱ ብርሃን የስንዴ ቅንጣት ያህል ጥቂት ሰጣቸው እንጂ፡፡ ስለዚህም በሰው ላይ አበሩ፡፡

# ካህን

ወኵሎ እንከ ዘያስተርኢ ወዘኢያስተርኢ ፈጢሮ ወአስተናቢሮ አኮ ዘተመክሐ እንዘ ይብል ገበርኩ ወፈጸምኩ ወአዐርፍ እምነ ኵሉ ፃማ ዘረከበኒ።

እንግዲህ የሚታየውንና የማይታየውን ሁሉ ፈጥሮ አዘጋጅቶ ሠርቼ ፈጸምሁ ካገኘኝም ድካም ሁሉ አርፋለሁ ብሎ የተመካ አይደለም።

# ካህን

ውእቱሰ እምቅድመ ይኩን አእመረ ወእምቅድመ ይግበት ፈጸመ እምቅድመ ይግበር ጻድቃነ ወኃጥኣነ ሠናያነ ወእኩያነ፡፡

እርሱ ሳይደረግ ዐወቀ ሳይሠራም ፈጸመ ጻድቃንንና ኃጥኣንን፡፡ ክፉዎችንና በጎዎችን ሳይፈጥር፡፡

# ካህን

እቅድመ ይፍጥሮ ለእጓለ እመሕያው ገነተ አስተዳለወ ከመ ያብእ ውስቴታ ለዘአፍቀረ ወእሳተ ሲኦል አስተዳለወ ከመ ያብእ ውስቴታ ለዘጸልዐ።

ሰውን ሳይፈጥረው ገነትን አዘጋጀ የወደደውን ወደ እርስዋ ያገባ ዘንድ። የሲኦልንም እሳት አዘጋጀ የጠላውን ወደ እርስዋ ያገባ ዘንድ።

# ካህን

ብፁዕ ዘኀረዮ ወብፁዕ ዘሠምሮ ንለቡ እንከ ዘንተ ቃለ በዐቢይ ጥንቃቄ፡፡ ከመ ኢንባእ ውስተ ዐቢይ ባሕር ኀበ ተደመረ እሳት ወማይ ወኀበ ኢንክል ጸቢተ ወወፂአ እምኔሁ፡፡

የመረጠው ብፁዕ ነው የወደደውም ብፁዕ ነው፡፡ እንግዲህ ይህን ቃል በፍጹም መጠንቀቅ እናስተውል፡፡ እሳትና ውኃ ወደ ተቀላቀለበት ከርሱም ዋኝቶ መውጣት ወደማይቻለን ታላቅ ባሕር እንዳንገባ፡፡

# ካህን

ሕነሰ ንለቡ በከመ መሐሩነ ሐዋርያት በእንተ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ እንዘ ይብሉ፡፡ አብ ይነግር በእንተ ወልዱ ውእቱ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘዋሕድ ሎቱ፡፡

እኛስ የአብንና የወልድን የመንፈስ ቅዱስንም ነገር እናስተውል ሐዋርያት እንዳስተማሩን ለርሱ አንድ የሚሆን ኢየሱስ ክርስቶስ ልጁ እንደሆነ አብ የልጁን ነገር ይናገራል ብለው፡፡

# ካህን

ወወልድ ይነግር ከመ እግዚአብሔር አብ ዘወለዶ።
ወመንፈስ ቅዱስ ይዜኑ ዘከመ ወፅአ እምአብ
ወዘከመ ነሥአ እምወልድ።

ወልድም የወለደው እግዚአብሔር አብ እንደሆነ
ይናገራል። መንፈስ ቅዱስም ከአብ እንደ ወጣ
(እንደ ሠረፀ) ከወልድም እንደ ነሣ ይናገራል።

# ካህን

አሐቲ ክብር ወአሐቲ ሥልጣን ወ1ዱ ኀይል ዘኢይትከፈል። አልቦ አመክንዮ ወኢቡዓዴ ለኀበ ዚአሁ ህላዌ። አልቦ ሕፀት ወተውሳክ ለኀ ዚአሁ መለኮት።

አንዲት ክብር አንዲት ሥልጣን የማይለይ አንድ ኃይልም ነው። በባሕርዩ ዘንድ ምክንያት መለየትም የለም። በመለኮቱም ዘንድ ጉድለትና ጭማሪ የለም።

# ካህን

በከመ አውሥአ እግዚእነ ለአርዳኢሁ በእንተ ህላዌሆሙ እንዘ ይብል አልብነ ቀዳማዊ ወአልብነ ደኅራዊ አልብነ የማን ወአልብነ ፀጋም አልብነ ጠፈር ወአልብነ መሠረት ንሕነ ጠፈር ወንሕነ መሠረት፡፡

ጌታችን ለደቀ መዛሙርቱ ያነዋወራቸውን ነገር እንደ ነገራቸው፡፡ ተቀዳሚና ተከታይ ቀኝና ግራ የለብንም ብሎ፡፡ ጠፈር የለብንም መሠረትም፡፡ የለብንም፡፡ ጠፈርም፡፡ መሠረትም እኛ ነን፡፡

# ካህን

አልቦ ዘይክል ርእዮተነ ወአልቦ ዘየአምር ዘከመ እፎ ህላዌነ፡፡ ንሕነ ነአምሮ ለኵሉ ወንሕነ ንጤይቆ ለኵሉ ወንሕነ ንጤይቆ ለኵሉ አትቶ ለልጹቅ ወናቀርቦ ለርሑቅ፡፡ ንጸመም አውያተ ልሳን ከመ ዘኢይሰምዕ፡፡ ወነአምር ለኍኖሳሰ ልብ ዘውስጥ፡፡

እኛን ማየት የሚቻለው የለም፡፡ አነዋወራችንም እንደምን እንደ ሆነ የሚያውቅ የለም፡፡ እኛ ሁሉን እናውቀዋለን፡፡ ሁሉንም እኛ እንረዳዋለን፡፡ የቀረበውን እናርቀዋለን የራቀውንም እናቀርበዋለን፡፡ እንደማይሰማ ያንደበትን ጩኸት ቸል እንላለን፡፡ የውሳጣዊን ልብ ለኍኖሳስ (ሹክሹክታ) እናውቃለን፡፡

## ካህን

**አቡየ ወአነ ወመንፈስ ቅዱስ ዴዴ ወአንቀጽ ወማኅደር፡፡**

**አባቴ፡፡ እኔም መንፈስ ቅዱስም ደጅ በርና ማደሪያ ነን፡፡**

## ካህን

አቡየ ወአነ ወመንፈስ ቅዱስ ግርማ ወጼጋ ወሞገስ፡፡

አባቴ እኔም መንፈስ ቅዱስም ግርማና ጼጋ፤ ሞገስም ነን፡፡

## ካህን

አቡየ ወአነ ወመንፈስ ቅዱስ ፀሓይ ወብርሃን ወዋዕይ፡፡

አባቴ እኔም መንፈስ ቅዱስም ፀሓይና ብርሃን፤ ዋዕይም ነን፡፡

## ካህን

አቡየ ወአነ ወመንፈስ ቅዱስ እሳት ወነበልባል ወፍሕም፡፡

አባቴ እኔም መንፈስ ቅዱስም እሳትና ነበልባል ፍሕምም ነን፡፡

# ካህን

ከመዝ ህላዌነ ወከመዝ ፍጻሜነ ወመዋዕሊነ ኢኮነ ለዓለም ኣላ ለዓለም ወለዓለመ ዓለም፡፡ ዓዲ አልቦ ኀኍልቀኍ ወኢተፍጻሜት፡፡

አነዋወራችን እንዲህ ነው፤ ፍጻሜያችንም እንዲህ ነው ዘመናችንም ለዓለም አይደለም፤ ለዘላለመ ዓለም ነው እንጂ፡፡ ዳግመኛ ቍጥርና ፍጻሜ የለውም፡፡

## ዲያቆን

ሳዕለ ይኩን ሕሊናክሙ፡፡ በሰማይ የሀሉ ልብክሙ፡፡ አእምሩ ኀበ ዘትቀውሙ፡፡

አሳባችሁ ወደ ላይ ይሁን፡፡ ልቡናችሁ በሰማይ ይኑር፡፡ የምትቆሙበትን ዕወቁ፡፡

# ካህን

ርሑቀ መዓት ወብዙኀ ምሕረት ወጻድቅ አልቦ አመ ተዐገሠ ወአልቦ አመ ኢተዐገሠ፡፡ ይትዔገሦ ለዘአበሰ እስከ ይገብእ ወይትመየጥ ኀቤሁ፡፡

መዓቱ የራቀ ምሕረቱም የበዛ እውነተኛ የታገሠበት ጊዜ የለም፡፡ ያልታገሠበትም ጊዜ የለም፡፡ የበደለውን ፈጽሞ ወደርሱ እስኪመለስ ድረስ ይታገሣል፡፡

# ካህን

ወአመ ተምዐ ደምሰሰ ኃጥኣነ በማየ አይኅ፡፡ ወአትረፈ ሰማኒተ ነፍሳተ እለ ዐቀቡ ቃሎ ወምስለ አቡሆሙ  ዐቀመ ኪዳነ ጽድቅ ዘለዓለም፡፡  አምላከ አማልክት እሳት በላዒ እሳት ማሕየዊ፡፡

በተቈጣ ጊዜም ኃጥኣንን በጥፋት ውኃ አጠፋ፡፡ ቃሉን የጠበቁ ስምንት ሰዎችንም አተረፈ፡፡ ከአባታቸውም ጋራ ለዘላለም የሚሆን የእውነት ኪዳንን አጸና (አቆመ፡፡) የአማልክት አምላክ የሚያቃጥል እሳት የሚያድን እሳት፡፡

## ካህን

መኑ ስሙ ወመኑ ስመ ወልዱ ዘከመ እፎ ብሒሉ ወዘከመ እፎ ሀገሩ።

ስሙ ማነው የልጁስ ስም ማነው? ብሒሉ እንደምን ያለ ነው? ሀገሩስ እንደምን ያለ ነው?

## ካህን

መንበሩ በእሳት ክሉል ወማኅደሩ በማይ ጥፉር ወዲበ ተድባበ ቤቱ ሕንባበ ማይ ዘኢትይከዐው፡፡

ዙፋኑ በእሳት የተከበበ ነው፤ ማደሪያውም በውኃ የተታታ ነው፤ በቤቱም ዙሪያ ላይ የማይፈስ የውኃ መርገፍ አለ፡፡

# ካህን

ወእመንበሩ ይወፅእ ፀዓዕ ከመ ርስነ እሳት ውስጡ ብርሃን ዐቢይ ውስቴቱ ከመ ቀስተ ደመና ዘክረምት መብረቅ ዐውዱ።

ከዙፋኑም ብልጭልጭታ ይወጣል። ውስጡ እንደ ጋለ እሳት ነው። በውስጡ እንደ ክረምት ቀስተ ደመና ያለ ደገኛ ብርሃን አለ። ዙሪያው መብረቅ ነው።

# ካህን

ወእምገበዋቲሁ ለውእቱ መንበር 4ቱ እንስሳ ከመ ዘይጸውሩ መልዕልተ ርእሶሙ መንበረ ስፉሐ ዘኀብረ በረድ ፀዓዳ፡፡

ከዚ.ያም መንበር አጠገብ አራቱ እንስሳ ኀብሩ እንደ በረድ ነጭ የሆነ ሰፊ መንበር በራሳቸው እንደ ተሸከሙ ሆነው አሉ፡፡

# ካህን

ወእምዐውዱ ለውእቱ መንበር ኣወ4ቱ ካህናት ወቅድሜሆሙ ይሬእዩ ሥዕለ በግዑ ወልብሰ ዘንዝኀተ በደም ወለመጽሐፍ ኀቱም፡፡

በዚህም መንበር ዙሪያ ሀያ አራት ካህናት አሉ፡፡ በፊታቸውም የበግዑን ሥዕል፣ ደምን የተረጨች ልብስንም፣ የታተመ መጽሐፍንም ያያሉ፡፡

# ካህን

ወለያድዎ ለውእቱ መንበር ይሰግዱ 3ተ ጊዜ ለውእቱ ሥዕለ በግዑ ወለይእቲ ልብስ ዘንዝኀት በደም ወለመጽሐፍ ኅቱም ወጢስ ስብሐት ይመልዕ ውስተ ደብተራ መርጡል ወእምታሕቴሁ ለውእቱ መንበር ይነቅዕ ባሕር ዘ2ኤ ፍናዊሁ ባሕር ዘብርሃን ወባሕር ዘነፋስ፡፡

ይህንም መንበር በዞሩ ቀኍጥር  ለዚያ ለበጉ ሥዕልና በደም ለታለለች ለዚያች ልብስ ለታተመው መጽሐፍም 3 ጊዜ ይሰግዳሉ፡፡  በአዳራሹም ድንኳን የምስጋና ጢስ ይመላል፡፡  ከዚህም መንበር፡፡  በታች ጐዳናው ሁለት የሆነ ባሕር ይፈልቃል፡፡  የብርሃን ባሕርና የነፋስ ባሕር፡፡

# ካህን

አኮ ህየ ዘይሄሉ አምላከ አማልክት ወአኮ ህየ ዘይትጋባእ እግዚአ አጋዕዝት ይሄሉ በአፍኣ ወይትረከብ በውስጥ።

የአጋዕዝትም ጌታ በዚያ የሚወሰን አይደለም። በውጭ ይኖራል፤ በውስጥም ይገኛል።

# ካህን

ኢየሐውሩ ከመ ይርከብዎ ወኢትይኀጣእ ሶበ የኀሥሥዎ፡፡ ኢይትገሠሥ ሶበ ይእኀዝዎ እስመ ብዑድ ውእቱ እምሕሊና፡፡

ያገኙት ዘንድ አይሄዱም፡፡ በሹትም ጊዜ አይታጣም፡፡ በያዙት ጊዜ አይዳሰስም፤ ከሕሊና ልዩ ነውና፡፡

# ካህን

የዐቅብ ባዕለ ወምስለ ነዳይ ይሄሉ ያፈቅር ትሑተ ወይትሔየይ ዕቡየ፡፡ ያጻድቅ ለእመ ፈቀደ ወያድኅን ለእመ ሠምረ ይጸምም ከመ ዘኢይሰምዕ ያረምም ከመ ዘኢይሬኢ፡፡ ይትዔገሥ ከመ ዘኢየአምር ያጉነዲ ከመ ዘኢይሁብ፡፡

ባለጸጋውን ይጠብቃል፤ ከድሃም ጋራ ይኖራል፤ ትሑቱን ሰው ይወዳል፤ ትዕቢተኛን ግን ቸል ይላል፡፡ ቢፈቅድ ያጸድቃል፤ ቢወድም ያድናል፤ እንደማይሰማ ቸል ይላል፤ እንደማያይ ዝም ይላል፤ እንደማያውቅ ይታገሣል፡፡ እንደማይሰጥ ያዘገያል፡፡

# ካህን

አምላክ አማልክት ወእግዚአ አጋዕዝት እግዚኦሙ ለአዚዛን ዘሎቱ ይሰግዱ መላእክት ወሊቃነ መላእክት፡፡

የአማልክት አምላክ የአጋዕዝትም ጌታ የጽኑዓን ጌታቸው መላእክትና ሊቃነ መላእክት የሚሰግዱለት እርሱ ነው፡፡

# ካህን

አኮ ዘይሰግዱ ሎቱ በነጽሮ አሳ ለመንበሩ ይሰግዱ ወለዕበዩ ይገንዩ፡፡ ወይሠሩ ውስተ ትርብዕተ ዓለም ለገቢረ ኵሉ ፈቃዱ፡፡

በማየት የሚሰግዱለት አይደለም ለመንበሩ ይሰግዳሉ ለጌትነቱም ይገዛሉ እንጂ፡፡ ፈቃዱን ሁሉ ለመሥራት ወደ አራቱ ማዕዘነ ዓለም ይወጣሉ፡፡

# ካህን

ሱራፌል ወኪሩቤል ይጸርሑ ወይብሉ ቅዱስ እግዚአብሔር ቅዱስ ኀያል፡፡ አኮ በኀይለ ትዕቢት ቅዱስ ሕያው ዘኢይመውት ዘሞተ በእንተ ፍቅረ ሰብእ፡፡

ሱራፌልና ኪሩቤል በትዕቢት ኀይል ያይደለ ጮኸው ቅዱስ እግዚአብሔር ቅዱስ ኀያል የማይሞት ስለ ሰው ፍቅር የሞተ ቅዱስ ሕያው ይላሉ፡፡

# ካህን

ወእምአሐቲ መዝገብ ዘእምእስትንፋሰ አፉሁ ይሠርፃ ወያሕመለምላ ነፍሳት እለ ይትወለዳ ውስተ ዓለም፡፡

በዓለም የሚወለዱ ነፍሳት ከአፉ እስትንፋስ ከተገኘ ች ከአንዲት መዝገብ ይወጣሉ ይለመልማሉም፡፡

# ካህን

ወበአሐቲ መዝገብ ይትወደይ ሥርናይ ዘአልቦ ክርዳድ፡፡ ህየ ይሠየማ ወህየ ይትዐቀባ ነፍስቲሆሙ ለጻድቃን እስከ አመ ይፈድዮ ለኵሉ በከመ ምግባሩ፡፡

በአንዲትም መዝገብ ክርዳድ የሌለበት ስንዴ ይገባል፡፡ የጻድቃን ነፍሶቻቸው በዚያ ይኖራሉ በዚያም ይጠበቃሉ፡፡ ለሁሉ እንደ ሥራው እስኪከፍለው ድረስ፡፡

# ካህን

ህየ ሀሎ ፍሥሓ ወሐሤት፡፡ ህየ ሀሎ አዳም አባ ኵሉ ህየ ሀለው አቤል ወሴት ወኄኖስ አርእስተ አበው ምስለ ኵሉ ፍሬሆሙ፡፡

ከዚያ ፍሥሓ ሐሤትም አለ፡፡ የሁሉ አባት አዳም ከዚያ አለ፡፡ የአበው አርእስቶች አቤል ሴት ሄኖስም ከፍሬያቸው ጋራ በዚያ አሉ፡፡

# ካህን

ህየ ሀለው አብርሃም ይስሐቅ ወያዕቆብ ዐርካነ እግዚአ፡፡ ህየ ሀለው ሙሴ ወአሮን ካህናት፡፡ ህየ ሀለዉ ሙሴ ወአሮን ካህናት፡፡ ህየ ሀለው ዳዊት ወሕዝቅያስ ወኢዮስያስ ወኰሎሙ ርቱዓነ ሃይማኖት ነገሥት፡፡

የጌታ ወዳጆች አብርሃምና ይስሐቅ ያዕቆብም ከዚያ አሉ፡፡ ሙሴና አሮን ካህናት ከዚያ አሉ፡፡ ዳዊትና ሕዝቅያስ ኢዮስያስም ሃይማኖታቸው የቀና ነገሥታትም ሁሉ፡፡

# ካህን

ህየ ሀለዉ ነቢያት ምስለ ትንቢቶሙ፡፡ ህየ ሀለዉ አርድእተ ዋሕድ ዘመራኁት ውስተ እደዊሆሙ እንዘ ይነብሩ አንቀጸ ከመ ያብኡ ውስቴታ ዘፈቀዱ፡፡

ነቢያት ከትንቢታቸው ጋራ ከዚያ አሉ፡፡ መክፈቻዎች በእጆቻቸው የተያዙ የዋሕድ ደቀ መዛሙርት ከዚያ አሉ፡፡ በበር ተቀምጠው የወደዱትን ወደ እርስዋ ያገቡ ዘንድ፡፡

# ካህን

ህየ ሀለዉ ሊቃነ ጳጳሳት ጳጳሳት ወኤጲስቆጶሳት ቀሳውስት ወዲያቆናት እለ አዕለሙ ምግቦሙ ዘተአመኖሙ እግዚአሙ።

የጳጳሳት አለቆ ጳጳሳትና ኤጲስቆጶሳት ቀሳውስትና ዲያቆናት ጌታቸው ያመናቸው ሹመታቸውን የመለሱ ከዚያ አሉ።

# ካህን

ህየ ሀለዉ ሰማዕት እንዘ ይበርቅ አክሊሎሙ ምስብዒተ እምፀሓይ፡፡ ህየ ሀለዉ ጻድቃን በትዕግሥቶሙ፡፡

ሰማዕታት ዘውዳቸው ከፀሓይ ሰባት እጅ እያበራ ከዚያ አሉ፡፡ ጻድቃን በትዕግሥታቸው ከዚያ አሉ፡፡

# ካህን

ህየ ሀለዉ እድ ወአንስት ትዕይንተ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ እለ አልቦሙ ኍልቍ፡፡ ህየ ይነብሩ በትፍሥሕት ወበሐሤት እስከ አመ ይትሜጠዉ ምክዕቢተ እምቀዳሚ፡፡

ቍጥር የሌላቸው የአብና የወልድ የመንፈስ ቅዱስም ሠራዊት ወንዶችም ሴቶችም ከዚያ አሉ፡፡ በፍጹም ደስታ በሐሤትም ከዚያ ይኖራሉ፡፡ ከቀድሞው ይልቅ ዕፅፍ ርስታቸውን እስኪቀበሉ ድረስ፡፡

# ካህን

ህየ ይነብሩ ጻድቃን በክብር የዋሃን በክብር ወኅሩያን በክብር፡፡ ንስእለከ እግዚኦ ኪያከ መሠጥወ ኪያከ ሰማዔ ወኪያከ ረዳኤ፡፡

ጻድቃን በክብር የዋሃን በክብር የተመረጡትም በክብር ከዚያ ይኖራሉ፡፡  አቤቱ የምትመልስ አንተን የምትሰማ አንተን የምትረዳ አንተን እንለምንሃለን፡፡

# ካህን

ናስተበቍዐከ እግዚኦ በእንተ እለ ኖሙ ወፈለሱ እምዝንቱ ዓለም ኅላፊ ወተሠልጠ ሥልጣነ ሞተ ላዕሌሆሙ ወተከድኑ ታሕተ ከፈር።

አቤቱ ከዚህ ከሚያልፍ ዓለም ተለይተው ስለ ሞቱና ስለ ተሰደዱ የሞት ሥልጣን ስለ ሠለጠነባቸውና ከመቃብር በታች ስለ ተከደኑ ሰዎች እንማልድሃለን።

## ካህን

ስእለከ እግዚኦ ወናስተበቍዐከ ከመ ትጸውዖሙ ውስተ ትንሣኤ ክብር እንዘ ታነሥአ ሥጋ እኀቢርከ ዘምስለ መንፈስ።

አቤቱ ሥጋን ከመንፈስ ጋራ አንድ አድርገህ ስታስነሣ በክብር ወደ መነሣት ትጠራቸው ዘንድ እንለምንሃለን እንማልድሃለን።

## ካህን

እንዘ ተዐሲ ዕሴተ ሠናየ ዘዐይን ኢርእየ ወእዝን አ ሰምዐ ውስተ ልበ ሰብእ ዘኢተሐለየ ዘአስተዳሎከ በወልድከ ኢየሱስ ክርስቶስ ለዓለመ ዓለም፡፡

ዓይን ያላየውን ጆሮ ያልሰማውን በሰው ልቡናም ያልታሰበውን በልጅህ በኢየሱስ ክርስቶስ ያዘጋጀኸውን በጎ ዋጋ እየሰጠህ ለዘላለሙ፡፡

## ዲያቆን

በእንተ ብፁእ ወቅዱስ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ወኤጲስ ቆጶሳት እንዘ የአኲቱከ በጸሎቶሙ ወበስእለቶሙ እስጢፋኖስ ቀዳሜ ሰማእት ዘካርያስ ካህን ወዮሀንስ መጥምቅ።. . . እስከ ተፈጸሜቱ።

ብፁእ ቅዱስ ስለሚሆን ስለ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ስለ አባ ___ ብፁእም ስለሚሆን ስለ አባ ____ በጸሎታቸውና በልመናቸው ሲያመሰግኑህ የሰማእታት መጀመሪያ እስጢፋኖስ። ካህኑ ዘካርያስና መጥምቁ ዮሀንስ። . . .

For the sake of the blessed and holy patriarch Abba… and the blessed Archbishop Abba… while they yet give thee thanks in their prayer and in their supplication: Stephen the first martyr, Zacharias the priest and John the Baptist…

## ንፍቅ ካህን

**ልዩ ሦስት የምትሆን አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ሆይ የሚፋቀሩ የክርስቶስ ወገኖች የሚሆኑ ሕዝብህን በሰማያውያንና ምድራውያን በረከት ባርክ......**

O Holy Trnity, Father and Son and Holy Spirit, bless Thy people, Christians beloved, with blessings heavenly and earthly…

በእኛ ላይም የመንፈስ ቅዱስን ጸጋ ላክ የቅድስት ቤተ ክርስቲያንህንም ደጆች በምህረትና በሃይማኖት እንዲከፈቱ አድርግልን።

እስከ መጨረሻው ህቅታም ድረስ ልዩ ሶስትነትህን ማመንን ፈጽምልን

And send upon us the grace of the Holy Spirit, and make the doors of Thy holy church open unto us in mercy and in faith; and perfect unto us the faith of the holy Trinity unto our latest breath.

ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ የታመሙ ወገኖችህን ጐብኝ፤ መንገድ የሄዱትንና እንግዶች የሆኑትን አባቶቻችንን ወንድሞቻችንን መርተህ በሰላምና በጤና ወደ ቤታቸው መልሳቸው። የሰማዩን ነፋስ ባርክ። ዝናሙንም በዚህች ዓመት የሚያፈራውን የምድሩን ፍሬ እንደቸርነትህ ባርክ። ዘወትር ተድላንና ደስታን አድርግ

O my Lord Jesus Christ, visit the sick of Thy people; heal them; and guide our fathers and our brethren who have gone forth and become strangers: bring them back to their dwelling-places in peace and in health. Bless the airs of heaven, and the rains and the fruits of the earth of this year, in accordance with Thy grace, and make joy and gladness prevail perpetually on the face of the earth.

ሰላምንም አጽናልን ሁል ጊዜ ለእኛ በጎ ነገርን ሊያደርጉልን ጽኑኣን የሚሆኑ የነገስታቱን ልቡና መልስ። በቅድስት ቤተ ክርስቲያንህ ሁል ጊዜ ለሚሰበሰቡ ለቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ፍቅርን ስጥ። ለሁሉም ለእያንዳንዱ በየስማቸው ኃያላን በሚሆኑ በነገስታቱ ፊት ሰላምን አብዛላቸው

And establish for us Thy peace. Turn the hearts of mighty kings to deal kindly with us always. Grant peace to the scholars of the church who are continually gathered in Thy holy church; to all, to each by their several names; in the presence of powerful kings, O our God, increase Thy peace.

አምላካችን ሆይ በቀናች ሃይማኖት ሆነው የአንቀላፉትንና ያረፉትን የአባቶቻችንንና የእናቶቻችንን የወንድሞቻችንን፤ የእህትቶቻችንንም ነፍስ አሳርፍ

Rest the souls of our fathers and our brothers and our sisters who have fallen asleep and gained their rest in the right faith.

አምላካችን ክርስቶስ በኢየሩሳሌም ሰማያዊት ዋጋቸውን ይከፍላቸው ዘንድ እጣንና ቊርባን ወይንና ሜሮን ዘይትም መጋረጃም የንባብ መጻህፍቶችን የቤተ መቅደስንም ንዋያት በመስጠት የሚያገለግሉትንም ባርክ

And bless those who give gifts of incense, and bread and wine, and ointment and oil, and hangings and reading books and vessels for the sanctuary, that Christ our God may give them their reward in the heavenly Jerusalem.

ይቅርታን ያገኙ ዘንድ ከእኛ ጋራ የተሰበሰቡትንም ሁሉ አምላካችን ክርስቶስ ሆይ ይቅር በላቸው። በሚያስፈራና በሚያስደነግጥ በመንበርህ ፊት ምጽዋት ያመጡትን ሁሉ ተቀበላቸው

And all them that are assembled with us to entreat for mercy: Christ our God have mercy upon them: and all them that give alms before Thy awful and terrifying throne, receive.

የተጨነቀችዩቱንም ነፍስ አሳርፍ፤ በሰንሰለት የታሰሩትን በስደትና በምርኮ ያሉትንም። መሪር በሆነ አገዛዝ የተያዙትንም አምላካችን ሆይ በቸርነትህ አድናቸው

And comfort every straitened soul, them that are in chains and them that are in exile or captivity. And them that are held in bitter servitude: our God, deliver them in Thy mercy.

መምህራችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ወዳንተ በምንማልድበት ጊዜ እንድናስባቸው ያዘዙንን ሁሉ በሰማያዊት መንግስትህ አስባቸው። ኃጥእ ባርያህን እኔንም አስበኝ። አቤቱ ሕዝብህን አድን ርስትህንም ባርክ። ጠብቃቸው። እስከ ዘላለምም ከፍ ከፍ አድርጋቸው።

And all them that have entrusted it to us to remember them in our supplications to Thee: O our Master Jesus Christ, remember them in Thy heavenly kingdom, and remember me, Thy sinful servant.

## ዲያቆን

**መሐርሙ እግዚኦ ወተሣሃሎሙ ሊቃነ ጳጳሳት፤ ጳጳሳት ኤጲስ ቆጶሳት ቀሳውስት ወዲያቆናት ወኵሎሙ ሕዝበ ክርስቲያን**

**አቤቱ የጳጳሳት አለቃ ጳጳሳቱን፤ ኤጲስ ቆጶሳቱን፤ ቀሳውስቱንና ዲያቆናቱን፥የክርስቲያን ወገኖችን ሁሉ ማራቸው፤ ይቅርም በላቸው።**

Lord pity and have mercy upon the patriarchs, archbishops, bishops, priest, deacons and all the Christian people.

## ካህን

እግዚአብሔር አብ ዘፈነወ ወልዶ ዋሕደ ከመ ይኅድር ውስተ ሥጋ ወለት እንተ ኢተአምር ምተ ተዐቍረ ውስተ ማኅፀን ሠዓሌ ሕፃናት እንዘ ኢትይጋባእ ተሰብአ እንዘ አምላክ ውእቱ ወተወልደ

እግዚአብሔር አብ አንድ ልጁን የሰደደው ባል በማታውቅ በወለት ሥጋ ያድር ዘንድ ነው፡፡ ሕፃናትን የሚፈጥር እርሱ ሳይወሰን በማኅፀን ተወሰነ፡፡

## ካህን

እንዘ እሳተ መለኮት ውእቱ ተሐዕነ አኮ በትርሲት ወክብር አላ ከመ ውሉደ ነዳያን ልሐቀ በዐቢይ ተግሣጽ እንዘ ይትኤዘዝ ለአዝማዲሁ፡፡

አምላክ ሲሆን ሰው ሆነ እሳተ መለኮትም ሲሆን ተወለደ አደገ በጌጥና በክብር አይደለም፡፡ እንደ ድሆች ልጆች ለዘመዶቹ እየታዘዘ በብዙ ተግሣጽ አደገ እንጂ፡፡

# ካህን

አድነነ ርእሶ ከመ ያጥምቆ ገብር እንዘ ንጹሕ ውእቱ እምኃጢአት፡፡ ገብረ ተእምራት እስከ ረሰየ ማየ ወይነ ወእስከ አጽገበ አእላፈ ብዙኃነ በገዳም፡፡

ከኃጢአት ንጹሕ ሲሆን ባርያ ያጠምቀው ዘንድ ራሱን አዘነበለ፡፡ ውኃን ጠጅ እስከማድረግ ድረስ ተኣምራት አደረገ በምድረ በዳም ለብዙ ሰዎች እስኪያጠግብ ድረስ፡፡

## ሕዝብ

ተዘከረነ እግዚኦ በውስተ መንግሥትከ ተዘከረነ እግዚኦ ኦ ሊቅ በውስተ መንግሥትከ ተዘከረነ እግዚኦ በውስተ መንግሥትከ በከመ ተዘከርኮ ለፈያታዊ ዘየማን እንዘ ሀሎከ ዲበ ዕፀ መስቀል ቅዱስ

አቤቱ በመንግሥትህ አስበን ሊቅ ሆይ አቤቱ በመንግሥትህ አስበን ሊቅ ሆይ አቤቱ በመንግሥትህ አስበን ቅዱስ በሚሆን በዕፀ መስቀል ላይ ሳለህ ፈያታዊ ዘየማንን እንዳሰብከው አቤቱ በመንግሥትህ አስበን

Remember us, Lord, in Thy kingdom; remember us, Lord, Master, in Thy kingdom; remember us, Lord, in Thy kingdom, as Thou didst remember the thief on the right hand when Thou was on the tree of the Holy Cross.

## ካህን

ኦ ዘአሜሃ ትውልድ ፆረ አዕይንቲ ሆሙ ከመ ኢይርአይዎ ደንቅወ እዘኒ ሆሙ ከመ ኢይስምዕዎ፡፡ ወተጸለለ ልባሙ ከመ ኢያእምርዎ አምሰልዎ ሰብአ ለዘየኀድግ ኃጢአት ወኰነንዎ ለመኰንነ መኳንንት፡፡

ወዮ በዚያ ጊዜ የነበሩ ትውልድ እንዳያዩት ዓይናቸው ታወረ፡፡ እንዳይሰሙት ጆሮዋቸው ደነቆረ፡፡ እንዳያውቁትም ልቡናቸው ተሸፈነ፡፡ ኃጢአትን ይቅር የሚለውን እርሱን ዕሩቅ ብእሲን አስመሰሉት፡፡ በመኳንንት ላይ የሚፈርደውን ፈረዱበት፡፡

ካህን

ወኅረየ እምውስቴቶሙ ፲ወ፪ተ ሐዋርያተ ወአንሶሰወ ምስሌሆሙ ወአርአዮሙ ሥርዓተ ምሥጢር ዘቊርባን፡፡

ከእነሱም ወገን አሥራ ሁለት ሐዋርያትን መረጠ ከነርሱም ጋራ ተመላለሰ፡፡ የቊርባን ምሥጢረ ሥርዓትንም አሳያቸው፡፡

ዲያቆን

አንሥኡ እደዊክሙ ቀሳውስት።

ቀሳውስት እጆቻችሁን አንሡ።

ሕዝብ

ነአምን ከመ ዝንቱ ውእቱ በአማን ነአምን።

እናምናለን ይህ እርሱ እንደ ሆነ በእውነት እናምናለን።

## ሕዝብ

አሜን አሜን አሜን ነአምን ወንትእመን
ንሴብሐከ ኦ እግዚእነ ወአምላክነ ከመ ዝንቱ
ውእቱ በአማን ነአምን፡፡

አሜን አሜን አሜን እናምናለን
እንታመንማለንም ጌታችንና አምላካችን ሆይ
እናመሰግንሃለን፡፡ ይህ እርሱ እንደ ሆነ
በእውነት እናምናለን፡፡

አሜን አሜን አሜን፡፡

# ካህን

አሜሃ ኢየሱስ ደቤ ተከዘት ነፍስየ እስከ ለሞት ዘውእቱ መስተፍሥሐ ትኩዛን፡፡

ያን ጊዜ ኢየሱስ ነፍሴ እስከ ሞት ደርሳ አዘነች አለ፡፡ ይኸውም ያዘኑትን ደስ የሚያሰኛቸው ነው፡፡

## ካህን

በይእቲ ሌሊት አኀዝዎ፡፡ ወጸቢሖ ረበናተ አይሁድ ወሊቃነ ካህናት ምስለ ጰላጦስ መስፍን ነበሩ ዐውደ ለኲንኖቱ፡፡

በዚያች ሌሊት ያዙት፡፡ በነጋም ጊዜ የአይሁድ መምህሮችና የካህናት አለቆች ከገዢ ከጲላጦስ ጋራ ሊፈረዱበት በአደባባይ ተቀመጡ፡፡

# ካህን

አሰርዎ ድኅሪተ ከመ ሠራቂ ወተለዎሙ
በፍቅር ከመ በግዕ የዋህ ነበሩ ዐውደ
ለኰንኖቱ አቀምዎ ቅድሜሆሙ ለዘሎቱ
ይቀውሙ ሠራዊተ መላእክት በፍርሀት
ወበረዓድ፡፡

እንደ ሌባ የኋሊት አሠሩት፤ እንደ የዋህ በግ
በፍቅር ተከተላቸው፤ ሊፈርዱበት በአደባባይ
ተቀመጡ፡፡ የመላእክት ሠራዊት በመፍራት
በመንቀጥቀጥ የሚቆሙለትን በፊታቸው
አቆሙት፡፡

## ካህን

ገብር እኩይ አጽንዐ እዴሁ ከመ ይጽፍዖ ለዘኢአበሰ ሎቱ ያደንኑ ሎቱ ከመ ይስግዱ በትዕቢት ለዘሎተ ይሰግዱ ሊቃነ መላእክት በዐቢይ ድንጋፄ፡፡

ክፉ ባርያ እርሱን ያልበደለውን ይጸፋው ዘንድ እጁን አጸና፡፡ የመላእክት አለቆች በፍጹም ድንጋፄ ለሚሰግዱለት ለርሱ በትዕቢት ይሰግዱ ዘንድ አጐነበሱለት፡፡

## ካህን

**አስተቀጸልዎ አክሊለ ዘሦክ ለርእሰ ሕይወት ሰለብዎ አልባሲሁ ወአልበስዎ ከለሜዳ ዘለይ ለዘይትዐጸፍ ብርሃነ ከመ ልብስ፡፡**

**የሕይወትን ራስ የሾህ ዘውድ ደፉበት፡፡ ብርሃንን እንደ ልብስ የሚጐናጸፈውን ልብሱን ገፈው ቀይ ግምጃ አለበሱት፡፡**

## ካህን

ወወሰድዎ ኀበ ይሰቅልዎ ብሔረ ዘስሙ ቀራንዮ አጸርዎ መስቀሎ ወደክመ ኢየሱስ በጸዊረ መስቀሉ ወሐፈወ እስመ ክቡድ ውእቱ፡፡

ወደሚሰቅሉበት ስሙ ቀራንዮ ወደሚባል አገር ወሰዱት፡፡ መስቀሉን አሸከሙት፡፡ ኢየሱስም መስቀሉን በመሸከም ደከመ ወዛ ከባድ ነውና፡፡

## ካህን

ኦ አፍ ዘነፍሐ ውስተ ገጹ ለአዳም መንፈሰ ሕይወት ሰረበ ብሒዐ ወከርቤ ቱሱሐ ዘምስለ ሐሞት፡፡

በአዳም ፊት የሕይወትን መንፈስ እፍ ያለ አፍ ወዮ ከሐሞት ጋራ የተቀላቀለ መጣጣንና ከርቤን ጠጣ፡፡

## ካህን

ገዐረ ኢየሱስ በሕማሙ ወጸርሐ ኀበ አቡሁ አድኀነ ርእሶ ወወፅአት መንፈሱ ሶቤሃ፡፡

ኢየሱስ በሕማሙ (በመከራው) አሰምቶ ጮኸ፤ ወደ አባቱ ጮኸ፡፡ ራሱን ዘለስ አደረገ፤ ያን ጊዜ ነፍሱ ወጣች (ተለየች፡፡)

## ካህን

ረገዝዎ ገቦሁ በኵናት ጸሊም በዘሎቱ
አንሐቡ፤ አውረድዎ እምዕፅ ወወደይዎ ውስተ
መቃብር አኮ ኀበ መቃብረ ዚአሆሙ
ዘወደይዎ አላ አፍኣ ኀበ መቃብረ እንግዳ
ዘ3ቱ እመቱ ወኀተምዎ በእብን፡፡
ለእርሱ ብለው ባሠሩት በጥቍር ጦር ጐኑን
ወጉት፡፡ ከእንጨት አውርደው በመቃብር
አኖሩት፡፡ በነርሱ መቃብር ያኖሩት
አይደለም፡፡ ከከተማ ውጭ ሦስት ክንድ
በሚሆን በስደተኛ መቃብር ነው እንጂ፤
በደንጊያም ገጠሙት፡፡

## ካህን

ወእንዘ ሀሎ ህየ ጸርሐ ኀበ አዳም ገብሩ
ወኀበ ኵሎሙ ደቂቁ።

በዚያም ሳለ ወደ ባርያው ወደ አዳም
ወደ ልጆቹም ሁሉ ጮኸ።

ካህን

እግዚአብሔር ምስለ ኵልክሙ፡፡

እግዚአብሔር ከሁላችሁ ጋራ ይሁን፡፡

ይ.ሕ.

ምስለ መንፈስከ፡፡

ከመንፈስህ ጋራ፡፡

ይ.ካ.

አእኵትዎ ለአምላክነ፡፡

አምላካችንን አመስግኑት፡፡

ይ.ካ.

አእኰትዎ ለአምላክነ።

አምላካችንን አመስግኑት።

ይ.ሕ.

ርቱዕ ይደሉ።

እውነት ነው ይገባል።

ይ.ካ.

አልዕሉ አልባቢክሙ፡፡

ልቡናችሁን ከፍ ከፍ አድርጉ፡፡

ይ.ሕ.

ብነ ኀበ እግዚአብሔር አምላክነ፡፡

አቡነ ዘበሰማያት፡፡ 3ተ ጊዜ፡፡

አንተ ውእቱ እግዚእነ ወአምላክነ፡፡

በአምላካችን በእግዚአብሔር ዘንድ አለን

የሰማይ አባታችን ሆይ 3 ጊዜ፡፡

ጌታችንና አምላካችን አንተ ነህ፡፡

# ካህን

ወሶበ ይቤ ዘንተ ለአዳም ገብሩ ተፈሥሐ አዳም ወወፅአ ምስለ ኵሎሙ ደቂቁ ወቦአ ውስተ ሀገር ቅድስት በከመ ተብህለ።

ይህንን ለባርያው ለአዳም በተናገረ ጊዜ አዳም ደስ አለው። ከልጆቹ ሁሉ ጋራ ወጥቶ ወደ ቅድስት አገር ገባ። እንደ ተነገረ።

## ካህን

ወካዕበ ከመ ያርኢ ስብሐተ ትንሣኤሁ አሥረቀ ንስቲተ መለኮቶ ወአውደቆሙ ለእለ የዐቅቡ ዝኀሮ፡፡

ዳግመኛም የትንሣኤውን ክብር ይገልጽ ዘንድ ጥቂት ብርሃኑን አወጣ መቃብሩን የሚጠብቁትንም ጣላቸው፡፡

# ካህን

ወተንሥአ በሣልስት ዕለት በዕለት ጥይቅት ቦአ ኀበ ህለው አርዳኢሁ ወአርአዮሙ ርግዘተ ገቦሁ ወቅንዋተ እደዊሁ፡፡ ወነበረ ምስሌሆሙ እንዘ ይሜህሮሙ በእንተ መንግሥተ ሰማያት፡፡

በሦስተኛዪቱ ቀን ተነሣ፡፡ በተረጋገጠች ቀን ደቀ መዛሙርቱ ወዳሉበት ገብቶ የጐኑን መወጋት የእጆቹን መቸንከር አሳያቸው፡፡ የመንግሥተ ሰማያትን ነገር እያስተማራቸው ከነርሱ ጋራ ኖረ፡፡

# ካህን

ወበ$ ዕለት ዐርገ ሰማያተ ኀበ አብ ዘፈነዎ፡፡ ወካዕበ ይመጽእ አኮ ዘይመጽእ በትሕትና፡፡ አላ በስብሐተ አብ ዘወልዶ በመፍርህ ሥልጣን ምስለ መላእክቲሁ ቅዱሳን በደመና ሰማይ፡፡

በአርባኛውም ቀን ወደ ላከው አብ ወደ ሰማይ ዐረገ፡፡ ዳግመኛም ይመጣል በትሕትና የሚመጣ አይደለም በወለደው በአብ ጌትነት በሚያስፈራ ሥልጣን ከቅዱሳን መላእክቶቹ ጋራ በሰማይ ደመና ነው እንጂ፡፡

ይ.ሕ.

ንዜኑ ሞተከ እግዚኦ ወትንሣኤከ ቅድስት ነአምን ዕርገተከ ወዳግመ ምጽአተከ ንሴብሖከ ወንትአመነከ ንስእለከ ወናስተበቍዐከ ኦ እግዚእነ ወአምላክነ።

አቤቱ ሞትህን ቅድስት ትንሣኤህንም እንናገራለን። ዕርገትህን ዳግመኛም መምጣትህና እናምናለን እናመሰግንሃለን እናምንሃለንም። ጌታችንና አምላካችን ሆይ እንለምንሃለን እንማልድሃለንም።

ካህን

ለተኩን እግዚኦ ምሕረትከ ላዕሌነ ወበከመ ላዕሌከ ተወከልነ፡፡

አቤቱ ይቅርታህ ለኛ ትደረግልን፡፡ በአንተ እንዳመነ መጠን፡፡

ይ.ሕ.

በከመ ምሕረትከ አምላክነ ወአኮ በከመ አበሳነ፡፡ 3ተ ጊዜ፡፡

አምላካችን ሆይ እንደ ቸርነትህ ነው እንጂ እንደ በደላችን አይደለም፡፡ 3 ጊዜ፡፡

# ካህን

ወተጋብኦትነ ይኩን በከመ ተጋብኦቶሙ ለአርዳኢከ አንተ ዘእሙንቱ ወአንተ ዘለነ፡፡ አንተ ዘአሜሃ ወአንተ ዘይእዜ፡፡

መሰብሰቢያችንም እንደ ደቀ መዛሙርትህ ስብሰብ ይሁን፡፡ የነርሱ ፈጣሪ አንተ ነህ፡፡ የእኛም አንተ ነህ፡፡ ያን ጊዜ የነበርህ አንተ ነህ ዛሬም ያለህ አንተ ነህ፡፡

# ካህን

ዚአከ ሰማያት ወዚአከ ምድር ዚአከ ጻድቃን ወዚአከ ኃጥኣን፡፡ እስመ አንተ ትትዐጾ አእሳፈ ኃጢአት፡፡ ወታቀውም ውኁደ ተክለ ጽድቅ ወትፈቅድ ምክንያት ለድኂን፡፡

ሰማያት ያንተ ናቸው ምድርም ያንተ ናት፡፡ ጻድቃን ያንተ ናቸው ኃጥኣንም ያንተ ናቸው፡፡ ብዙውን ኃጢአት ይቅር ትላለህና፡፡ ጥቂቱን ስለ ጽድቅ ታቆማለህ፡፡ ለመዳንም ምክንያት ትሻለህ፡፡

## ይ.ዲ.

በኵሉ ልብ ናስተብቍዖ ለእግዚአብሔር አምላክነ ኅብረተ መንፈስ ቅዱስ ሠናየ ከመ ይጸግወነ፡፡

በፍጹም ልብ አምላካችንን እግዚአብሔርን እንማልደው፡፡ ያማረ የመንፈስ ቅዱስን አንድነት ይሰጠን ዘንድ፡፡

## ይ.ሕ.

በከመ ሀሎ ህልወ ወይሄሉ ወትውልደ ትውልድ ለዓለመ ዓለም፡፡

በፊት እንደ ነበረ ለዘላለሙ ለልጅ ልጅ ይኖራል፡፡

## ካህን

ደሚረከ ተህቦሙ ለኵሎሙ ለእለ ይነሥኡ እምኔሁ ይኩኖሙ ንጽሐ ለእለ ይነሥእዎ ወኅሩየ ለእለ ይትሜጠውዎ፡፡ ከመ በርእየቱ የዓይ ሦከ ኃጢአት ትትመሳኅ አበሳ ወትደምሰስ ጌጋይ ወትንሐይ ነፍስ እምአበሳሃ ፍጹመ፡፡

ከርሱ ለሚቀበሉ ሁሉ አንድ አድርገህ ስጣቸው፡፡ ለሚቀበሉት ንጽሕን ይሆናቸው ዘንድ፡፡ ለሚቀበሉትም መመረጫ ይሆናቸው ዘንድ፡፡ እርሱን በማየት የኃጢአት እሾህነት ይቃጠል ዘንድ አበሳ ትነቀል ዘንድ በደልም ትጠፋ ዘንድ ነፍስም ከበደልዋ ፈጽማ ታርፍ ዘንድ፡፡

# ካህን

ይትቀፈጽ ኅኖኀተ ብርሃን ወይትረኀው አናቅጸ ስብሐት ወይትፈኖ መንፈስ ቅድሱ ወሕያው እመካን ዘሥውር ህላዌሁ ይረድ ወይምጻእ፡፡ ወያንጽብርቅ ዲበ ዝንቱ "እማሬ" ኅብስት ወይኩን ሥጋ ክርስቶስ አምላክነ፡፡

የብርሃን ደጅ ይገለጥ፡፡ የብርሃን በርም ይከፈት፡፡ ቅዱስና ሕያው የሚሆን መንፈስም ይላክ፡፡ አናኗሩ ከተሠወረ ቦታ ይውረድ ይምጣም፡፡ በዚህም ኅብስት "እማሬ"ላይ ያብራ የአምላካችንን የክርስቶስን ሥጋ ይሁን፡፡

# ካህን

ወይትወለጥ ጣዕሙ ለዝንቱ “እማሬ” ጽዋዕ ወይኩን ደመ ክርስቶስ አምላክነ፡፡

የዚህ “እማሬ” የጽዋው ጣዕም ተለውጦ የአምላካችንን የክርስቶስን ደም ይሁን፡፡

ይ.ሕ.

አሜን እግዚኦ መሐረነ

እግዝኦ መሐከነ

እግዚኦ ተሣሃለነ፡፡

አሜን አቤቱ ማረን

አቤቱ ራራልን

አቤቱ ይቅር በለን፡፡

# ካህን

ወምስለ ኵሉ ፍጻሜ ማኅበራ ለቅድስት አሐቲ እንተ ላዕለ ኵሉ ቤተ ክርስቲያን መሐሮሙ ወተሣሃሎሙ ወፈድፋደሰ ለእለ ኀረዩ ንዴተ ዚአየ ለመልእክተ ዝንቱ ምሥጢር መሐሮሙ ወተሣሃሎሙ ለዓለም ዓለም አሜን፡፡

ከሁሉ በላይ የምትሆን ያንዲት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን የማኅበርዋን ፍጻሜ ማራቸው፡፡ ይቅርም በላቸው ይልቁንም ይህንን ምሥጢር ለማገልገል የእኔን ንዴት የመረጡትን ማራቸው ይቅርም በላቸው፡፡ ለዘላለሙ አሜን፡፡

## ካህን (ሕዝብ ካህኑን ይቀበል)

ሀበነ ንኅበር በዘዚአከ መንፈስ ቅዱስ፤ ወፈውሰነ፤ በዝንቱ ጵርስፎራ፤ ከመብከ ንህየው፤ ዘለኵሉ ዓለም፤ ወለዓለመ ዓለም

የአንተ በሚሆን በመንፈስ ቅዱስ አንድ እንሆን ዘንድ በዚሁም በሥጋው በደሙ አድነን ለዓለሙ ሁሉ በምትሆን በአንተ ለዘለዓለሙ ሕያው እንሆን ዘንድ

Grant us to be untied through Thy Holy Spirit, and heal us by this oblation that we may live in Thee for ever.

## ካህን (ሕዝብ ካህኑን ይቀበል)

ቡሩክ ስሙ ለእግዚአብሔር፥ ወቡሩክ ዘይመጽእ፥ በስመ እግዚአብሔር፥ ወይትባረክ፥ ስመ ስበሀቲሁ ለይኩን፥ ለይኩን፥ ቡሩከ ለይኩን

የእግዚአብሔር ስሙ ምስጉን ነው በእግዚአብሔር ስም የሚመጣውም ምስጉን ነው ጌትነቱም ይመስገን ይሁን ይሁን ይመስገን ይሁን

Blessed be the name of the Lord, and blessed be He that cometh in the name of the Lord, and Let the name of His Glory be blessed. So be it, so be it, so be it blessed.

ካህን (ሕዝብ ካህኑን ይቀበል)

ፈኑ፲ ጸጋ መንፈስ ቅዱስ ላዕሌነ

የመንፈስ ቅዱስ ፀጋ ላክልን

Send the grace of the Holy Spirt upon us.

ዲያቆን

ተንሥኡ ለጸሎት

ለጸሎት ተነሱ

Stand up for prayer.

ሕዝብ

እግዚኦ ተሣሃለነ

አቤቱ ይቅር በለን

Lord have mercy upon us.

ካህን

ሰላም ለኵልክሙ

ሰላም ለሁላችሁ ይሁን

Peace be unto you all.

ሕዝብ

ምስለ መንፈስከ

ከመንፈስህ ጋር

And with Thy spirit

# ካህን

ወካዕበ ናስተበቍዖ ለአኃዜ ዓለም ወቤዛሆሙ እምኃጢአቶሙ፡፡ ተዘከር ሥጋ እንተ ነሣእከ እምቅድስት ድንግል እንቲአነ ሥጋ አኮ እሰማያት ዘአውረድከ፡፡

ዳግመኛም ዓለምን የያዘውን ኃጢአታቸውም ቤዛ የሆናቸውን እርሱን እንማልደዋለን፡፡ ከቅድስት ድንግል የነሣኸው ሥጋ የኛ ሥጋ እንደ ሆነ ከሰማይ ያወረድኸው እንዳደለ አስብ፡፡

# ካህን

ተዘከር ሥጋ አንተ ነሣአከ እምቅድስት ድንግል ከመ ውእቱ ሥጋ ዘቆመ ቅድመ ጲላጦስ፡፡

ከቅድስት ድንግል የነሣኸው ሥጋ በጲላጦስ ፊት የቆመ ሥጋ እንደ ሆነ አስብ፡፡

# ካህን

ተዘከር ሥጋ እንተ ነሣእከ እምቅድስት ድንግል ከመ ውእቱ ሥጋ ዝግሐታት መዋቅሕት ዘጸረ።

ከቅድስት ድንግል የነሣኸው ሥጋ የማሠሪያ መዘጋትን የተሸከመ ሥጋ እንደ ሆነ አስብ።

# ካህን

ተዘከር ሥጋ እንተ ነሣአከ እምቅድስት ድንግል ከመ ውእቱ ሥጋ ዘሐመ ወሞተ።

ከቅድስት ድንግል የነሣኸው ሥጋ የታመመው የሞተውም እንደ ሆነ አስብ።

# ካህን

ተዘከር ሥጋ እንተ ነሣእከ እምቅድስት ድንግል ከመ ውእቱ ሥጋ ዘተንሥአ እሙታን በሣልስት ዕለት፡፡

ከቅድስት ድንግል የነሣኸው ሥጋ ሦስተኛው ቀን ከሙታን ተለይቶ የተነሣው ሥጋ እንደ ሆነ አስብ፡፡

## ካህን

ተዘከር ሥጋ እንተ ነሣእከ እምቅድስት

ድንግል ከመ ውእቱ ሥጋ ዘዐርገ በስብሐት ውስተ ሰማያት ወነበረ በየማነ አቡሁ፡፡ ወካዕበ ይመጽእ በውእቱ ሥጋ ምስለ ኃይለ መለኮቱ እግዚአብሔር አምላክነ፡፡

ከቅድስት ድንግል የነሣኸው ሥጋ በክብር በምስጋና ወደ ሰማይ ያረገ በአባቱም ቀኝ የተቀመጠው እንደ ሆነ አስብ፡፡ ዳግመኛም አምላካችን እግዚአብሔር በዚህ ሥጋ ከመለኮቱ ኃይል ጋራ ይመጣል፡፡

ዲያቆን

# ጸልዩ

Pray ye.

## ሕዝብ

አቡነ ዘበሰማያት ይትቀደስ ስምከ፤ ትምጻእ መንግሥትከ፤ ወይኩን ፈቃድከ በከመ በሰማይ ከማሁ በምድር። ሲሳየነ ዘለለ ዕለትነ ሀበነ ዮም። ኅድግ ለነ አበሳነ ወጌጋየነ ከመንህነኒ ንኅድግ ለዘአበሰ ለነ። ኢታብአነ እግዚኦ ውስተ መንሱት አላ አድኅነነ ወባልሃነ እምኵሉ እኩይ፤ እስመ ዚአከ ይእቲ መንግሥት ኃይል ወስብሐት ለዓለመ ዓለም።

Our Father who art in heaven, hallowed be Thy name, Thy kingdom come, Thy will be done on earth as it is in heaven; give us this day our daily bread, and forgive us our trespasses as we forgive them that trespass against us, and lead us not into temptation but deliver us and rescue us from all evil; for Thine is the kindom, the power and the glory for ever and ever.

## ካህን

ዔና መዓዛ ሠናይ ከመ ታእምሩ ዔና መዓዛሁ ምሥጥዎ ለሕሊናክሙ ኀበ መልዕልት ኀበ ሀሎ ዝንቱ ኅብስት፡፡

መዓዛው ያማረ ሽታ ነው፤ የመዓዛውን ሽታ ታውቁ ዘንድ አሳባችሁን ይህ ኅብስት ወዳለበት ወደ ላይ አውጡት፡፡

## ካህን

ነጽሩ ነፍሰክሙ ወአንጽሑ ነፍስተክሙ ወኢ.መኑሂ እምኔነ ኢ.ይድወይ በብዝኀ አበሳ ወኃጢ.አት፡፡

ነፍሳችሁን መርምሩ ሰውነታችሁንም አንጹ፡፡ ከኛ ወገን ማንም በበደልና በኃጢ.አት ብዛት አይታመም፡፡

# ካህን

ናሁ ሀሎ ምስሌነ ዮም ዲበ ዝንቱ ማዕድ አማኑኤል በግዑ ለእግዚአብሔር ናሁ ሀሎ አብ ብርሃን ምስለ ወልዱ ወምስለ መንፈስ ቅዱስ።

የእግዚአብሔር በግ አማኑኤል እነሆ ዛሬ ከኛ ጋራ በዚህ ማዕድ ላይ አለ። እነሆ ብርሃን አብ ከልጁ ጋራ ከመንፈስ ቅዱስም ጋራ አለ።

# ካህን

ሁ ሀለዉ መላእክተ ብርሃን እለ ይሔውጹ ቤተ ክርስቲያን ነጽሩ ነፍሰክሙ ወአንጽሑ ነፍስተክሙ ወኢመኑሂ እምኔነ ኢይድወይ ቦ ዘአበሳ ወቦ ዘኃጢአት፡፡

ቤተ ክርስቲያንን የሚጐበኙ የብርሃን መላእክት እነሆ አሉን ነፍሳችሁን መርምሩ ሰውነታችሁንም አንጹ ከኛ ወገን ማንም ማን አይታመም፡፡

# ካህን

ቅሕ ሕሊናነ ከመ ንኩን ድልዋነ ለነሚአ ዝንቱ ምሥጢር ለዓለመ ዓለም፡፡

የበደል አለ፤ የኃጢአትም አለ፤ ይህንንም ምሥጢር ለመቀበል የተገባን እንሆን ዘንድ ሕሊናችንን ንቁሕ እናድርግ ለዘላለሙ፡፡

ይ.ሕ.

ሠራዊተ መላእክቲሁ ለመድኃኔ ዓለም ይቀውሙ ቅድሜሁ ለመድኃኔ ዓለም፡፡ ወይኬልልዎ ለመድኃኔ ዓለም ሥጋሁ ወደሙ ለመድኃኔ ዓለም፡፡

የመድኃኔ ዓለም የመላእክት ሠራዊት በመድኃኔ ዓለም ፊት ይቆማሉ፡፡ መድኃኔ ዓለምን ያመሰግኑታል የመድኃኔ ዓለም ሥጋውና ደሙ፡፡

# ካህን

የመድኃኔ ዓለም የመላእክት ሠራዊት በመድኃኔ ዓለም ፊት ይቆማሉ፡፡ መድኃኔ ዓለምን ያመሰግኑታል የመድኃኔ ዓለም ሥጋውና ደሙ፡፡

የመድኃኔ ዓለም የመላእክት ሠራዊት በመድኃኔ ዓለም ፊት ይቆማሉ፡፡ መድኃኔ ዓለምን ያመሰግኑታል የመድኃኔ ዓለም ሥጋውና ደሙ፡፡

# ካህን

ወንብጻሕ ቅድመ ገጹ ለመድኃኔ ዓለም በአሚነ ዚአሁ ለክርስቶስ ንገኒ፡፡ ወቦ ዘይቤሉ ጻድቃን ተጋደሉ በእንቲአሁ፡፡

ከመድኃኔ ዓለም ፊት እንድረስ፡፡ እርሱን በማመን ለክርስቶስ እንገዛለን፡፡ ጻድቃን ስለርሱ ተጋደሉ የሚሉም አሉ፡፡

ዲያቆን ንፍቅ

አርኀዉ ኆኃተ መኳንንት

መኳንንት ደጆችን ክፈቱ

Open ye the gates, princes.

ዲያቆን

እለ ትቀውሙ አትሕቱ ርእሰክሙ

የቆማችሁ ሰዎች ራሳችሁን ዝቅ ዝቅ አድርጉ

Ye Who are standing, bow your heads.

# ካህን

ነአኵተከ እግዚኦ በፍቁር ወልድከ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘአቅረብከነ ቅድመ ዕበየ ልዕልናከ ለከ ስብሐት ወክብር ወአኰቴት ለዓለመ ዓለም፤ አሜን።

በልጅህ በወዳጅህ በኢየሱስ ክርስቶስ ወደጌትነትህ ገናንነት ፊት ያቀረብኸን አቤቱ እናመሰግንሃለን። ላንተ ጌትነትና ክብር ምስጋናም ይገባል ለዘላለሙ፤ አሜን።

ዲያቆን

ስግዱ ለእግዚአብሔር በፍርሃት
በፍርሃት ሆናችሁ ለእግዚአብሔር ስገዱ
Worship the Lord with fear.

ሕዝብ

ቅድሜከ እግዚኦ ንሰግድ ወንሴብሐከ
አቤቱ በፊትህ እንሰግዳለን
Before Thee, Lord, we worship, and Thee do we glorify.

ካህን

ጸሎተ ንስሐ

የንስሐ ጸሎት

Prayer of Pentence

አቤቱ ዓለምን ሁሉ የያዝህ ጌታችን እግዚአብሔር አብ
የነፍሳችንንና የስጋችንን፤ የደመ ነፍሳችንንም ቍስል የምታድን
አንተ ነህ። በአንድ ልጅህ በጌታችን በአምላካችንና
በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ አፍ ተናግረሃልና፤ ለአባታችን
ለጴጥሮስ እንዲህ ብሎ የተናገረውን አንተ ድንጋይ ነህ በዚህችም
ድንጋይ ላይ ክብርት ቤተ ክርስቲያኔን እሰራታለሁ የሲኦልም
ደጆች ሊያጠፏትና ሊያነዋውጧት አይችሉም። ሳንተም
የመንግስተ ሰማያትን መክፈቻ እሰጥሃለሁ በምድር ያሰርኸው
በሰማይ የታሰረ ይሆን ዘንድ፤ በምድርም የፈታኸው በሰማይ
የተፈታ ይሆን ዘንድ።

O Lord God, the Father almighty, it is Thou that healest the wounds of our soul and our body and our spirit, because Thou hast said, with the mouth of Thy only-begotten Son, our Lord and our God and our Savior Jesus Christ, that which He said to our father Peter, Thou art a rock and upon this rock  I will build my holy church, and the gates of hell shall not prevail against it, and unto thee I give the keys of the Kingdom of heaven, what thou hast bound on earth shall be bound in heaven, and what thou hast loosed on earth shall be loosed in heaven:

ወንዶቹም ሴቶቹም ባሮችህ ሁሉ በየስማቸው የተፈቱ
ነጻም የወጡ ይሁኑ በመንፈስ ቅዱስ ቃል ኃጥእ
በደለኛ በምሆን በእኔም በባርያህ _ቃል በማወቅ ወይም
ባለማወቅ ቢሰሩ። አቤቱ እኚህን ባሮችህን አባቶቼንና
ወንድሞቼን እኅቶቼንም አጽንተህ ጠብቃቸው።
ዳግመኛም ኃጥእ በደለኛ የምሆን እኔን ወራዳነቴን
አይተህ ፍታኝ

Let all Thy servants and Thy handmaids, according to their several names, be absolved and set free out of the mouth of the Holy Spirit, and out of the mouth of me also Thy sinful and guilty servant… whether they have wrought wittingly or unwittingly. Keep them, Lord, and defend them, they servants, my fathers, brothers and sisters.

ልዩ ሶስት በሚሆኑ በአብና በወልድ በመንፈስ ቅዱስም ቃል የተፈቱ ነጻም የወጡ ይሁኑ። ኃጥእ በደለኛ በምሆን በእኔም በባርያህ ቃል። መሀሪም ይቅር ባይ ሰውንም የምትወድ አምላካችን እግዚአብሔር ሆይ የዐለምን ኃጢአት የምታርቅ የወንዶቹንና የሴቶቹን ባሮችህን ንስሃቸውን ተቀበል። የዘላለም ደኅንነት የሚሆን ብርሃንንም ግለጽላቸው፤ አቤቱ ኃጢታቸውንም ሁሉ ይቅር በላቸው፤ ቸር፤ ሰውንም የምትወድ አንተ ነህና

And absolve them and set them free out of the mouth of the holy Trinity, the Father and the Son and the Holy Spirit, and out of the mouth of me Thy sinful and unrighteous servant. O powerful, merciful and lover of man, Lord our God, that takest away the sin of the world, accept the penitence of Thy servants and Thy handmaids, and shine upon them with the light of everlasting life, and forgive them, Lord, all their sins; for thou art good and the lover of man.

ይቅር ባይ አምላካችን እግዚአብሔር ሆይ መዓትህ የራቀ ምህረትህም የበዛ እውነተኛም የምትሆን የኔን ሀጢአቴን አስተስርይልኝ ወንዶችንና ሴቶችንም ባሮችህንም ሁሉ ከመደልም ከመርገምም ሁሉ አድናቸው በቃላችንም ቢሆን በስራችንም ቢሆን በአሳባችንም ቢሆን አቤቱ አንተን ብንበድል ተውልን አስተሥርይ አቃልልን ይቅርም በለን አምላካችን እግዚአብሔር ሆይ አንተ ቸር ሰውን ወዳጅ ነህና።

O Lord our God, merciful, slow to anger, plenteous in mercy and righteous, forgive me my sins; and deliver all Thy servants and handmaids, and shine upon them with the light of everlasting life, and forgive them, Lord, all their sins; for thou art good and the lover of man.

አቤቱ የተፈታንም ነጻ የወጣን አድርገን፤ ወገኖችህንም ሁሉ ፍታቸው ኃጥእ የምሆን እኔንም ባርይህን ፍታኝ። ክቡር የሚሆን የሊቃነ ጳጳሳቱን አለቃ አባ ___ አስበው። ብጹእ የሚሆን አባ አስበው። አምላካችን ሆይ ለብዙ ዘመናት ለረጅም ወራት በእውነትና በሰላም መጠበቅን ጠብቅልን

O Lord, absolve us and set us free, and absolve all Thy people, and absolve me Thy sinful servant. Lord the honorable father, our Patriarch Abba… and the blessed Archbishop Abba…. Our God, keep them for us for many years and length of days in righteousness and peace.

አቤቱ ኢትዮጵያን አስባት የሚጣሏትንና ጠላቶቿን ከእግሯ በታች ፈጥነህ አስገዛላት።የጳጳሳቱን አለቆች ጳጳሳቱንና ኤጲስ ቆጶሳቱን፤ ቀሳውስቱንና ዲያቆናቱን አንባቢዎችንና መዘምራኑን ደናግሉንና መነኰሳቱን። ባልቴቶችንና አባት እናት የሞቱባቸውን፤ ወንዶቹንና ሴቶቹን፤ ሽማግሌዎቹንና ልጆቹን፤ ክብርት በምትሆን በዚህች ቤተ ክርስቲያን ያሉትን የቆሙትንም የክርስቲያንን ወገኖች ሁሉ ክርስቶስን በማመን አጽናቸው

Remember, Lord, our country, Ethiopia, subdue her dversaries and her enemies under her feet speedily. Remember, Lord the Patriarchs, archbishops, bishops, priests and deacons, anagnosts and singers, virgins and monks, widows and orphans, men and women, aged and children; and all Christian people that are standing in this holy church; strengthen them in the faith of Christ.

አቤቱ በቀናች ሃይማኖት ሆነው የሞቱትንና ያረፉትን አባቶቻችንንና እናቶቻችንን ወንድሞቻችንንና እኅቶቻችንንም ሁሉ አስባቸው። ነፍሶቻቸውንም በአብርሃምና በይስሀቅ በያእቆብም አጠገብ አኑር። እኛንም ከኃጢአት ሁሉ ከመርገምም ከበደልም ሁሉ ከክህደትም ሁሉ በሀሰትም ከመማል ሁሉ ከመገዘትም ሁሉ አድነን። በክህደትና በርኩሰት ከዓላውያንና ከአረማውያን ጋራ አንድ ከመሆን አድነን

Remember, Lord, all our fathers, brothers and sisters that are asleep and resting in the orthodox faith, andlay their souls in the bosom of Abraham, Isaac and Jacob. And as for as, deliver us from every transgression andcurse and from all wickedness and from all rebellion and from all false swearing and from all anathema and from all perjury and from mingling with heretics and gentiles in error and defilement.

አቤቱ ጥበብንና ኃይልን ልብንና ልቡናን እውቀትንም ስጠን። እንግዲህ ከሚፈታተነን ከሰይጣን ስራ ሁሉ እስከ ዘላለሙ እንርቅ እንሸሽም ዘንድ አቤቱ ሁል ጊዜ ፈቃድህን ውድህንም እንሰራ ዘንድ ስጠን። ስማችንንም በመንግስተ ሰማያት በህይወት መጽሀፍ ከቅዱሳንና ከሰማእታት ሁሉ ጋራ ጻፍ፤ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ፤ በርሱ ያለ ክብር ጽንእ ለአንተ ይገባል፤ ከርሱ ጋራ ከመንፈስ ቅዱስም ጋራ፤ ዛሬም ዘወትርም ለዘላለሙ አሜን።

Grant us, Lord, wisdom and power and reason and understanding and knowledge that we may depart and flee for evermore from all works of Satan the tempter. Grant us, Lord, to do Thy will and Thy good pleasure at all times, and write our names in the book of life in the kingdom of heaven with all saints and martyrs, through Jesus Christ our Lord, through whom to thee with Him and with the Holy Spirit be glory and dominion, both now and ever and world without end. Amen.

ዲያቆን

ነጽር

ተመልከት

Give heed.

ካህን

ቅድሳት ለቅዱሳን

Holy things for the Holy.

## ሕዝብ

አሐዱ አብ ቅዱስ
አሐዱ ወልድ ቅዱስ
አሐዱ ውእቱ መንፈስ ቅዱስ
አንዱ ቅዱስ አብ ነው፤
አንዱ ቅዱስ ወልድ ነው፤
አንዱ ቅዱስ መንፈስ ቅዱስ ነው።
One is the Holy Father,
One is the Holy Son,
One is the Holy Spirit.

## ካህን

**እግዚአብሔር ምስለ ኵልክሙ**

**እግዚአብሔር ከሁላችሁ ጋር ይሁን**

The Lord be with you all

## ሕዝብ

**ምስለ መንፈስከ**

**ከመንፈስህ ጋራ**

And with Thy spirit

ካህን (ሕዝብ ይቀበላል)

# እግዚኦ መሐረነ ክርስቶስ

# አቤቱ ክርስቶስ ማረን

# Lord have compassion upon us O! Christ!

## ዲያቆን

እለ ውስተ ንስሃ ሀለውክሙ አትሀቱ ርእሰክሙ

በንሰሐ ውስጥ ያላችሁ ራሳችሁን ዝቅ ዝቅ አድርጉ

Ye that are penitent, bow your heads.

### ካህን

አምላካችን እግዚአብሔር ሆይ በንስሓ ውስጥ ወዳሉት ወገኖች ተመልከት እንደ ይቅርታህም ብዛት ይቅር በላቸው። እንደ ቸርነትህም ብዛት በደላቸውን አጥፋላቸው፤ ከክፉም ነገርም ጠብቃቸው ሰውራቸውምኾ የቀደመ ስራቸውን ይቅር ብለህ በሰላም ነፍሳቸውን አድን፤ ከቅድስት ቤተ ክርስቲያንህ አንድ አድርጋቸው፤ ተቀዳሚ ተከታይ በሌለው ባንድ ልጅህ በጌታችንና በአምላካችን በመድታኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በይቅርታውና በምህረቱ ከቅድስት ቤተ ክርስቲያንህ ጨምራቸው። በርሱ ያለ ክብር ጽንእ ስአንተ ይገባል፤ ከርሱ ጋራ ከመንፈስ ቅዱስም ጋራ፤ ዛሬም ዘወትርም ስዘላለሙ አሜን።

Lord our God, look upon thy people that are penitent, and according to thy great mercy have mercy upon them, and according to the emultitude of the compassion blot out their iniquity, cover them and keep them from all evil. And redeem their souls in peace, forgive their former works. Join them with they Holy church; through the grace and compassion of thy only begotten son our Lord and our God and our SaviorJjesus Christ, through whom to Thee with him and with the Holy Spirit be glory and dominion, both now and ever and world without end. Amen.

## ዲያቆን

ተንሥኡ ለጸሎት

ለጸሎት ተነሱ

Stand up for prayer.

## ሕዝብ

እግዚኦ ተሣሃለነ

አቤቱ ይቅር በለን

Lord have mercy upon us.

## ካህን

ሰላም ለኵልክሙ

ሰላም ለሁላችሁ ይሁን

Peace be unto you all.

## ሕዝብ

ምስለ መንፈስከ

ከመንፈስህ ጋር

And with Thy spirit.

ይ.ካ.

ሥጋ ቅዱስ ዘበአማን ዝ ውእቱ ዘእግዚእነ ወአምላክነ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘይትወሀብ ለሕይወት ወለመድኃኒት ወለሥርየተ ኀጢአት ለእለ ይነሥኡ እምኔሁ በአሚን አሜን፡፡

በእውነት ክቡር የሚሆን የጌታችንና የአምላካችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋ ይህ ነው፡፡ ምነው ከርሱ ለሚቀበሉ ሕይወትና መድኃኒት የኃጢአት ማስተሥረያም ሊሆን የሚሰጥ፡፡ አሜን፡፡

ይ.ካ.

ደም ክቡር ዘበአማን ዝ ውእቱ ዘእግዚእነ ወአምላክነ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘይትወሀብ ለሕይወት ለመድኃኒት ወለሥርየተ ኃጢአት ለእለ ይትሜጠው እምኔሁ በአሚን፡፡

ይ.ሕ.

አሜን፡፡ በእውነት አምነው ከርሱ ለሚቀበሉ ሕይወትና መድኃኒት የኃጢአት ማስተሥረያም ሊሆን የሚሰጥ የጌታችንና የአምላካችን የኢየሱስ ክርስቶስ ክቡር ደም ይህ ነው፡፡ አሜን፡፡

ይ.ካ.

እስመ ዝንቱ ውእተ ሥጋሁ ወደሙ ለአማኑኤል አምላክነ ዘበአማን፡፡

ይ.ሕ.

አሜን፡፡ በእውነት የአማላካችን አማኑኤል ሥጋውና ደሙ ይህ ነውና፡፡

ይ.ሕ.

አሜን፡፡

ይ.ካ.

አአምን አአምን አአምን ወእትአመን እስከ ደኃሪት እስትንፋስ ከመ ዝንቱ ውእቱ ሥጋሁ ወደሙ ለእግዚእነ ወአምላክነ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘነሥአ ምእግዝእተ ኵልነ ቅድስት ድንግል በ2 ማርያም፡፡

ይ.ሕ.

አሜን፡፡ አምናለሁ አምናለሁ አምናለሁ፡፡ እስከ መጨረሻዪቱም እስትንፋስ እታመናለሁ፤ በሁለት ወገን ድንግል ከምትሆን ከሁላችን እመቤት ከቅድስት ማርያም የነሣው የጌታችንና የአማላካችን የመድኃኒታችንም የኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋው ደሙ ይህ እንደ ሆነ፤

ይ.ካ.

ወረሰዮ 1ደ ምስለ መለኮቱ ዘእንበለ ቱስሕት ወኢትድምርት፤ ዘእንበለ ፍልጠት ወኢውላጤ ወኮነ ሰማዕተ በስምዕ ሠናይ በመዋዕለ ጲላጦስ ጰንጤናዊ ወመጠዎ በእንቲአነ ወበእንተ ሕይወተ ኵልነ።

ይ.ሕ.

ያለመቀላቀልና ያለትድምርት ለመለወጥና ያለመለየት ከመለኮቱ ጋራ አንድ ያደረገው፤ በጰንጤናዊ ጲላጦስም ዘመን ባማረ ምስክርነት ምስክር የሆነ፤ ስለ እኛና ስለ ሁላችንም ሕይወት አሳልፎ የሰጠው።

ይ.ካ.

አአምን አአምን አአምን ወእትአመን ከመ ኢተፈልጠ መለኮቱ እምትስብእቱ ኢአሐተ ሰዓተ ወኢከመ ቅጽበተ ዓይን አሳመጠዎ በእንቲአነ ለሕይወት ወለመድኃኒት ወለሥርየተ ኃጢአት ለእለ ይትሜጠዉ እምኔሁ በአሚን፡፡

አምናለሁ አምናለሁ አምናለሁ፡፡ መለኮቱ ከሰውነቱ አንዲት ሰዓት እንኳን አንድ ዓይን ቅጽበትስ ስንኳ እንዳልተለየም እታመናለሁ፤ ስለኛ ሰጠው እንጂ፤ ለሕይወትና ለመድኃኒት ለኃጢአትም ማስተሥረያ ሊሆን አምነው ለሚቀበሉ ሰዎች ስለኛ አሳልፎ ሰጠው እንጂ፡፡ አሜን፡፡

ይ.ካ.

አአምን አአምን አአምን ወእትአመን ከመ ዝንቱ ውእቱ ሥጋሁ ወደሙ ለእግዚእነ ወአምላክነ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ፡፡ ዝውእቱ ዘሎቱ ይደሉ ክብር ወስብሐት ወስግደት ምስለ አቡሁ ኄር ሰማያዊ ወመንፈስ ቅዱስ ማሕየዊ ይእዜኒ ወዘልፈኒ ወለዓለመ ዓለም፤ አሜን፡፡

አምናለሁ አምናለሁ አምናለሁ፡፡ የጌታችንና የአምላካችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋው ደሙ ይህ እንደ ሆነ እታመናለሁ፡፡ ክብርና ምስጋና ስግደትም ቸር ከሚሆን ከሰማያዊ አባቱ ጋራ ምሕየዊ ከሚሆን ከመንፈስ ቅዱስ ጋራ የሚገባው ይህ ነው፡፡ ዛሬም ዘወትርም ለዘላለሙ፤ አሜን፡፡

# የዕለቱ ምንባብ

# ከሃይማኖቴ አበው

## ቍርባኑ ከመቀበል አስቀድሞ
## ከቅዱስ ምሥጢር የሚቀበሉ ሁሉ እዲህ ይበሉ፡፡

አቤቱ ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ርኩስት ከሆነች ከቤቴ ጠፈር በታች ትገባ ዘንድ የሚገባኝ አይደለም። እኔ አሳዝኜሃለሁና፤ በፊትህም ክፉ ስራ ሰርቻለሁና፤ በአርአያህና በአምሳልህ የፈጠርኸው ስጋዬንና ነፍሴን ትእዛዝህን በማፍረስ አሳድፌአለሁና፤ ስራም ምንም ምን የለኝምና ነገር ግን ስለ መፍጠርህና እኔን ለማዳን ሰው ስለ መሆንህ፤ ስለ ክቡር መስቀልህም ማኅየዊት ስለምትሆን ስለሞትህ፤ በሶስተኛውም ቀን ስለ መነሳትህም ጌታዬ ሆይ ከበደልና ከመርገም ሁሉ ከኃጢአትና ከርኲሰትም ሁሉ ታነጻኝ ዘንድ እለምንሃለሁ፤ እማለድሃለሁም

O my Lord Jesus Christ, it in no wise beseemeth Thee to come under the roof of my polluted house, for I haveprovoked Thee to wrath, and have done evil in Thy sight, and through the transgressionof Thy commandment have polluted my soul and my body which Thou dedst create after Thy image and Thy likeness, and in me dwelleth no good thing. But for the sake of Thy contrivance and Thy incarnation for my salvation, for the sake of Thy precious cross and Thy life-giving death, for the sake of my resurrection on the third day, I pray Thee and bessech Thee, O my Lord, that Thou wouldest purge me from all guilt and curse and from all sin and defilement.

የቅድስናህንም ምስጢር በተቀበልሁት ጊዜ ለወቀሳ ለመፈራረጃ አይሁንብኝ፤ ማረኝ ይቅርም በለኝ፤ እንጂ። የዓለም ህይወት ሆይ በርሱ የኃጢአቴን ስርየት የነፍሴንም ሕይወት ስጠኝ እንጂ። በሁለት ወገን ድንግል በምትሆን በወለደችህ በእመቤታችን በቅድስት ማርያም፤ በመጥምቁ በዮሀንስም አማላጅነት፤ ክቡራን በሚሆኑ በመላእክትም በሰማእታትና ለበጎ ነገር በሚጋደሉ በጻድቃንም ሁሉ ጸሎት፤ እስከ ዘላለሙ ድረስ አሜን።

And when I have received Thy holy mystery let it not be unto me for judgement nor for condemnation, but have compassion upon me and have mercy upon me; and through it grant me remission of my sin and life for my soul, O life of the world, through the petition of our Lady, the holy Mary of twofold virginity Thy mother, and of John the Baptist, and through the prayer of all the holy angels and all the martyrs and righteous who have fought for the good, world without end. Amen.


ማርያም፡ድንግል፡
ምስለ፡ፍቁር፡ወልዳ።

ካህን

ሰላም ለኪ እንዘ ንሰግድ ንብለኪ
ማርያም እምነ ናስተበቍዓኪ

ሰላም ላንቺ ይሁን እያልን እንሰግዳለን፤
እናታችን ማርያም ሆይ እንማልድሻለን

Peace be unto you, while bowing unto you, our mother Mary, we as for your prayers

## ሕዝብ

እምአርዌ ነዓዊ ተማኅፀነ ብኪ፤ በእንተ ሐና እምኪ፤ ወኢያቄም አቡኪ፤ ማኅበረነ ዮም ድንግል ባርኪ

ከአዳኝ አውሬ ታድኝን ዘንድ ተማጽነንብሻል፤ ስለ እናትሽ ሐና ስለ አባትሽም ኢያቄም ድንግል ሆይ አንድነታችንን ዛሬ ባርኪልን

Protect us from evil animals. For the sake of thy mother, Hanna, and your father, Iyakem, O! Virgin bless this day.

## ካህን

**ይወርድ መንፈስ ቅዱስ በላዕለ ኅብስቱ ወወይኑ፤ ሶበ ይብል ካህን ጸጋ መንፈስ ቅዱስ ፈኑ**

**ካህኑ የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ ላክ ባለ ጊዜ መንፈስ ቅዱስ በኅብስቱና በወይኑ ላይ ይወርዳል**

As the priest says let the Holy Spirit descend, on this revered Holy of Holies.

## ሕዝብ

ማዕከለ ዛቲ ቅድስት ቤተ ክርስቲያኑ ይዌልጦሙ በቅጽበት አባለተ ክርስቶስ ይኩኑ፤ በኃይለ ጥበቡ መንክር ወዕፁብ ኪኑ

አስደናቂ በሚሆን የጥበቡ ኃይልና በአስገራሚ ብልሃቱ በቅድስት ቤተ ክርስቲያኑ መካከል የክርስቶስ አባሎች ይሆኑ ዘንድ በቅጽበት ይለውጣቸዋል

The Holy Spirit will descend upon the bread and wine, His special Spirit will transform them in an instant with His wisdom towards the Flesh and Blood.

ካህን

ሰላም ለክሙ ጻድቃን ወሰማዕት ዕለ አዕረፍክሙ በሃይማኖት

በሃይማኖት ያረፋችሁ ጻድቃን ሰማዕታት ሰላም ለናንተ ይሁን

Peace be unto you, blessed and martyrs, who have died for the faith.

## ሕዝብ

መዋዕያን ዓለም አንትሙ በብዙኃ ትዕግሥት ሰአሉ ቅድመ ፈጣሪ በኵሉ ሰዓት፤ እንበለ ንስሐ ኪያነ ኢይንሥአ ሞት

በብዙ ትዕግሥት ዓለምን ድል የነሳችሁ እናንተ፤ ለንስሐ ሳንበቃ ሞት እንዳይወስደን በየሰዓቱ በፈጣሪ ፊት ቆማችሁ ለምኑልን

Ye who have conquered the world by patience, pray for us day and night standing in front of our Creator, so that death will not take us before we have repented.

ካህን

ሰላም ለክሙ ጻድቃን ዛቲ ዕለት ኩልክሙ ፤ እድ ወአንስት በበአስማቲክሙ

በዚህች ዕለት ጻድቃን ሁላችሁ ሰላም ለናንተ ይሁን ወንዶችም ሴቶችም በየስማችሁ

Peace be unto you, all those blessed on this day, men and women according to your name.

## ሕዝብ

ቅዱሳን ሰማይ ወምድር ማኅበረ ሥላሴ አንትሙ፤
ዝክሩነ በጸሎትክሙ በእንተ ማርያም እሙ፤
ተማኅፀነ በክርስቶስ በሥጋሁ ወበደሙ

በሰማይና በምድር የከበራችሁ የሥላሴ ወገኖች፣
ስለ እናቱ ስለ ማርያም ብላችሁ በጸሎታችሁ
አስቡን በክርስቶስ ሥጋና ደም ተማጽነባችሁ

Ye that are glorified in heaven and on earth, friends of the Holy Trinity; remember us in your prayers for the sake of Mary and for the sake of Christ's flesh and blood, we beseech You.

# በመቀባበል

እግዚኦ መሐረነ ክርስቶስ (፫ ጊዜ)

አቤቱ ክርስቶስ ሆይ ማረን (3 ጊዜ)

Lord have compassion upon us, O! Christ, Lord. (3 times)

በእንተ ማርያም መሐረነ ክርስቶስ (፫ ጊዜ)

ክርስቶስ ሆይ ስለ ማርያም ማረን (3 ጊዜ)

For the sake of Mary, have compassion upon us, O! Christ, Lord (3 times)

ካህን

ሰአሊ ለነ ማርያም፥ ምሕረተ ወልድኪ ሳህሎ ይከፍለነ።

ማርያም ሆይ! የልጅሽን ምህረት ለምኝልን፤ ይቅርታውን ያደርግልን ዘንድ።

O Mary, pray for our mercy, so that He may forgive us.

ዲያቆን

**ጸልዩ በአንቲአነ ወበእንተ ኵሎሙ ክርስቲያን እለ ይቤሉነ ግበሩ ተዝካሮሙ በሰላም፤ ወበፍቅረ ኢየሱስ ክርስቶስ ሰብሑ ወዘምሩ**

**ስለእኛና አስቡን ስላሉን ስለ ክርስቲያኖች ሁሉ ጸልዩ፤ በኢየሱስ ክርስቶስ ሰላምና ፍቅር አመስግኑ ዘምሩም**

Pray Ye for us and for all christians who bade us to make mention of them. Praise Ye and sing in the peace and love of Jesus Christ.

## በቊርባን ሰዓት በኅብረት

ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ ሥሉስ ዘኢይትነገር፤ ሀበኒ ከመ እንሣእ ለሕይወት ዘንተ ሥጋ ወደመ ዘእን በለ ኰነኔ...

የማይነገር ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ ሦስት የምትሆን ይህንን ሥጋና ደም ሕይወት ሊሆነኝ ሳይፈረድብኝ እቀበል ዘንድ ስጠኝ...

Holy! Holy! Holy! Trinity ineffable, grant me to receive this Body and this Blood for life and not for condemnation. ...

ሀበኒ እግበር ፍሬ ዘያሰምረከ ከመ አስተርኢ
በስብሀቲከ ወእሕየው ለከ እንዘ እገብር
ዘዚአከ ፈቃደ፤

በጌትነትህ እንድገለጽ ደስ የሚያሰኝህን ፍሬ
እሠራ ዘንድ ስጠኝ፤ የአንተንም ፈቃድ
እየሠራሁ እኖርልህ ዘንድ ስጠኝ፤

Grant me to bring forth fruit that shall be well pleasing unto Thee, to the end that I may appear in Thy glory and live unto Thee doing Thy will.

በተአምኖ እጼውአከ አብ ወእጼውዕ መንግሥተከ ይትቀደስ እግዚኦ ስምከ በላዕሌነ፤ እስመ ኃያል አንተ እኩት ወስቡሕ ወለከ ስብሐት ለዓለመ ዓለም

በማመን አባት ብዬ እጠራሃለሁ፣ አቤቱ ስምህ በኛ ላይ ይመስገን፤ ምስጉን ክቡር የምትሆን ኃያል አንተ ነህና ለአንተ ክብር ይገባሃል ለዘለዓለሙ

In faith, I call upon Thee, Father, and call upon Thy Kindom; hallowed, Lord, be Thy name upon us, for mighty art Thou, praised and glorious, and to Thee be glory, world without end.

## በቁርባን ሰዓት በኅብረት የሚደጋገም

… እስመ ኃያል አንተ እኩት ወስቡሕ ወለከ ስብሐት ለዓለመ ዓለም

… ኃያል አንተ ነህና ለአንተ ክብር ይገባሃል ለዘለዓለሙ

… for Mighty art Thou, praised and glorious, and to Thee be Glory, for ever and ever.

## ዲያቆን

ነአኵቶ ለእግዚአብሔር ቅድሳቶ ነሢአነ፤ ከመ ለሕይወተ ነፍስ ይኩነነ ፈውሰ ዘተመጦነ ንስእል ወንትመኅፀን እንዘ ንሴብሖ ለእግዚአብሔር አምላክነ።

ሥጋውን ደሙን ተቀብለን እግዚአብሔርን እናመሰግነዋለን ለነፍሳችን አኗኗር መድኃኒት ይሆነን ዘንድ የተቀበልን እኛ አምላካችንን እግዚአብሔርን እያመሰገንን እንለምናለን፤ አደራም እንላለን።

We thank God for that we have partaken of His Holy things; we pray and trust that that which we have received may be healing for the life of the soul while we glorify the Lord our God.

ካህን

**አሌዕለከ ንጉሥየ ወአምላኪየ ወእባርክ ስምከ ለዓለም ወለዓለመ ዓለም ።**

**ንጉሤና ፈጣሪዬ ሆይ! ከፍ ከፍ አደርግሃለሁ፤ ቅዱስ ስምህንም ለዘለዓለም አመሰግናለሁ ።**

I will extol Thee, my King and my God, and I will bless Thy name for ever and ever.

## ሕዝብ

**አቡነ ዘበሰማያት ኢታብአነ እግዚኦ ውስተ መንሱት።**

**በሰማይ ያለህ አባታችን ሆይ አቤቱ ወደ ፈተና አታግባን።**

Our Father Thou art in heaven,
lead us not, Lord, into temptation.

## ዲያቆን

**ተመጠነ እምሥጋሁ ቅዱስ ወእምደሙ ክቡር ለክርስቶስ።**

**ከክርስቶስ ከቅዱስ ሥጋውና ከክቡር ደሙ ተቀበልን።**

We have received of the Holy Body and the precious Blood of Christ.

ካህን

ኵሎ አሚረ እባርከከ ወእሴብሕ ለስምከ ለዓለም ወለዓለመ ዓለም።

ዘወትር አከብርሃለሁ፤ ቅዱስ ስምህን ለዘለዓለሙ አመሰግናለሁ።

Every day will I bless Thee, and I will praise Thy name for ever and ever.

ሕዝብ

አቡነ ዘበሰማያት ኢታብአነ እግዚኦ ውስተ መንሱት።

በሰማይ ያለህ አባታችን ሆይ አቤቱ ወደ ፈተና አታግባን።

Our Father Thou art in heaven,
lead us not, Lord, into temptation.

ዲያቆን

ወናእኩቶ ይደልወነ ከመ ንሳተፍ ምሥጢረ ክብርተ ወቅድስት።

ክብርት ቅድስት የምትሆን ምሥጢርን እንሳተፍ ዘንድ ስለበቃን ልናመሰግነው ይገባል።

And let us give thanks unto him that make us meet to communicate in the precious and holy mystery.

## ካህን

ስብሐተ እግዚአብሔር ይነግር አፉየ ወኵሉ ዘሥጋ ይባርክ ለስሙ ቅዱስ፤
ለዓለም ወለዓለመ ዓለም።

አንደበቴ የእግዚአብሔርን ምስጋና ይናገራል፤ የሥጋ ፍጥረትም ሁሉ ቅዱስ የሚሆን ስሙን ያመሰግናል ለዘላለሙ።

My mouth shall speak the praise of the Lord, and let all flesh bless His Holy name for ever and ever.

ሕዝብ

አቡነ ዘበሰማያት ኢታብአነ እግዚኦ ውስተ መንሱት።

በሰማይ ያለህ አባታችን ሆይ አቤቱ ወደ ፈተና አታግባን።

Our Father Thou art in heaven,
lead us not, Lord, into temptation.

# ካህን

ቀዳሚሁ ቃል ውእቱ ቃል ቃለ እግዚአብሔር
ውእቱ ቃል ሥጋ ኮነ ወኅደረ ላዕሌነ፡፡ ወርኢነ
ስብሐቲሁ ከመ ስብሐት 1ዱ ዋሕዱ ለአቡሁ፡፡
ውእቱ ቃል ውስተ ዚአሁ መጽአ ወእሊአሁሰ
ኢተወክፍዎ፡፡

ያ ቃል ቀድሞ የነበረ ነው፡፡
ያ ቃል የእግዚአብሔር ቃል ነው
ያ ቃል ሥጋ ሆነ በኛም አደረ፡፡
ለአባቱ አንዳንድ ልጅ ክብር የሚሆን ክብሩን
አየን፡፡ ያ ቃል ወደ ወገኖቹ መጣ ወገኖቹ ግን
አልተቀበሉትም፡፡

ሕዝብ

ንሕነ እሙንቱ እለ ተወከፍኖ 3)0ወ8ቱ ርቱዓነ ሃይማኖት ሠራዕያነ ሕገጋቲሃ ለቅድስት ቤት ክርስቲያን ዘውእቱ መርዓዊሃ እግዚአብሔር አምላክነ፡፡

የተቀበልነው እኛ ሦስት መቶ አሥራ ስምንቱ ነን፡፡ ሃይማኖትን ያቀናን ሙሽራዋ አምላካችን እግዚአብሔር የሆነ የቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ሕግ የሠራን፡፡

ይ.ዲ.

ጸልዩ፡፡

## ካህን

አንተ ውእቱ ዘየዐውዱከ ኪሩቤል እለ ብዙኃት አዕይንቲሆሙ ወሱራፌል እለ 6ቱ ክነፊሆሙ፡፡

ዓይኖቻቸው ብዙዎች የሚሆኑ ኪሩቤል ክንፎቻቸው ስድስት የሚሆኑ ሱራፌል የሚከቡህ አንተ ነህ፡፡

**ካህን**

ኦ ዘለሐኮ ለአዳም በዘዚአከ አርአያ ወአምሳል ኦ ዘወጣሕኮ ለእሳት ዲበ ማይ። ኦ ዘኢይጸልሞ ጽልሙት ወኢይሜወሮ ሌሊት አንተ ውእቱ ዘአቅረብከነ ቅድመ ዝንቱ ምሥጢር ለከ ስብሐት ወክብር ወአኰቴት ለዓለመ ዓለም።

አዳምን በአንተ አርኣያና አምሳል የፈጠርከው ሆይ እሳትን በውኃ ላይ ያሰፈርከው ሆይ። ጨለማ የማይጨልምበት ሌሊትም የማይሠወረው ሆይ ወደዚህ ምሥጢር ፊት ያቀረብከን አንተ ነህ። ለአንተ ጌትነት ክብር ምስጋናም ይገባል ለዘላለሙ።

**ይ.ሕ.** አሜን።

## ካህን

ሃሌ ሉያ ሃሌ ሉያ አቡነ ዘበሰማያት ይትቀደስ ስምከ ሥረይ ለነ ኰሎ አበሳነ ኢታብአነ ውስተ መንሱት እግዚኦ አድኅነነ አምዕለት እኪት ወባልሐነ እምኵሉ መንሱት።

ሃሌ ሉያ ሃሌ ሉያ በሰማይ ያለህ አባታችን ሆይ ስምህ ይቀደስ ኃጢአታችንን ሁሉ አስተሥርይልን፤ አቤቱ ወደ ፈተና አታግባን ከክፉ ቀን አድነን ከፈተናም ሁሉ አድነን።

ካህን

መልዐት እግዚኦ ምሥጢርከ ቅድስት እንተ ኢትማስን ዘወሀብከነ ለነ ኃይለ ወመድኃኒነ ተዝካረ ሞትከ ዘህልው ምስሌከ።

አቤቱ የማታልፍ ቅድስት ምሥጢርህ ለሁሉ ተሰጠች። ካንተ ጋራ ያለ የሞትህን መታሰቢያ ኃይልንና መድኃኒትን ለኛ የሰጠኸን።

## ካህን

ወርኢነ ምሥጢረ ትንሣኤከ ቅድስት ወአውርሰነ ሕይወተ ወዕቀበነ ቦቱ በዛቲ ሰዓት ወበኵሉ ጊዜ፤ እስመ አንተ ንጉሥ ክቡር ላዕለ ኵሉ እግዚእነ ወአምላክነ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ።

ክብርት የምትሆን የትንሣኤህንም ምሥጢር አየን፤ ሕይወትንም አውርሰን። በዚህች ሰዓት በጊዜውም ሁሉ በርሱ ጠብቀን። ጌታችንና አምላካችን መድኃኒታችንም ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ በሁሉ ላይ የከበርህ ንጉሥ አንተ ነህና ላንተ ምስጋናን ገናንነትን ክብርንም እናቀርብልሃለን።

ካህን

ለከ ናዐርግ አኰቴተ ዕበየ ወክብረ ምስለ አቡከ ኄር ሰማያዊ ወምስለ መንፈስ ቅዱስ ማሕየዊ ለዓለመ ዓለም፤ አሜን፡፡

ሰማያዊ ከሚሆን ከቸር አባትህ ጋራ፤ ማሕየዊ ከሚሆን ከመንፈስ ቅዱስም ጋራ ለዘላለሙ፤ አሜን፡፡

ከማየ መቅረር በኋላ የሚጸለይ ጸሎት ነው፤
የሁሉም ነውና በአንድነት ይድገሙ፡፡

አቤቱ ጌታዬ አምላኬ ወዳንተ እጸልያለሁ፤ እለምንሃለሁም መንጋህን የወደድህ ቸር ጠባቂ ለበጎችህ ቤዛ ሰውነትህን የሰጠህ በእውነት የጽድቅ መብል ሥጋህንና የዘለዓለም የእውነት መጠጥ የሚሆን ደምህን ትሰጠኝ ዘንድ፡፡

ጻግመኛም ጌታዬ ሆይ ይህ የተቀበልሁት ሥጋህና ደምህ ሥጋዬንና ነፍሴን እንዳያስነቅፍና እንዳያሳድፍ እለምንሃለሁ፤ እማልድሃለሁ፡፡

ፈጽሞ የሚያድነኝ አንተን መፍራትንም የሚያስረዳኝ ፍቅርህንም የሚያስተምረኝ ይሁን እንጂ፤ በሕይወቴ ዘመን ሁሉ ሳንተ አደላ ዘንድ ያለ ማቋረጥም አመሰግንህ ዘንድ፡፡

አቤቱ ሰውነቴን አንጻት ላንተ መሥዋዕት ትሆን ዘንድ ዳግመኛም አጽራት፤ ልቡናዬንም እንዲድን መንፈስ ቅድሱ እንዲያድርበትና እንዲመላበት አድርገው። ሥጋህንና ደምህን አምኜ ተቀብያለሁና ከካህናቱም እጅ ተቀብዬ በሳሁ ላንተ ምስጋና ይገባል፤ ለዘላለሙ፤ አሜን።

ይ.ዲ.

ስለ ማመስገናችን እንማልዳለን፤ እግዚአብሔር በሕይወት መጽሐፍ ልመናችንን ይጽፍ ዘንድ ለዘላለሙ የሚኖር አምላክም በቅዱሳን ማደሪያ በርሱ ብርሃን ያስበን ዘንድ። ወደ ኋላ ስላሉ አባቶቻችንና ወንድሞቻችን ስለ እኅቶቻችንም እንማልዳለን፤ እግዚአብሔር ትጋትን ይሰጣቸው ዘንድ ለሁሉም ያስብ ዘንድ። የዚህን ዓለም ማሠሪያን ከነርሱ ይመልስ ዘንድ፤ ሥርዓትን ፍቅርንና ማመንን በጎ ተስፋንም ይሰጣቸው ዘንድ፤ ስለ እግዚአብሔር ልጅ ሥጋና ደም፤ ለዘላለሙ አሜን ይሁን ይሁን።

ወደ ኋላ ስላሉ አባቶቻችንና ወንድሞቻችን ስለ እኅቶቻችንም እንማልዳለን፤ እግዚአብሔር ትጋትን ይሰጣቸው ዘንድ ለሁሉም ያስብ ዘንድ። የዚህን ዓለም ማሠሪያን ከነርሱ ይመልስ ዘንድ፤ ሥርዓትን ፍቅርንና ማመንን በጎ ተስፋንም ይሰጣቸው ዘንድ፤ ስለ እግዚአብሔር ልጅ ሥጋና ደም፤ ለዘላለሙ አሜን ይሁን ይሁን።

## ካህን

ኦ እግዚኦ እግዚእነ ወአምላክነ ወመድኀኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ ባርከነ ወቀድሰነ፡፡ ወረስየነ ንኩን ድልዋነ ከመ ንሑር ውስተ አብያቲነ በፍሥሓ ወበሐሤት ዘእንበለ ኃጢአት ወዘእንበለ ደነሰ፡፡

አቤቱ ጌታችንና አምላካችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ባርከን ቀድሰን፡፡ ያለ ኃጢአት ያለ ርኵሰት በፍጹም ደስታ ወደ ቤታችን ለመሄድ የበቃን እንድንሆን አድርገን፡፡

## ካህን

ተመጦነ ሥጋከ ወደምከ እምክብርት ማዕድከ ይኩነነ ዘያሐይወነ፡፡ ወመንፈስከ ቅዱሰ እግዚኦ ፈኑ ለነ ከመ ይመርሐነ ውስተ ፍኖተ ጽድቅ ወሕይወት፡፡

ከክብርት ማዕድህ የተቀበልነው ሥጋህና ደምህ የሚያድነን ይሁንልን፡፡ አቤቱ ቅዱስ መንፈስህንም ላክልን ወደ ጽድቅና ወደ ሕይወት ጐዳና ይመራን ዘንድ፡፡

# ካህን

ሥጋሁ ወደሞ ሥርዐ ወልደ እግዚአብሔር ሕያው ውስተ ዓለም ከመ ንብላዕ እምኔሁ ወከመ ንሕየው ምስሌሁ፡፡

የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ሥጋውንና ደሙን በዚህ ዓለም ሠራ፡፡ ከርሱ በልተን ከርሱ ጋራ እንኖር ዘንድ፡፡

## ካህን

አቅርበነ ኀቤከ በምሕረትከ ኀበ ምሥዋዒከ ሕያው ወቅዱስ ንሰመይ ገብሮ ለእግዚአብሔር ወምዕራፎ ለልዑል፡፡ ወንቅረብ ኀቤሁ ኵልነ፡፡ በስኢል ወበሰጊድ በጸሎት ወበንጽሕ ንብጻሕ ቅድመ ገጹ በአሚን፡፡

ሕያውና ቅዱስ በሚሆን መሠውያህ ዘንድ በምሕረትህ ወደ አንተ አቅርበን፡፡ የእግዚአብሔር ባሮች የልዑልም ማረፊያ እንባል ዘንድ፡፡ ሁላችንም ወደርሱ እንቅረብ በልመናና በስግደት በጸሎትና በንጽሕና በማመን ከፊቱ እንደርስ ዘንድ፡፡

ካህን

ሥጋሁ ቅዱስ ወደሙ ክቡር ዘተመጠነ በእደዊሆሙ ለካህናት እለ ያዐርጉ ጸሎተ ወስእለተ በኵሉ ጊዜ ወበኵሉ ሰዓት ይኩነነ ለሕይወት ለተስፋ ወለመድኀኒት ለሥርየተ ኀጢአት ወለትንሣኤ ሙታን ለዓለመ ዓለም አሜን፡፡

በየጊዜው ሁሉ በየሰዓቱም ሁሉ ጸሎትንና ልመናን በሚያሳርጉ በካህናት እጅ የተቀበልነው ቅዱስ ሥጋውና ክቡር ደሙ ለሕይወት ለተስፋ ለመድኀኒትና ለኀጢአት ማስተሥረያ ከሙታንም ተለይቶ ለመነሣት ይሁነን፤ ለዘላለሙ አሜን፡፡

## ሕዝብ

አባታችን ሆይ በሰማያት የምትኖር ስምህ ይቀደስ መንግስትህ ትምጣ ፈቃድህ በሰማይ እንደሆነች እንድሁ በምድር ትሁን  የእለት እንጀራችንን ስጠን ዛሬ በደላችንንም ሁሉ ይቅር በለን እኛም የበደሉንን ይቅር እንደምንል አቤቱ ወደ ፈተና አታግባን ከክፉ ሁሉ አድነን እንጂ መንግስት ያንተ ናትና ሀይል ክብር ምስጋና ለዘላለሙ አሜን።

Our father who art in heaven, hallowed be thy name, Thy  Kingdom come, Thy will be done on earth as it is in heaven;  Give us this ay our trespasses as we forgive them that  trespass against us, and lead us not into temptation but  deliver us and rescue us from all evil; for Thine is the  kingdom, the power and the glory for ever and ever. Amen

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ሆይ በመልአኩ
በቅዱስ ገብርኤል ሰላምታ ሰላም እንልሻለን በሀሳብሽ
ድንግል ነሽ በስጋሽም ድንግል ነሽ የአሸናፊ የእግዚአብሔር
እናት ሆይ ሰላምታ ለአንቺ ይገባሻል ከሴቶች ሁሉ
ተለይተሽ አንቺ የተባረክሽ ነሽ የማህጸንሽም ፍሬ የተባረከ
ነው ጸጋንየተመላሽ ድንግል ሆይ ደስ ይበልሽ እግዚአብሔር
ከአንቺ ጋር ነውና ከተወደደው ልጅሽ ከጌታችን
ከመድኅኒታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ዘንድ ይቅርታንና
ምህረትን ለምኝልን ሀጢአታችንን ያስተስርይልን ዘንድ
ለዘላለሙ አሜን።

O Our Lady, Virgin St. Mary! In St. Gabriel’s greetings, Peace be unto you. Holy and pure, O mother of the almighty God! Peace be unto you. Blessed are thou amongst women and blessed is the fruit of thy womb. Hail Mary, full of Grace, the Lord is with Thee. Pray for us before our Lord Jesus Christ that he may forgive us our sins. Amen


አጋዕዝተ፡ዓለም፡ሥላሴ።

## ዲያቆን

**አድንኑ አርእስቲክሙ ቅድመ እግዚአብሔር አምላክነ በእደ ገብሩ ካህን ከመ ይባርክሙ**

**በአምላካችን በእግዚአብሔር ፊት ራሳችሁን ዝቅ ዝቅ አድርጉ፤ አገልጋይ በሚሆን በካህኑ እጅ ይባርካችሁ ዘንድ**

Bow your heads in front of the Lord our God, that He may bless you at the hand of His servant the priest.

**ይ.ሕ.**

**በእደ ገብሩ ካህን አሜን ይባርከነ፡፡**

**ይ.ሕ.**

**አገልጋዩ በሚሆ በካህኑ እጅ አሜ ይባርከ፡፡**

People:

Amen, may He bless us at the hand of His servant the priest.

ካህን

አቤቱ ሕዝብህን አድን ርስትህንም ባርክ። አቤቱ ህዝብሕን አድን ርስትህንም ባርክ (በሕዝቡ ላይ 3 ጊዜ ባርክ) እስከ ዘላለሙ ጠብቃቸው ከፍ ከፍም አድርጋቸው በአንድ ልጅህ በጌታችንና በአምላካችን በመድታኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በክቡር ደሙ የዋጀሃት ቤዛም የሆንካት ቅድስት ቤተ ክርቲያንህንም ጠብቃት

Priest:-

O Lord, save thy people and bless the inheritance. Feed them, lift them up for ever, and keep Thy church which thou didst purchase and ransom with the precious blood of Thy only-begotten Son, our Lord and our God and our Savior Jesus Christ;

ለነገስታትና ለመኳንንት ለንጹህ ወገንና ቅዱስ ለሆነ ህዝብ ማደሪያ ትሆን ዘንድ የጠራሃት በዚህች ቅድስት ቤተ ክርስቲያን መጥታችሁ ተሰብስባችሁ የጸለያችሁ፤ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ቅዱስ ስጋውን የበላችሁ፤ ክቡር ደሙንም የጠጣችሁ በማወቅ ወይም ባለማወቅ የሰራችሁትን ታጢአታችሁን ይቅር ይበላችሁ

And  which thou hast called to be a dwelling–place for kings and rulers, for pure kindred and holy people, you who have come and gathered and prayed in his holy church, and you who have eaten the Holy body and drunk the precious blood of our Lord Jesus Christ. May he forgive your sins which you have committed wittingly or unwittingly.

ስጋ መለኮት ስለሚባል ስጋው የህግና የስርኣት ደም ስለሚሆን ደሙ የአሸናፊ የእግዚአብሔር ልጅ በድንጋሌ ስጋ በድንጋሌ ህሊናም ኅትምት የምትሆን የማርያም ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ ባለፈውም ይቅር ይበላችሁ፤ በሚመጣውም ይጠብቃችሁ። ለዘላለሙ አሜን።

May he forgive you your past sins and keep you from future ones, for the sake of his body, the divine body, and for the sake of his blood, the blood of the covenant of Jesus Christ the Son of the Lord of hosts, and the Son of pure Mary, who has sealed the virginity of her conscience and body, world without end . Amen.

ኑዛዜ ይሰጣል

እግዚኦ መሀረነ ክርስቶስ (12 ጊዜ)
አቤቱ ይቅር በለን

በእንተ እግዝእትነ ማርያም መሀረነ ክርስቶስ (12 ጊዜ)
ስለ እመቤታችን ማርያም ብለህ ይቅር በለን

**ካህን**

እግዚአብሔር ይሐሉ ምስለ ኵልክሙ

እግዚአብሔር ከሁላችሁ ጋራ ይሁን

The Lord be with you all

**ሕዝብ**

ምስለ መንፈስከ

ከመንፈስህ ጋራ

And with thy spirit

## ሕዝብ

አሜን እግዚአብሔር ይባርከነ ለአግብርቲሁ በሰላም ሥርየተ ይኩነነ ዘተመጦነ ሥጋከ ወደመከ አብሓነ በመንፈስ ንኪድ ኵሎ ኃይሎ ለጸላዒ

አሜን እግዚአብሔር እኛን አገልጋዮቹን በሰላም ይባርከን፤ የተቀበልነውን ሥጋህና ደምህ ለሥርየት ይሁነን፤ የጠላትን ኃይል ሁሉ በመንፈስ እንረግጥ ዘንድ አሰልጥነን

Amen may God bless us, His servants, in peace. Remission be unto us who have received Thy body and Thy blood. Enable us by the Spirit to tread upon all the power of the enemy.

## ሕዝብ

በረከተ እዴከ ቅድስት እንተ ምልዕተ ምሕረት ኪያሃ ንሴፎ ኵልነ እምኵሉ ምግባረ እኩይ አግኅሰነ ወውስተ ኵሉ ምግባረ ሠናይ ደምረነ ቡሩክ ዘወሀበነ ሥጋሁ ቅዱሰ ወደሞ ክቡረ

ምሕረትን የተመላች ክብርት የምትሆን የእጅህን በረከት ሁላችን ተስፋ እናደርጋለን ከክፉ ሥራ ሁሉ አርቀን፤ በበጎውም ሥራ ሁሉ አንድ አድርገን ቅዱስ ሥጋውን ክቡር ደሙንም የሰጠን ብሩክ ነው

We all hope for the blessing of Thy holy hand which is full of mercy. From all evil works keep us apart, and in all good works unite us. Blessed be He that hath given us His holy body and His precious blood.

## ሕዝብ

ጸጋ ነሣእነ ወሕይወተ ረከብነ በኃይለ መስቀሉ ለኢየሱስ ክርስቶስ፤ ኪያከ እግዚኦ ነአኲትነሚአነ ጸጋ ዘእመንፈስ ቅዱስ

ጸጋን ተቀበልን፤ ደህንነትንም በኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀሉ ኃይል አገኘን፤ አቤቱ ከመንፈስ ቅዱስ የተገኘ ጸጋን ተቀብለን አን ተን እናመሰግንሃለን

We have received grace and we have found life by the power of the cross of Jesus Christ. Unto Thee, Lord, do we give thanks, for that we have received grace from the Holy Spirit.

ዲያቆን

እትው በሰላም

በሰላም ወደ ቤታችሁ ግቡ

Go ye in peace.


አጋዕዝተ፡ዓለም፡ሥላሴ።


ቅዱስ፡ሚካኤል፡
ቅዱስ፡ገብርኤል፡
ማርያም፡ድንግል፡
ምስለ፡ፍቁር፡ወልዳ።